# በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች አሰላለፍ እና የፖለቲካ ትብብር ጥያቄ

**በአምሃ ዳኘው**

**የጽሁፉ አላማ**

ኢኮኖሚ የተባለ ሳምንታዊ ጋዜጣ በየካቲት ወር ውስጥ ባወጣው እትሙ ላይ የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች ፖለቲካ የምርጫ ጊዜ ፖለቲካ እንደሆነ፣ ከምርጫ በፊት ያለውን ጊዜያቸውን በአብዛኛው የሚያሳልፉት በፖሊሲ እና ስትራቴጂ ጉዳዬች ዙሪያ ያሏቸውን ልዩነቶች ነቅሶ ለማውጣት፣ ሊጣጣሙ የሚችሉትን ለማጣጣም፣ ሊጣጣሙ የማይችሉትን በልዩነት በማስቀመጥ ተከባብረው በየግላቸው አመለካከታቸውን ለማራመድ የሚችሉበትን ሁኔታ በመፍጠር ላይ ሳይሆን፤ አንዱ ሌላውን በማዳከም ተግባር ላይ እንደሆነ፣ ምርጫ በተቃረበ ቁጥር ውህደት ህብረት ጥምረት ወዘተ… እያሉ ገዥውን ፓርቲ ለመጣል ብቻ የሚያራምዱት ፖለቲካ ደካማ ፖለቲካ እንደሆነ በስፋት ዕፎበታል። (ኢኮኖሚ 36፡ 2,10-11)

ጋዜጣው ከዚህ ቀደም ተመስርተው የነበሩ የተቃዋሚዎች ህብረቶች ሊያስወግዷቸው ያልቻሉ ተደጋጋሚ ስህተቶችን ሲዘረዝር፣

1ኛ/ ህብረቶቹ የተሞከሩት የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከት ባላቸው ድርጅቶችና ግለሰብ መሪዎች መካከል መሆኑ እና የድርጅቶቹ ልዩነቶች በሚገባ ታውቀው ሊቻቻሉ የሚችሉበት ስልት ሊቀየስ አለመቻሉ፣

2ኛ/ የድርጅቶቹ መሪዎች የፖለቲካ ስብእና መሪነትን ለመልቀቅ የማይፈቅድ መሆኑና የመሪነት ቦታን ሙጥኝ ብሎ ለመያዝ ያለ ፍላጐትን ለመተው ያለመቻል፣

3ኛ/ የእስካሁኖቹ የህብረት ሙከራዎች በድርጅት መሪዎችና አንቱ በሚባሉ ፖለቲከኞች መቀራረብ ላይ ብቻ የተመሠረቱ እና ድርጅታዊ አቅምና ህዝባዊ መሠረት ያልነበራቸው መሆኑ፣

4ኛ/ የእስካሁኖቹ ህብረቶች ከምርጫ ጋር የተያያዙና ምርጫ ሲቃረብ የሚውጠነጠኑ በመሆናቸው ከምርጫ በኂላ ዘላቂ ሁነው ሊቀጥሉ የሚችሉበት ሁኔታ አልታዬም በማለት በአራት ዘርፍ ከፍሎ አቅርቧቸዋል።

ስለሆነም በአሁኑ ወቅት የፖለቲካ ድርጅቶች ተቀራርበው መስራትን ሲያስቡ እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ድክመቶች ከግንዛቤ በማስገባት ሊታረሙ የሚችሉበትን ሁኔታ መቀየስ ያስፈልጋቸዋል።

በሌላ በኩል በሃገራችን በአሁኑ ወቅት የብዙሃን ፓርቲ ህልውና የተረጋገጠበት የፖለቲካ ስርአት አለ ቢባልም፣ በተጨባጭ የሚታዬው ሁኔታ ግን የገዢው ፓርቲ አምባገነንነት የሰፈነበት የፖለቲካ ስርዓት አግጦ የመታየቱ ሁኔታ ነው። ይህ ሊሆን የቻለው በኢህአዴግ ጥፋት እና ጥንካሬ ብቻ አይደለም። ባለፉት ዓመታት እንደታዘብነው የኢትዮጵያን የተቃውሞ ፖለቲካ እንመራለን የሚሉ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ፓርቲዎችን በተቋማዊ መልክ (Institutional capacity) አጠናክረው ሲገነቡ፣ አመሠራረታቸውንም ሆነ አሠራራቸውን ዲሞክራሲያዊ ሲያደርጉ፣ አመራሮቻቸውን ለድርጅት ደንብ እና ዓላማዎች ሲያዝገዙ አልታዩም። ከዲሞክራሲያዊ ድርጅት ግንባታ ይልቅ ለግል ዝናና ጥቅም አለፍ ሲልም ከፓርቲ ፕሮግራም ሳፈነገጠ የቡድን ተልእኮ የሚሰሩ ሁነው ታይተዋል።

የመንግሥት ስልጣን በፓርቲ እንጅ በግለሰብ ሊያዝ እንደማይገባ፣ ለመንግሥት ስልጣን ከሚደረግ ፉክክር በፊት የፖለቲካ ፓርቲን እንደ ተቋም መገንባት እንደሚያስፈልግ ተገቢ ትኩረት ሲሰጠው አይስተዋልም። የአፍሪካ ፖለቲካ ትልቁ ችግር ይኸ ነው። ፓርቲን እንደ ተቋም ዲሞክራሲያዊ በሆነ ዘይቤ የመገንባቱ ፍላጐትም ሆነ ልምድ ባለመኖሩ፣ ከፓርቲዎች ይልቅ የፓርቲ መሪዎች ገነው ይታያሉ። ይህ ደግሞ ፖለቲካን ዲሞክራሲያዊ ወደ ሆነ አቅጣጫ ሳይሆን ወደ ፈላጭ ቆራጭነት (authoriterian) አቅጣጫ እንዲያመራ ያደርገዋል። ይህ በብዙ የአፍሪካ አገሮች የሚታይ ፓርቲን እንደተቋም ያለመገንባት ችግር ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ለገዥ ፓርቲዎች ደባ ወይም ምልጃ እንዲጋለጡ

-------------------------

* ይህ ፅሁፍ በታህሳስ ወር መጀመሪያ ላይ ለፓርቲው ሥ/አስፈፃሚ ኮሚቴ ቀርቦ የነበረ ፅሁፍ ነው። በአቶ አምሃ ዳኘው የአንድነት ፓርቲ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል እና የጥናት እና ምርምር ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ናቸው። ተዘጋጅቶ ለአንድነት ጥናት እና ምርምር ቋሚ ኮሚቴ ቀርቦ የዳበረ እና በቋሚ ኮሚቴው የጸደቀ ጽሁፍ ነው። ጽሁፉ ውይይት ሳይደረግበት ቆይቶ በጥር ወር አጋማሽ ላይ ለብሄራዊ ምክር ቤት አባላት እንዲዳረስ ተደረገ። ያም ሁኖ በፓርቲው አካላት ውስጥ እስካሁን ድረስ ውይይት ስላልተካሄደበት፣ የመድረክ ስብስብ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች እና ታዋቂ ግለሰቦች በታህሣሥ ወር ሁለተኛ አጋማሽ ላይ ለሴሚናር ያቀረቡአቸው ጥናታዊ ፅሁፎች ሲገኙ ይህን ፅሁፍ እንደገና በሴሚናሩ ላይ ከቀረቡ ጽሁፎች ጋር አገናዝቦ ማዘጋጀቱ የግድ ሆነ። ይህ ፅሁፍ የዚህ አገናዝቦ የማቅረብ ጥረት ውጤት ነው።

አድርጐ በማዳከም የመድበለ ፓርቲ ስርዓት እንዳይጠናከር አድርጐታል፡፡ ከዚህ አይነት ሁኔታ ወደ ዛቀኛ የብዙሃን ፓርቲ አሰራር ለመሸጋገር እና የተጣበበውን የሃገሪቱን የፖለቲካ  ምህዳር ለማስፋት የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን ራሳቸውን በሂስ መነፅር አዙረው በመመልከት ድክመቶቻቸውን ነቅሰው በማውጣት ለማሻሻል ቁርጠኝነተ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በየጊዜው የሚነሳው እና የሚከሽፈው የተቃውሞ ፖለቲካ ትብብርም ከምርጫ ያለፈ ሁኖ መቀየስ ይኖርበታል፡፡

ስለብዙሃን ፓርቲ ስርዓት ያለው ግንዛቤም የተዛባ ነው፡፡ በአንድ አገር ያለን የፖለቲካ ስርዓት የብዙሃን ፓርቲ ወይም መድበለ ፓርቲ የሚያሰኘው የፖለቲካ  ፓርቲዎች ቁጥር በዝቶ መገኘቱ አይደለም፡፡ ከመቶ በላይ ፓርቲዎች ኑረው ፕሮግራማዊ ይዘታቸው ተመሳሳይ ከሆነ የብዙሃን ፓርቲ ስርዓት አለ ለማለት አይቻልም፡፡ የብዙሃን ፓርቲ ስርዓት አለ ለማለት የሚቻለው ቁጥራቸው በጣም አናሳ ሁነውም ቢሆን እያንዳንዳቸው ግልፅ ያሉ እና የተለያዩ የፖለቲካ፣ የኢኰኖሚ እና የማህበራዊ ፕሮግራማዊ አማራጮችን ይዘው የቀረቡ መሆናቸው ሲረጋገጥ ነው፡፡ የሃገራችን የተቃውሞ ፖለቲካ ይህን መሠረታዊ ጉዳይ ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይጠበቅበታል፡፡ ገዥ ፓርቲው የሚከተላቸውን ዘርፈ ብዙ ፖሊሲዎች መቃወም ብቻውን የተቃውሞ ፖለቲካ ሊባል አይገባም፡፡ የተቃውሞ ፖለቲካን ማራመድ በየዘርፉ አማራጭ ፖሊሲዎችን ዘርዝር አድርጐ መቀመርና ለህዝብ ማሳወቅ ይጠይቃል፡፡

እያንዳንዱ ፓርቲ በፓርቲነት ሲቋቋም የራሱ የሆኑ አመለካከቶች፣ አላማዎች እና ራዕዬች ሊኖሩት ይገባል፡፡ በአመለካከት ዙሪያ ትብብር ከመፍጠር በፊት ደግሞ በቅድሚያ የራስን የፖለቲካ አቋም በግልፅ መቀመር፤ የሌሎችንም በሚገባ ማወቅን ይጠይቃል፡፡ ሊታረቁ የማይችሉ አመለካከቶች በሁሉም ዘንድ ታውቀው መከበር ይኖርባቸዋል፡፡ ተቀራራቢ እና ሊታረቁ የሚችሉትን አቀራርቦ እና አጣጥሞ የትብብር መሠረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ አማራጭ ፖሊሲን እና አመለካከትን በትክክል ቀምሮ ማቅረብ ማን ከማን የተለየ ለማን የቀረበ አቋም እንዳለው ሕዝቡ እንዲያውቅ ይረዳል፡፡ ተቃውሞ ደግሞ ከድርጅታዊ አመለካከት እና ከፖሊሲ ጋር እንጂ ከድርጅት ጋር ወይም ድርጅትን ከሚመሩ ሰዎች ጋር ሊሆን አይገባም፡፡ ሌላው እና መናልባትም ተቃዋሚዎች ከኢህአዴግ ሊማሩት የሚገባው ስልጣን ለመያዝ ከመሞከር በፊት ፓርቲን ሁለአቀፍ በሆነ ሁኔታ አደራጅቶ የመገኘትን አስፈላጊነት ነው፡፡ አለ ተጠናከረ ፓርቲ ስልጣን ለመያዝ መሞከር በሃገር ላይ ከመቀለድ ተነጥሎ ሊታይ አይችልም፡፡ የተጠናከረ ፓርቲ ሲባል ግን እንደ ኢህአዴግ በማሌ ድርጅታዊ መርሆዎች ላየ የተገነባ ሳይሆን ከዘመኑ ጋር የሚሄድ በዲሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ የተገነባ እና የሚንቀሳቀስ ፓርቲ ሊሆን ይገባል፡፡ ትብብርም ሲታሰብ በተጠናከሩ እና ህዝባዊ መሠረት ባላቸው ፓርቲዎች መካከል ቢሆን ነው ለሃገር ጠቀሜታ ያለው ውጤት ሊያስገኝ የሚችለው፡፡ ይህ እውን ባልሆነበት ሁኔታ የተቃውሞ ፖለቲካ ንግድ ይሆናል፡፡ ፖለቲካና ንግድ የተለያዩ ሙያዎች ስለሆኑ መቀላቀለቸው አግባብነት የለውም፡፡ የፖለቲካ ትብብር መሠረቱ ጥርት ብሎ በተቀመጠ የፖለቲካ ራእይ እና ዓላማ ዙሪያ ያለ የአመለካከት አንድነት ወይም ተቀራራቢነት ነው፡፡ ከዚህ ውጭ የሚደረግ ትብብር "ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ" እንደማለት ይሆናል፡፡

ሌላው ከአፍሪካ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአጠቃላይ ከኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚጐለው የፖለቲካ ግልፅነት አስፈላጊነትን በተገቢ ሁኔታ ያለመገንዘብ ነው፡፡ በሃገራችን የፖለቲካ ባህል የተወረሰ አንዱ መጥፎ ልማድ ፖለቲካን እንደሚሰጥር እና ድብቅ ሊሆን እንደሚገባው ነገር የመመልከቱ መጥፎ ባህል ነው፡፡ ፖለቲካ ግልፅ እና ቀጥተኛ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ፖለቲካ (politics) የተሰኘው የእንግሊዘኛ ቃል ራሱ የተገኘው/የመጣው "ፖሊቲኰስ" (politikos) ከተሰኘው የግሪክ ቃል ነው፡፡ "ፖለቲኰስ" የተሰኘው የግሪክ ቃል ወደ እንግሊዘኛ ሲተረጐም "of the citizen" ማለት ነው፡፡ ወደ አማርኛ ሲተረጐም "የዜጋ ጉዳይ" ወይም ዜጋን የሚመለከት ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ የዜጋ ጉዳይ ማለት ደግሞ ዜጋን ከሃገር ነጥሎ ለማየት ስለማይቻል፣ ስለ ሃገር ጉዳይ የሚኖር አመለካከት ማለት ነው፡፡ ይኽ ደግሞ ሚስጥርነት ሊኖረው የሚችል ጉዳይ አይደለም፡፡ በመሆኑም ሚስጥራዊነትን ከሃገራችን ፖለቲካ ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡ በኢትዮጵያ የተቃውሞ ፖለቲካ ወደ መድበለ ፓርቲ ፖለቲካ ሊሸጋገር የሚችለው ይህን ዓይነት አካሄድን እንደ ጥሩ ባህል አድርጐ ሲቀበል እና ሲሰራበት ነው፡፡

ከግንቦት 1997 ምርጫ በፊት በነበሩ ጥቂት ወራት ውስጥ ኢህአዴግ የህዝቡን የፖለቲካ ብስለት በሚገባ ባለማገናዘብ አንጻራዊ በሆነ ሁኔታ አንዳንድ የፖለቲካ መብቶችን ለቀቅ አድርጎ ነበር፡፡ ህዝቡ ያገኘውን አጋጣሚ ተጠቅሞ  የደረሰበት ውሳኔ  ለኢህአዴግ በእጅጉ አስደንጋጭ ነበር፡፡ ከዚያ ሁኔታውን በትክክል ለማገናዘብ ከተገደደበት አጋጣሚ በመነሳት ያንን ያህል የፖለቲካ  ክፍተት ዳግም ላለመልቀቅ ኢህአዴግ መወሰኑን በብዙ ከዚያን ጊዜ ወዲህ በሚወስዳቸው እርምጃዎች አረጋግጧል፡፡ ጠቅላይ ሚ/ር መለስ ዜናዊ በሰኔ ወር 2000 ዓ. ም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሃላፊዎችን  በሰበሰቡበት ወቅት በ1997 ምርጫ ዋዜማ አካባቢ እንደነበረው የፖለቲካ ምህዳሩን ሰፋ የማድረግ ሁኔታ ሁለተኛ እንደማይደገም በይፋ ተናግረዋል፡፡ ለዚህም ነው በአሁኑ ጊዜ የሃገሪቱ የፖለቲካ አየር ታፍኖ የሚገኘው፡፡ ይህን አፋኝ የሆነ የፖለቲካ አየር ሊገፈፍ የሚችልበትን ሁኔታ በማመቻቸት ረገድ በተቃዋሚነት የተሰለፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች በትብብር መስራታቸው አስፈላጊ ነው፡፡

እስከ ዛሬይቱ ኢትዮጵያ ድረስ ህዝቡን እንወክላለን ብለው የተቋቋሙ የፖለቲካ ሃይሎች ከንጉሳዊ ስርአቱ ጀምሮ እስከ ደርግ እና በተለይም ከደርግ በኂላ የተቋቋሙ የፖለቲካ ድርጅቶች ተቃውሞን ከመግለፅ በስተቀር አማራጫቸውን ዘርዘር ባለ ሁኔታ ለህዝብ ሲያቀርቡ አልታዩም፡፡ ቅንጅት ይህን ድክመት በማረም አመለካከቱን በምርጫ ማኒፌስቶው አማካይነት ዘርዘር አድርጐ በማቅረቡ እና በተጨባጭ ለገዥው ፓርቲ የአስተሳሰብ እና የፖሊሲ አማራጮች ይዞ ብቅ በማለቱ ከሚያዚያ 30/1997 በፊት በኢትዮጵያ ታይቶ የማይታወቅ የእልፍ አእላፍ ህዝብ የፖለቲካ ድጋፍ ለመቀስቀስ ችሎ ነበር፡፡ በውል ላስተዋለው ሰው ለቅንጅት የተቸረው ህዝባዊ ድጋፍ ምስጢር ብዙም የተወሳሰበ አልነበረም፡፡ ተቃዋሚዎች ተባበሩ የሚለውን የህዝብ ምኞት በይፋ ሲገለጽ እና በስውር ሲናፈስ የነበረ የቆየ ጥያቄ ቅንጅት ለማሟላት በመሞከሩ ነበር፡፡ ከግንቦት 1997 ምርጫ በፊት በተናጠል ይንቀሳቀሱ የነበሩት አራት ድርጅቶች ማለትም መኢአድ፣ ኢድአፓ፣መድህን ቀስተዳመናና ኢድሊ የየራሳቸውን ድርጅታዊ አመራር፣ የየራሳቸውን ፓርቲ ይዘው፣ በምርጫ እርስ በርስ ላለመወዳደር ተስማምተው በጋራ በተቀበሉት የቅንጅት የምርጫ ማኒፌስቶ አማካይነት በአንድ ስያሜ እና በአንድ የምርጫ ምልክት ስር በአንድነት ለምርጫ ውድድር መቅረባቸው ህዝቡ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዲተባበሩ የነበረውን ከፍተኛ ፍላጎት ያሟላ ነበር፡፡ ህዝቡም ፍላጎቱን እንዳሟሉለት ሲያይ ከዚያ ቀድም ለማንም ሰጥቶት የማያውቀውን እጅግ ከፍተኛ ድጋፍ ሰጠ፡፡

እዚህ ላይ ከተነሳንበት የዚህ ጽሁፍ አላማ ጋር በቅርብ የተገናኙ በመሆናቸው በውል ሊጤኑ የሚገባቸው ሁለት ቁም ነገሮችን ማንሳት ያስፈልጋል፡፡ እነሱም 1ኛው ቅንጅትን ተባብረው የመሰረቱት አራቱ የፖለቲካ ድርጅቶች ያከናወኑት ድርጅታዊ ተግባር እና 2ኛ የፖለቲካ አመለካከታቸውን አንድ ወጥ ለማድረግ የወሰዱት እርምጃ  ነው፡፡ ቅንጅትን የመሰረቱት አራቱ የፖለቲካ ድርጅቶች የየግል ድርጅታዊ ፕሮግራማቸውን ሲገመግሙ አራቱም በምክክር ከተስማሙበት የጋራ የምርጫ ማኒፌስቶ ጋር የይዘት ልዩነት እንደሌለው ተገነዘቡ፡፡ የየራሳቸውን ፕረግራም ወደ ጎን በመተው የቅንጅትን የምርጫ ማኒፌስቶ የራሳችን ነው በማለት በቅንጅት ማኒፌስቶ ለመመራት ወሰኑ፡፡የወሰኑበትም ምክንያት በተለያየ አጋጣሚ ቀደም ሲል ለየብቻቸው የተደራጁ ቢሆንም፣በሂደት በጋራ ውይይት አካሂደው የተስማሙበት የቅንጅት ዓላማ እና ቅንጅት የሚመራበት ርእዮተአለም የእያንዳንዳችንን ድርጅቶች የፖለቲካ አመለካከት በሚገባ የሚገልጽ እና የሚያሟላ ነው ከሚል እምነት ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ቅንጅቱ የተመሰረተው በመለስተኛ ፕሮግራም ላይ ሳይሆን ዋንኛ ፕሮግራማቸውን አጥፈው በአንድ ወጥ ፕሮግራም ለመመራት በወሰኑ አራት የህብረ-ብሄር የፖለቲካ ድርጅቶች ነበር፡፡ ለምርጫም የቀረቡትም ድርጅታዊ ውህደት ባይፈፅሙም አንድ የተዋሃደ ፓርቲ እንደሚያደርገው በአንድ የፖለቲካ ፕላትፎርም በአንድ ስያሜ እና በአንድ የምርጫ ምልክት ስር ነበር፡፡

በአንጻሩ ከግንቦት 1997 ምርጫ በፊት በነበሩት ጥቂት ወራት የቅንጅት እና  የህብረትን ግንኙነት ብንመለከት ሁኔታው የቅንጅት አራቱ አባል ድርጅቶች ተከትለውት ከነበረው አካሄድ የተለየ  ነበር፡፡ የቅንጅት የምርጫ ማኒፌስቶ በሕወሀት/ኢህአዴግ አቀነባባሪነት የተዘጋጀውን ህገመንግስት እንዲሻሻል የሚጠይቅ ነበር፡፡ በህብረት ስር የተካተቱት አብኮ እና ደቡብ ህብረት ልክ እንደ ኢህአዴግ በክልል ብሄረተኝነት ዙሪያ መደራጀትን የፖለቲካ ዓላማ ያደረጉ እንደመሆናቸው በአፈጻጸም ደረጃ ከኢህአዴግ ጋር የማይስማሙባቸው ጉዳዮች ቢኖሩም፣ የህገ መንግስቱ ዋና ዋና አከራካሪ አስተሳሰቦች እንዲቀየሩ አይፈልጉም፡፡ ከቅንጅትም ጋር በአንዳንድ የምርጫ ዝግጅት ቅደመ ሁኔታዎች ላይ በጋራ የሚሰሩባቸው ሁኔታዎች ነበሩ፡፡ ከህብረቱ አባል የሚሰሩባቸው ሁኔታዎች ነበሩ፡፡ ከህብረቱ አባል ድርጅቶች ክልላዊ አደረጃጀት አንፃር ወደ ምርጫ ክልል ክፍፍል ያመራ የጋራ ግንባር ስምምነት አልነበራቸውም፡፡ በ1997  የምርጫ  ዋዜማ ቅንጅት እና ህብረትን ያጠጋጋቸው ምርጫው ፍትሃዊ እንዲሆን ኢህአዴግን ወደ ድርድር ለማምጣት የነበራቸው ፍላጐት ነው፡፡ ይህ አይነት ትብብር በረዥሙ ጊዜ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ውስብስብ ሁኔታዎችን በሚገባ ያላገናዘበ፣ በታክቲክ ደረጃ ላይ ብቻ ያተኮረ ጠበብ ያለ አመለካከት ነበር፡፡ ትብብሩም ዘላቂነት ሊኖረው ያልቻለው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ያም ሁኖ በወቅቱ መሥርተውት የነበረው የግንኙነት አይነት በተወሰኑ ጉዳዩች ዙሪያ (functional relationship) እንጅ መዋቅራዊ ግንኙነት (structural relationship) አልነበረም፡፡

በአሁኑ ተጨባጭ ሁኔታ የፖለቲካ ስብስቦች ስልጣን መያዝን በተመለከተ የሚያራምዱት አመለካከት ኢህአዴግን ከመጣል ያለፈ እይታ ሊኖረው ይገባል፡፡ እይታው የኢትዮጵያን ህዝብ አንድነት እየሸረሸረ በመሄድ ላይ የሚገኘውን የፖለቲካ ዘይቤ ከስረ  መሰረቱ በመቀየር ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል፡፡ በየጊዜው እንዲመሠረት የሚፈለገው የፖለቲካ ድርጅቶች ውህደት፣ ግንባርም ሆነ ጥምረት ከዚህ ስትራቴጂያዊ እና መሠረታዊ እይታ አንፃር መመዘን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ እይታ አንጻር አንድነት ፓርቲ እና መድረክን የፈጠሩት የፖለቲካ ድርጅቶች በመለስተኛ ፕሮግራም የሚቋጭ የጋራ ግንባር ሊመሰርቱ ይችላሉ ወይ የሚለው ጥያቄ  በተገቢ ሁኔታ  ሊዳሰስ የሚገባው ነው፡፡ የመድረክ እና የአንድነት ፓርቲን የግንኙነት ሁኔታ ለመተለም ስንፈልግ ከዚህ ቀደም በቅንጅት ውስጥ ከተፈጠረው የፖለቲካ ድርጅቶች ትብብር ጋር ሊነጻጸር የማይችል መሆኑ ከግንዛቤ ውስጥ መግባት ይኖርበታል፡፡

በቅንጅት ውስጥ ታቅፈው የነበሩት አራቱም ድርጅቶች በአንድ ወጥ ርእዮተዓለማዊ አመለካከት ድርጅቶቻቸውን ለማዋሃድ የተነሱ ነበሩ። በፖለቲካ ፕሮግራም አለመጣጣም ምክንያት ውህደት መፍጠር ባይቻል፣ በመለስተኛ ፕሮግራም ላይ ህብረት/ግንባር መፍጠር አይቻልም ወይ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችል ይሆናል። ይህም የማይቻል ከሆነ የማይቻልበት ሁኔታ መብራራት ይኖርበታል። ውህደትም ህብረት/ግንባርም ካልተቻለ አንድነት ከመድረክ ጋር በምን ሁኔታ አብሮ ሊሰራ ይችላል የሚለው ጥያቄ ደግሞ ደረጃውን ጠብቆ በሶስተኛ ጥያቄነት ሊነሳ እና ምላሽ ሊያገኝ ይገባል። መድረክ እና አንድነት በጋራ መለስተኛ የፖለቲካ ፕሮግራም ሊቀርጹ አይችሉም የሚል ድምዳሜ ላይ ቢደረስ፣ ከመለስተኛ ፕሮግራም ውጭ በሚያግባቧቸው ጥያቄዎች ዙሪያ በጥምረት በመስራት ሊተባበሩ ይችላሉ፤ ይገባልም። አንድነት ከመድረክ ጋር እስከ ምን ደረጃ ድረስ ሊተባበር ይችላል? አንድነት ከመድረክ ጋር በጋራ በሚስማሙባቸው የፖለቲካ ጉዳዩች ዙሪያ ጥረታቸውን ቢያቀናጁ ሁለቱም ተጠቃሚ ሊሆኑ አይችሉም ወይ? የዚህ ጽሁፍ አላማ በእነዚህ ጥያቄዎች ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ርእስ ጉዳዩችን በመዳሰስ ውይይትን ለመጫር የሚያገለግሉ የመነሻ ሃሳቦችን ለማቅረብ አልሞ የተነሳ ነው።

ጽሁፉ አምስት ንዑስ ክፍሎችን የያዘ ነው። የመጀመሪያው እና በመግቢያነት የሚያገለግለው የጽሁፉ ዓላማ የተገለፀበት ነው። ሁለተኛው ንዑስ ክፍል እስከ 1997 ድረስ የነበረውን የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች አሰላለፍ በተመለከተ ዋና ዋና ተብለው ከቀረቡ አቋሞቻቸው ጋር በማነጻጸር ለመገምገም ጥረት የተደረገበት ነው። ሶስተኛው ንዑስ ክፍል ከ1997 ምርጫ በኂላ እና እስካሁኑ ወቅት ድረስ ያለውን የፖለቲካ ፓርቲዎች አሰላለፍ ለመገምገም የተሞከርበት ነው። አራተኛው ንዑስ ክፍል የዚህ ጽሁፍ ዋንኛ ቁምነገር የሆነውን ከአንድነት የፖለቲካ ዓላማ፣ ተልእኮ እና ስትራቴጂ አንፃር የውህደት፣ የግንባር እና የጥምረት ግንኙነትን ከምክክር መድረኩ የፖለቲካ አካሄድ ጋር በማገናዘብ የሚዳስስ ነው። አምስተኛው እና የዚህ ጽሁፍ የመጨረሻው ንዑስ ክፍል የመድረክን በጋራ የመስራት ጥሪ በተመለከተ የአንድነት ፓርቲ አቋም ምን ሊሆን ይገባል፣ ግንኙነቱ በተጨባጭ የትኛውን ዓይነት መልክ/ደረጃ ሊይዝ ይገባል፣ አብሮ መስራት ሲባል ምን ማለት ነው? የተሰኙትን አስተሳሰቦች በመቃኘት በመደምደሚያነት ያቀረበበት ንዑስ ክፍል ነው። በተለየ ሁኔታ በእዝል መልክ በመጨረሻ ላይ የቀረበው አነስተኛ መግለጫ የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ ከምን ታሪካዊ እና ገቢራዊ ክንውን ተነስቶ ይህን ፅሁፍ እንዳቀረበ የገለፀበት ክፍል ነው።

## 2. በኢትዮጵያ የወቅቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች አሰላለፍ

በኢትዮጵያ ታሪክ ከዘመነ መሳፍንት በኂላ የአገር አንድነት እና የዘመናዊነት ግንባታ ጥረት የተጀመረው በአጼ ቴዎድሮስ ሲሆን፣ ይህ ጥረት በተለይም በአጼ ምኒሊክ ዘመነ መንግሥት እንዲስፋፋ እና እንዲዳብር ሲደረግ፣ በአጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግስት ደግሞ ጥረቱ ይበልጥ ተጠናክሯል።ዘመናዊ ትምህርት በሃገራችን መስፋፋት የጀመረው በአጼ ሃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት እንደመሆኑ፣ የሃገራችን ልሂቃን መብራከት እና ስለሃገራቸው ራእይ መሰነቅ የጀመሩት ከ1950ዎቹ አመታት መጀመሪያ አንስቶ እንደነበር ይታወቃል። ራእያቸውን ወደ ተግባር ለመተርጎም ያደረጉት የመጀመሪያ ሙከራ በ1953 የተደረገው በወንድማማቾቹ በጀነራል መንግሥቱ እና ግርማሜ ነዋይ የተመራው የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ነበር።

ለ1953ቱ መፈንቅለ መንግሥት ድጋፍ በመስጠት በቀድሞው የቀዳማዊ ሃይለሥላሴ በዛሬው በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የተጠነሰሰው የኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ውስጥ ተበራክተው ለሚገኙ ልዩ ልዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች መፈልፈያ ቦታ ነበር ቢባል የተጋነነ አይሆንም። በ1960ዎቹ የመጀመሪያ አመታት ጀምሮ በኢትዮጵያ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች እንቅስቃሴ እየጎለበተ፣ በወቅቱ አጠራር የጸረ-ፊውዳል እና ጸረ-ኢምፔርያሊስት የትግል ሰንደቅ ማውለብለብ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በተማሪው እንቅስቃሴ ውስጥ ሁለት የፖለቲካ አዝማሚያዎች ብቅ ማለታቸው ይታወሳል።

ከ1950ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ አንስቶ በአሜሪካ እና በአውሮፓ በሚገኙ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት በኂላም በቀ/ኃ/ዩኒቨርስቲ ውስጥ በነበረው የተማሪዎች ማህበር በይፋ ይራመድ የነበረው የግራ ርእዮተዓለም፣ ከዲሞክራሲያዊ እና ለዘብተኛ አመለካከት ተነጥሎ መስበክ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ተማሪዎች በኂላም ልሂቃን /Elites/ የፖለቲካ አካሄድ በሁለት የመከፈል አዝማሚያ እንደተጠናወተው አይዘነጋም።

አንደኛው አዝማሚያ ለኢትዮጵያ ተሃድሶ የሚደረገውን ትግል በሃገረአቀፍ ጥላ ስር አካቶ፣ ከመገንጠል በመለስ በኢትዮጵያ ያሉ ብሄረሰቦች እኩልነት የሚጠበቅበት ቀመር ከኢትዮጵያ ብሄረተኝነት (Ethiopian Supra Ethnic Naitonalism) ጋር ተጣጥሞ ሊተለም ይገባዋል የሚል አመለካከት የሚያጠነጥነው የፖለቲካ አዝማሚያ ነው። ሁለተኛው አዝማሚያ ደግሞ በክልላዊ ብሄረተኝነት (Ethnic Nationalism) ዙሪያ

የተደራጁ፣ ቀደም ሲል በኤርትራ በኋላም በኦሮሞ እና በትግራይ አንዳንድ አካባቢዎች የተጀመሩትን እንቅስቃሴዎች የሚደግፈው የፖለቲካ አዝማሚያ ነበር። ይህ የፖለቲካ አዝማሚያ ከሰብዓዊ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊን ጨምሮ ማህበራዊ መብቶች አለመረጋገጥ ይልቅ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ዋንኛ ቅራኔ በብሄረሰቦች መካከል ያለው ቅራኔ ነው የሚል ቅኝት ሲያራምድ የቆየ እና አሁንም ከግለሰብ መብት ይልቅ ለብሄረሰብ መብት (ወይም ለወል መብት) ቅድሚያ ሊሰጥ ይገባል በሚል አመለካከት ዙሪያ የሚያቀነቅን ነው።

በወቅቱ በስልጣን ለይ የነበረው የቀዳማዊ ኃይለሥላሤ መንግስት በተፈጥሮው በዘውዳዊ የፖለቲካ ምእክልና (Absolute Monarchy) ላይ የተመሠረተ፣ ከዘመናዊ የፖለቲካ ዲሞክራሲ ባህሪያት ጋረ የማይተዋወቅ ስለነበር፣ የመንግስት ተቃዋሚ በመሆን ሊደራጁ የቻሉ የፖለቲካ ድርጅቶች በይፋ ሊቋቋሙ የቻሉት ከሃገር ውጭ በአውሮፓ እና በአሜሪካ በኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ በበርሃ ነበር።

በዘመናዊ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ድባብ ውስጥ ከ1966 ህዝባዊ ኣብዮት በፊት የነበሩት የፖለቲካ ድርጅቶች የኤርትራ ነጻ አውጭ ግንባር እና ሻእቢያ፣ መኢሶን እና ኢህአፓ፣ ከኣብዮቱ በኋላ በደርግ የመንግስትነት ጊዜ የተፈጠሩት ኦነግ እና ህወሃት/ ኢህአዴግ፣ የወዝሊግ፣ ማልሪድ፣ ኢጭአት እና ሰደድ በኋላም እራሱ ኢሠፓ እንደ ቀደም ተከተላቸው በክልላዊ ብሄረተኝነት እና በኢትዮጵያ ብሄረተኝነት የፖለቲካ መስመሮች ዙሪያ የተከፈሉ ነበሩ።

መኢሶን እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በነሐሴ 1960 በጀርመን ከተማ ሃምቡርግ ላይ ሲመሠረት፣ ኢህአፓ ደግሞ ከሶስት አመት በኋላ ጥንስሱ በሶቭየቶች አቀነባባሪነት ሞስኮ ላይ ተጥሎ ፓርቲው ግን በይፋ እንደተቋቋመ የተገለፀው በምስራቅ ጀርመን በርሊን ከተማ በ1963 ነበር። የትግራይ እና የኦሮሞ ክልላዊ ብሄረተኝነት የፖለቲካ ንቅናቄዎች ርእዩተዓለማዊ መሠረታቸውን ያገኙት ህብረብሄራዊ እና ሶሽያሊስታዊ ይዘት ይዘው በተነሱት የግራ ፓርቲዎች በነበሩት በኢህአፓ እና በመኢሶን አማካይነት መሆኑን በኢትዮጵያ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ የነበረው ሁሉ የሚያውቀው ነው። በኢህአፓ እና በመኢሶን መሪነታቸው የሚታወቁት ብርሃነ መስቀል ረዳ* እና ሃይሌ ፊዳ ያራምዱ ከነበረው የግራ ርእዩተዓለም ጋር በማስታከክ የሌንናዊ ስታሊናዊ አስተምህሮ ትሩፋት የሆነውን የብሄር/ብሄረሰብ ጥያቄ እና ከኢትዮጵያ ታሪካዊ ግንዛቤ እና ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የማይሄደውን የመገንጠል እና መገነጣጠል ፖለቲካ በተማሪው ንቅናቄ ውስጥ በመጫር እና በማራመድ ጉልህ ሚና የተጫወቱ ነበሩ። ብርሃነ መስቀል ረዳ እና ሃይሌ ፊዳ በፖለቲካ ድርጅት መሪነታቸው እና እንቅስቃሴው ውስጥ ጉልህ ሚና በመጫወታቸው ተጠቀሱ እንጅ፣ የኢትዮጵያን ህዝብ ፍላጐት ባላገናዘበ መልኩ የግራ ርእዩተዓለም በኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር ላይ እንዲንሠራፋ በማድረግና ይህም ድርጊት በሃገር ላይ ለደረሰው ጉዳት የዚህን ፅሁፍ አቅራቢ ጨምሮ፣ በተራማጁ እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ የነበረው ቀለም ቀመሱ የሀገራችን የህብረተሰብ ክፍል ከታሪክ ተጠያቂነት አያመልጥም።

1985 ዓ.ም በሽግግር መንግሥቱ ዘመን ኢህአዴግ የህገ መንግሥት ማስረቀቅ ሂደቱን በጀመረበት ጊዜ በ"መድረክ" መፅሄት፣ ቅፅ 1 ቁጥር 1 ላይ **"የብሄሮች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ፅንሰሃሳብና አባሪ ችግሮች"** በሚል ርእስ በወጣው ጥናታዊ ጽሁፍ የመገንጠልን መብት እንዲያካትት የታሰበው የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ፅንሰሃሳብ ተብራርቶ ቀርቧል። ይህን ፅንሰሃሳብ መሠረት አድርጐ በወቅቱ በህገ መንግሥቱ ውስጥ እንዲካተት የታሰበው እና በኋላም የተካተተው የብሄር ፌደራሊዝም (Ethnic Federalism) መንግሥታዊ አወቃቀር ስነስርዓት ላለው ህገ-መንግሥታዊ ተፈፃሚነት አመችነት የሌለው፣ በኤርትራ ሁኔታ እንደታየው ተግባራዊነቱ ከህገመንግሥታዊ ሂደት ውጪ ሊገለፅ የሚችል፣ ከሌሎች ሶሽያሊስት አገሮች ልምድ እንደታየውም በኤርትራ ብቻ ሊገታ የማይችል አፍራሽ መርህ በመሆኑ ለኢትዮጵያ አይበጅም የሚል አመለካከት አራምዷል። በግንቦት ወር 1985 አዲስ አበባ ውስጥ በተካሄደው የኢትዮጵያ ህገመንግሥት ዝግጅት ሲምፖዚየም ላይ ተጋባዥ ከነበሩት እና ጥናታዊ ፅሁፍ ካቀረቡት የውጭ ምሁራን መካከል አሜሪካዊው ፕሮፌሰር አለን ቡካነን የመገንጠል መብትን በማስመልከት **"አንድ አገር የሚበተን አይደለም፤ መበተንም የለበትም የሚል እምነት ካለ፣ ያአገር ሊበተን የሚችልበትን ደንብ ማውጣቱ አስፈላጊ አይደለም"** (Buchanan 1991) ሲሉ ማስገንዘባቸውን በማጣቀስ የፌድራል አድያማቱም (Federal units) የአከላለስል መስፈርት ቋንቋ/ብሄር ብቻ መሆን አይገባውም የሚል ሃሳብ ከአማራጩ ጋር አቅርቧል።

---------------------

* ኢህአፓ እንደ ድርጅት የ"ኤርትራን የቅኝ ግዛትነት ቴዎሪ" እንደተቀበለ የሚያሳይ ይፋ ያደረገው ሰነድ የለም። የዚህ "ቴዎሪ" ቀደምት አራማጅ፣ የኢህአፓ ዋንኛ "አይዲዎሎግ"፣ የድርጅቱ የወታደራዊ ክንፍ አዛዥ እና የፖለቲካ ቢሮው አባል ብርሃነ መስቀል ረዳ ነበር። የኢህአፓ ሊቀመንበር ተስፋዬ ደበሳይም የዚሁ "ቴዎሪ" አራማጅ ነበር።

በ1986 በወጣው የ'መድረክ' መፅሄት ሁለተኛ እትም አማካይነት ደግሞ የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ በብዕር ስም **"ዘመናዊ ህገመንግሥት በኢትዮጵያ ከየት ወደ የት? አንዳንድ የትኩረት ነጥቦች"** በሚል ርእስ ባቀረበው ጥናታዊ ፅሁፍ በወቅቱ መረቀቁ ተጀምሮ የነበረው የአሁኑ የሃገሪቱ ህገመንግሥት በምን መልኩ ሊዘጋጅ ይገባል? መካተት የሚጠበቅባቸው እና የማይጠበቅባቸው ቁምነገሮች የቶቹ ናቸው? የሚሉ አስተሳሰቦችን በማንሳት፣ በዝግጅቱ ሂደት ሊኖር ይገባል ብሎ ያመነበትን ህዝባዊ ውይይት ለማበረታታት እና ለማገዝ የሚረዱ አስተሳሰቦችን በወቅቱ ሰንዝሯል። በዚያ ፅሁፍ አማካይነት ህገ-መንግሥቱ የህዝብ ፍላጐት የሚንፀባረቅበት እንጅ የተወሰነ የፖለቲካ ፓርቲዎች በተለይ ደግሞ የኢህአዴግ አመለካከት ማህተም ሁኖ መቀረፅ አይገባውም ብሎ ተከራክሯል። የመንግሥት አወቃቀር ጉዳይ፣ የመከላከያ፣ የፖሊስና የፀጥታ ሃይሎች ታማኝነት ለመስተዳደሩና ለፖለቲካ ፓርቲዎች ሳይሆን ለህገመንግሥቱ መሆኑ ሊረጋገጥ ስለሚችልበት ሁኔታ፣ የግለሰብ መብት እና የወል መብትን በተመለከተ፣ ነፃ የምርጫ አስፈፃሚ አካል መኖርን በተመለከተ፣ የንብረት ባለቤትነት ጉዳይን በተመለከተ፣ ልማትን የማፋጠኑ ፍላጐት ከልማት ጥረቱ ዲሞክራሲያዊነት ጋር ተገናዝቦ መቀረብ ማስፈለጉን በተመለከተ፣ የሲቪል ህብረተሰብን መጠናከር በተመለከተ፣ በዚያን ጊዜ እየተዘጋጀ በነበረው ህገ መንግሥት ውስጥ የሚቀረፁበት ሁኔታ የሕዝቡን ፍላጐት እና ስሜት ባገናዘበ መልኩ እንጅ የአሸናፊ ፓርቲው አመለካከት ማህተም ሁኖ መቀረፁ ትክክል አይሆንም በሚል አመለካከቱን አቅርቧል።

የዚሁ የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል ፖለቲካ ሌላው ትሩፋት የስርዓተ-ፅሕፈት መለያየት ጉዳይ ነው። በኢህአዴግ የሽግግር መንግሥትነት የመጀመሪያ ዓመታት በአንዳንድ መፅሔቶች ላይ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ተፃራሪ አመለካከቶችን የሚያንፀባርቁ ፅሁፎች ወጥተው ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜ ኦሮምኛ ቋንቋን በላቲን ፊደል መጻፍን ያስተዋወቀው የመኢሶኑ መስራች ሃይሌ ፊዳ ሲሆን፣ በምእራብ ጀርመን እያለ "ሂርማታ አፋን ኦሮሞ" በሚል ርእስ በላቲን ፊደል ያዘጋጀውን የኦሮምኛ ሰዋስው መጽሃፍ አትሞ ያወጣው እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጣር በ1965 ዓ. ም. ነው። ይህም የሆነው በምእራብ ጀርመን ሃምቡርግ ከተማ በሃምቡርግ ዩኒቨርስቲ የአፍሪካ ምርምር ተቋም ውስጥ የሃሚትክ ቋንቋዎች አስተማሪ በነበረበት ጊዜ ነው።* ከ16ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ጉልህ ሚና ሲጫወት ለቆየው፣ ከበርካታ ሌሎች የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ጋር በመቀላቀል ለኢትዮጵያ ህዝብ መቀራረብ ከፍተኛ ድርሻ ያለው የኦሮሞ ብሄረሰብ፣ ሌሎቹ አጋሮቹ የሆኑት የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ከሚጠቀሙበት በብቸኛ አፍሪካዊ ቅርስነቱ መላ አፍሪካዊያን ከሚኮሩበት የኢትዮፒክ (የግእዝ) ፊደል ይልቅ በብሄረሰቡ ልሂቃን የላቲን ፊደል ተመርጧል። ምርጫው የተደረገው በህወሃት/ኢህአዴግ የሽግግር መንግሥትነት ዘመን ሲሆን በኦነግ ተወካዮች አቅራቢነት እና በህወሃት/ኢህአዴግ አቀነባባሪነት ነው።

ይህ ክንዋኔ የራሱ መነሻ ታሪክ ያለው ነው። በአጼ ሃይለሥላሤ ዘመነ መንግስት ከሜጫ እና ቱለማ ማህበር በተጨማሪ የኦሮሞ ኤሊቱ እንቅስቃሴ ሲካሄድ የነበረው በወለጋ አካባቢ በሚሲዮን ት/ቤቶች አማካይነት ነበር። "በነዚህ ሚሲዮኖች አማካይነት፣ አማራ እና ትግሬ ይጨቁናችኋል፣ ኦሮሞ በታሪኩ በባህሉ ከነዚህ "ከአበሾቹ" የተለየ ነው፤ ራሱን ችሎ ነጻ መውጣት አለበት" የሚለው ሃሳብ እንዲሰርጽ ተደረገ ። የሚሲዮን ት/ቤት ውጤት የሆኑ የኦሮሞ ኤሊቶች የታሪክ አመለካከት፡- **የአበሾች ጭቆና የቆመው ወይም የሚተላለፍበት መንገድ አራት ዘርፍ ያለው ነው። እነሱም ሀ/ ቋንቋ ለ/ ኦርቶዶክስ ክርስትና ሐ/ የግእዝ ፊደል መ/ ዘውድ ናቸው በሚል አመለካከት ዙሪያ የተዋቀረ ነበር። በመሆኑም ቋንቋን በተመለከተ በራስ ቋንቋ ብቻ መናገር፣ የራስ ቋንቋ ማዳበር። ኦርቶዶክስ ክርስትናን በተመለከተ በፕሮቴስታንት እምነት መተካት። የግእዝ ወይም የኢትዮፒክ ፊደልን በተመለከተ በላቲን ፊደል እንዲተካ ማድረግ፤ ዘውድን በተመለከተ ከሌሎች የኢትዮጵያ ዘውዳዊ መንግስት ተቀናቃኞች ጋር በማበር ፊት ለፊት በመዋጋት ማስወገድ** የሚሉ አመለካከቶችን የሚያራምድ ሁኖ የተጠነሰሰ ነው። በንጉሡ ዘመን በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ ይህ የፖለቲካ አዝማሚያ በዚህ በቀረበበት መልኩ ሳይሆን በማሌ አስተምህሮ ተጠቅልሎ እና ተሸፍኖ ነበር የቀረበው። በንጉሡ ስርዓት የተማሪው እንቅስቃሴ ለኢትዮጵያ ብሄረሰቦች እኩልነት መከበር የነበረውን ቀና አመለካከት በመጠቀም፣

------------------

*ሃይሌ የመጀመሪያ ዲግሪውን ያገኘው በጅኦሎጂ ሲሆን፣ ባገኘበት ጊዜ እጅግ ከፍተኛ ውጤት በማምጣቱ የጂኦሎጂ ትምህርቱን በድህረምረቃ ደረጃ እንዲከታተል በንጉሰ ነገሥቱ ሥርዓት ተፈቅዶ ወደ ፈረንሳይ ሶርቦን ዩኒቨርስቲ በመንግስት ስኮላርሽፕ ተላከ። እዚያ ሲደርስ ከድንጋይ ጋር ምን አታገለኝ በማለት የጅኦሎጂ ትምርህርቱን ትቶ የሶሺዬሎጂ ትምህርት መከታተል ቀጠለ። ሃይሌ ጀርመን ሃምቡርግ ከተማ እያለ ከምትኩ ተርፋሳ ጋር በመተጋገዝ የኦሮምኛ ቋንቋን ለመጀመሪያ ጊዜ በላቲን ፊደል አዘጋጀ። ያዘጋጀውን መጽሃፍ እዛው ሃምቡርግ አሳትሞ ከህትመቱ አስር ቅጅ በሚስጥር ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ እና ለሜጫ እና ትሎማ አንዳንድ የአመራር አባላት፣ በደርግ ጊዜ ለተገደሉት የፕሮቴንስታንቱ ቤተክርስቲያን መሪ ለነበሩት ለቄስ ጉዲና ቱምሳ እንዲደርስ አስደረገ። ይህ የተደረገው በ1965 ዓ.ም ከአብዬቱ ፍንዳታ አንድ ዓመት በፊት ነበር። የኦነግ ምስረታ ከዚህ ታሪካዊ ክስተት ጋር የቅርብ ግንኙነት ያለው ነው። የብሄሮች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትን መኢሶን እንደ ድርጅት የሚደግፈው መብት ነበር። አፋን ኦሮሞን በግእዝ ፊደል ሳይሆን በላቲን ፊደል የመፃፉን ውሳኔ ግን መኢሶን እንደ ድርጅት አልተስማማበትም። የመኢሶኑ መሪ የሃይሌ ፊዳ የግል የፖለቲካ ምርጫ ነበር። ወደ በኂላ ላይ የሃይሌን ጅማሮ በማሻሻል ረገድ ጥላሁን ገምታም አስተዋፅኦ እንዳደረገ ይነገራል።

የእንቅስቃሴውን አመራረ ይዘው የነበሩ የክልል ብሄረተኞች በመሣሪያነት ተጠቀሙበት። የተማሪው እንቅስቃሴ ከላይ የተጠቀሱትን የአክሱም ስልጣኔ ቅርሶች እና የኢትዮጵያ አንድነት ተመስርቶባቸው የነበሩትን ድር እና ማጎች ጠቃሚ ጎናቸውን እንኳ እንዳያገናዝብ ተደርጎ እንደጋ ሪ ተለጎሞ በጽኑ እንዲዋጋቸው ተደረገ። ይህ አጠቃላይ አባባል ከላይ ከተራ ቁጥር (ሀ) እስከ (መ)ከተዘረዘሩት መካከል (ሀ)ን አይመለከትም። በራስ ቋንቋ መናገር ከዲሞክራሲ መብትነትም ባሻገር የተፈጥሮ መብት ነው።

ኦሮሚኛን ጨምሮ ለአንዳንድ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች የስርዓተ-ጽህፈት የላቲኑ ፊደል የተመረጠው ከላይ እንደተጠቀሰው ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ተጠንቶ፣ ሕዝብ መክሮበት እና ወስኖበት ሳይሆን፣ የአሸናፊ ሃይሎች የፖለቲካ ውሳኔ ሁኖ ነው። ይህ እርምጃ የተወሰደው በተለይ የኦሮሞው ኤሊቶች የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል የሚለውን አመለካከት መንደርደሪያ በማድረግ ልዩነትን አጉልቶ ለማውጣት የተጠቀሙት አካሄድ ነው። ይህ የስርዓተ ጽሁፍ አመራረጥ ጉዳይ በአሁኑ ጊዜ ለምን ይነሳል የሚሉ ተችዎችም ሊኖሩ ይችላሉ። በፖለቲካ ድርጅቶች መካከል በውህደት፣ በህብረት/ግንባር ወይም በጥምረት/ትብብር ለመስራት እንቅስቃሴ ተጀምሯል። ከሶስቱ የትብብር ዓይነቶች በአንዱ ለመስራት ሲፈለግ በቅድሚያ ይህን ዓይነት ግንኙነት በሚፈልጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች/ስብስቦች መካከል ያሉት ርእዩተዓለማዊ፣ፖለቲካዊ/ድርጅታዊ ኢኰኖሚያዊ እና ማህበራዊ የፍልስፍና እና የአመለካከት ልዩነቶች በዝርዝር ተነቅሰው መውጣት ይኖርባቸዋል። በመጀመሪያ ልዩነትን ማወቅ፣ የሚታረቅ እና የማይታረቅ መሆኑን መለየት፣ የሚቻለውን ማስማማት የማይታረቀውን አውቆ ተቻችሎ እና ተከባብሮ ለመቀጠል የሚቻልበትን አካሄድ መፈለጉ ነው ዘላቂነት ሊኖረው የሚችለው። "አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ" የተሰኘው ተረት እውን እንዳይሆን ከተፈለገ፣ስለፖለቲካ ድርጅቶች ተቀራርቦ መስራት ሲወሳ ልዩነት ያለባቸው ጉዳዬች ሁሉ ሳይድበሰበሱ ተዘርዝረው መውጣት፣ በየዘርፍ ዘርፋቸው መመደብ በኂላ ሊነሱ የሚችሉ አለመግባባቶችን በቅድሚያ አስተካክሎ ለመጓዝ ይረዳል ከሚል እምነት ነው የስዓተ ጽሁፉን አመራረጥ ጉዳይ በዚህ አጋጣሚ ለመዳሰስ የተፈለገው። በዚህ ጉዳይ ላይ በዚህ ጽሁፍ ወደ ዝርዝር መግባቱ አስፈላጊ አይደለም። በስርዓተ ጽሁፍ አመራረጥ ዙሪያ ቀደም ሲል ጀምሮ ሲካሂድ የነበረውን ክርክር በሌላ ጽሁፍ ለመዳሰስ ይሞከራል። ይህን ርእስ ጉዳይ ለመዘጋት ስለስርዓተ ጽሁፍ ምርምር ያካሂዱ ኢትዮጵያዊ ምሁር በጥናታዊ ጽሁፋቸው ላይ ያሰፈሩትን አባባል መጥቀሱ የሚያስፈልግ ይመስላል።

*አማርኛንና ኦሮምኛን ብንወስድ በአማርኛ ውስጥ ከሚገኙት 27 ተነባቢ ጽምፆች ውስጥ 23ቱ በኦሮምኛም ይገኛሉ። እንደዚሁም ከ24ቱ የኦሮምኛ ተነሳቢዎች 23ቱ በአማርኛ ያሉ ናቸው። ይህ ዓይነት ተቀራራቢነት በቋንቋዎች መካከል ካለ አንደኛው ቋንቋ በሚፃፍበት ፊደል ሌላውን መፃፍ ይቻላል።*

ከዚህ ሀቅ በመነሳት ነው የኦሮሞው ተወላጅ ኦናሲሞስ ነሲብ በግምት ከ120 ዓመታት በፊት መጽሃፍ ቅዱስን ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮፒክ (ግዕዝ) ፊደል በመጠቀም ከላቲን ቋንቋ ወደ ኦሮምኛ ቋንቋ የተረጎመው። ኦነሲሞስ ኢሉባቡሩ ተወልዶ ኤርትራ ያደገ ነው። እንግሊዝ የባሪያ ንግድን ህገወጥ ካደረገች በኂላ ኦነሲሞስ በባሪያ ፈንጋዮች ተጠልፎ ወደ አውሮፓ በመርከብ ሲላክ፣ የእንግሊዝ የባህር ሃይል በአጋጣሚ እሱ የተጫነበትን መርከብ ይዞ ኦነሲሞስን ከሌሎች ተፈንጋዬች ጋር ነፃ በማውጣት ምጽዋ አጠገብ ሞንኩሉ የምትባል ቦታ ጥሎት ይሄዳል። በዚያ ባለ የካቶሊክ ሚሲዮን ጠለላ ተሰጥቶት ያድጋል። በኂላ ከሞንኩሉ ከረን ይሄድና እዚያ ከካቶሎክ ሚስዮናውያን ዘንድ ይማራል። በኂላም ከከረን ወደ ስዊድን ተልኮ በቲዎሎጅ ትምህርት በከፍተኛ ደረጃ ይመረቅና ሰባኪ ቄስ ይሆናል።

ኦነሲሞስ ነሲብ መጽሃፍ ቅዱስን ከላቲን ቋንቋ ወደ ኦሮምኛ ቋንቋ የተረጐመው ከከረን ክሪሽና (ስዊዘርላንድ) ድረስ በመመላለስ ባዘጋጀው የኦርምኛ ቋንቋ የስፔሊንግ መጽሃፍ በመጠቀም እና አስቴር ከተሰኘች ሌላ የኦሮሞ ተወላጅ ጋር በመተባበር ነው። ኦነሲሞስ ነሲብ ከቴዎሎጂ ምሁርነቱ በተጨማሪ ላቲንን፣ ትግሪኛን የስዊድን እና ኦሮሚኛ ቋንቋዎችን በሚገባ ጠንቅቆ የሚያውቅ የቋንቋ ምሁር ነበር። የኦሮምኛ ቋንቋን ለመጻፍ በኦሮምኛ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ድምጾችን የላቲኑ ፊደል በሚገባ ይወክላቸዋል ብሎ ቢያምን ኑሮ ፊደሉን ከላቲን ወደ ግእዝ ወይም ኢትዮፒክ ፊደል መለወጡ ባላስፈለገው ነበር። በነገራችን ላይ ኦነሲሞስ ነሲብ ከኦሮምኛና ከትግርኛ ውጪ አማርኛ መናገር እንደማይችል አንዳንድ ምንጮች ይጠቁማሉ። በመድረክ ዙሪያ ከተሰባሰቡት የፖለቲካ ድርጅቶች እና ተዋቂ ግለሰቦች መሃከል አብዛኞቹ የተወሰኑ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ስርዓተ ጽህፈት ከኢትዮፒክ (ግእዝ) ወደ ላቲን ስርዓተ ጽህፈት መለወጡን ደግፈውታል። በአሁኑ ጊዜ በዚህ ጉዳይ ላይ ያላቸው አቋም መለወጥ ወይም አለመለወጡን በተመለከተ ማብራሪያ ሊሰጡበት ይገባል። በአገራችን ባሉ ብሄረሰቦች መካከል ከሚገኙ ተጨባጭ ቋንቋ ነክ ልዩነቶች በተጨማሪ የሕዝብን አመኔታ ባላገኘ፣ ከቋንቋዎች መስፋፋትና እድገት አንጻር ጠቃሚነቱ በተጨባጭ መረጃ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ልዩነትን ለማበራከት ሲባል የተወሰደ የፖለቲካ እርምጃ ጊዜ እየቆጠረ ሲሄድ ወደ ተጨባጭ ልዩነት የማደጉ ሁኔታ እውን ሊሆን ይችላል። ይህ ደግሞ ወደፊት በሕዝብ አንድነት እና በአገር ሉዓላዊነት ላይ አደጋ የመጋረጥ ስጋት ሊኖረው ይችላል።

በተለይ ደግሞ ኢትዮጵያ ሃገራችን በቅርቡ ከፈራረሱት ከሶቭየት፣ ከቸኰዝሎቫኪያ እና ከዩጉዝላቭ የብሄር ፌደሬሽኖች መቅሰም

የሚገባትን ልምድ በጥሞና ማገናዘቡ በእጅጉ አስፈላጊ ነው። ሌኒን ከታላቁ የጥቅምት ሶሺያሊስት አብዮት በፊት የሩሲያ ግዛቶችን አስመልክቶ ቋንቋ ወይንም ብሄርን ብቸኛ መሠረት አድርጐ የውስጥ ድንበርን በማካለል የብሄሮች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል የተሰኘውን ፅንሰ ሃሳብ በሶቭየት ህብረት መቀመሩ ይታወቃል። ይህንንም እውን የሚያረግበትን ህገ መንግሥት ከአብዮቱ በኋላ በ1922-23 በሶቭየት ኮምኒስት ፓርቲ ድርጅታዊ ስራ አማካይነት እንዲፀድቅ ሲያደርግ ሁለት እሳቤዎች ነበሩት። 1ኛ/ ቋንቋን እና ብሄርን መሰረት በማድረግ የተካለሉት ሪፓብሊኮች እና ራስ ገዝ ክልሎች በሶቭየት ህገመንግሥት ውስጥ የመገንጠል መብት እንዲሰፍር በመደረጉ የህብረታቸው መሠረት አብሮ ለመኖር ያላቸው ፍላጐት ብቻ መሆኑን ስለሚያምኑ፣ በፈለጉበት ጊዜ የመገንጠል መብት እንዳላቸው ስለሚገነዘቡ በተግባር የመገንጠልን አደጋ ለመከላከል ይቻላል 2ኛ/ ለብሄሮች የመገንጠል መብት እውቅና መስጠት ብሄሮች የብሄረተኝነት ጥማታቸውን ሙሉ በሙሉ ለማርካት የሚችሉበት ደረጃ ላይ ስለሚያደርሳቸው፣ በሂደትም የሪፓብሊኮቹ የኢኰኖሚ እድገት እንዲመጣጠን እና እንዲቀራረብ ስለሚደረግ ይህ ሂደት አዲስ ወደሆነ ወደላቀ ህብረተሰብ፣ ማለትም ከሶቭየት ህዝቦች ወደ ሶቭየት ሕዝብነት የሚደረገውን ሽግግር እውን ያደርጋል የሚል ነበር። የሌኒን የመጀመሪያው ሃሳብ በቋንቋ እና ብሄር መመዘኛነት የተዋቀረው የሶቭየት የብሄር ፌደራሊዝም የተለያዩ የሶቭየት ብሄሮችን የብሄራዊ ስሜት ጥማታቸውን እንዲያረኩ የማድረጉ ጉዳይ ሙሉ በሙሉ ግቡን መቷል። በሶሺያሊስት የብሄር ፌደራሊዝም የሌኒናዊ - ስታሊናዊ ቀመር የብሄር ስሜት ጥማቸውን ካረኩ በኋላ ወደ አንድ ወጥ የሶቭየት ሕዝብነት ይለወጣሉ በሚል ፈሊጥ የተቀመረው የሌኒናዊ - ስታሊናዊ የብሄር ፌደራሊዝም ቀመር እንዳልሠራ እና ሶቭየት ህብረት ወደ 15 ነፃ ሪፓብሊኰች እንደተበተነች ይታወቃል። የዩጐዝላቪያ እና የቸኰዝላቫኪያም ሁኔታ ከሶቭየት ህብረት ጋር ተመሳሳይ ነው።

የዩጐዝላቪያ ዳር ድንበር ከፀደቀበት እና የዩጐዝላቭ ሶሺያሊስታዊ ፌደሬሽን ከተመሠረተበት ከ1926 ጀምሮ በፌደሬሽኑ ውስጥ ሰርቢያ እና ክሮኤሺያ ለበላይነት ይፎካከሩ ነበር። ሰርቢያ እና ክሮኤሽያ ሁለቱም የአንድ ዓይነት ቋንቋ ተናጋሪ እና የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ሲሆኑ፣ ልዩነታቸው ሰርቢያ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ክሮኤሺያ ደግሞ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ተከታይ መሆናቸው፣ ሰርቢያ በኦቶማን ቱርክ ስርዎ መንግሥት ክሮኤሺያ ደግሞ በኦስትሮ ሃንጋሪ ስርዎ መንግሥት ስር መቆየታቸው ነው። አሁን እንደሚታወቀው የዩጐዝላቪያ ፌደሬሽን ፈርሶ በምትኩ ስድስት ነፃ ሃገሮች ተመስርተዋል።

ከ1924 ጀምሮ ሶቭየት ህብረት ወደ 15 ነፃ ሪፓብሊኰች እስከ ተበተነበት እስከ 1992 ድረስ ሶቭየት ህብረት አንድ ሃገር ሁና ለ70 አመታት ሳይፈርስ የቆየበት ዓይነተኛ ምክንያት ነበረው። ይኸውም በብሄር ፌደራሊዝም መርሆዎች ተዋቅሮ ለነበረው የሶቭየት ህብረት መንግሥት ሁለንተናዊ አመራር ይሰጥ የነበረው በመላ ሶቭየት ህብረት ግዛት ማለትም በአስራ አምስቱም ሶቭየት ሪፓብሊኰች ጭምር በአሃዳዊነት መርሆዎች ተደራጅቶ የነበረው ቦልሸቪኩ የሶቭየት ህብረት ኰምኒስት ፓርቲ (The CPSU (B)) ነበር። "የሶቭየት ህብረት ኰምኒስት ፓርቲ የሶቭየት መንግሥት መሪ ሃይል ነው፤" የሚለው ሕገመንግሥታዊ የማሰሪያ አንቀፅ በጐርባቾቭ የተሃድሶ ፖለቲካ አማካይነት ከሕገመንግሥቱ እንዲወጣ እስከተደረገበት ጊዜ ድረስ ለ70 ዓመታት ያህል የሶቭየት ህብረት ፌደራላዊ መንግሥት ፖለቲካውን ጨምሮ ሁለንተናዊ አመራር ያገኝ የነበረው ከሶቭየት ኰምኒስት ፓርቲ ነበር። (አስፋው ቦጋለ 1985፡ 37-45)

ከሶቭየት ህብረት የብሄር ፌደራሊዝም የሚቀሰመው ልምድ በትኩረት ሊጠና የሚገባው ነው። ከምስራቁ አስተምህሮ የተቀዳው የብሄር ፌደራሊዝም ለተወሰነም ጊዜ ቢሆን መበታተንን ሳይያስከትል ሊቀጥል የሚችለው በአንድ ፓርቲ ወይም የፖለቲካ ድርጅት ፍፁማዊ የፖለቲካ የበላይነት እና አመራር የተደገፈ እንደሆነ ብቻ ነው። በዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴው ግፊት ይህ ዓይነቱ አምባገነናዊ የፖለቲካ አገዛዝ ሲቀር ወይም እንዲለወጥ ሲደረግ፣ የመበታተን አዝማሚያን ገድቦ የሚይዝ ሃይል ስለማይኖር የመበታተን አደጋ ሊያጋጥም እንደሚችል ታይቷል። የሶቭየት ህብረት ብቻ ሳይሆን የዩጐዝላቢያም ሆነ የቼኰዝሎቫኪያ ልምድ  ይህን አባባል ይበልጥ የሚያጠናክር ነው። በሃገራችን በአሁኑ ጊዜ ያለውም ሁኔታ ከተጠቀሱት አገሮች ሁኔታ ጋር የቀረበ ተመሳሳይነት ያለው ነው። በአሁኑ ወቅት በሃገራችን ባለው የክልል ብሄረተኝነትን መሠረት ባደረገ ፌደራላዊ አወቃቀር መሠረት በዘጠኙም ክልላዊ መስተዳድሮች በስተጀርባ ሁኖ መላ እንቅስቃሴያቸውን የሚቆጣጠረው ኢህአዴግ ነው።

ፖለቲካቸውን በክልል ብሄረተኝነት ዙሪያ ያደራጁ የፖለቲካ ፓርቲዎች የኢትዮጵያ አንድነት እና ሉዓላዊነት መከበርን በተመለከተ አጠራጣሪ አቋም እንደሌላቸው ይህ ፀሐፊ ይገነዘባል። በክልል ብሄረተኝነት ዙሪያ መደራጀታቸው በኢትዮጵያ ብሄረተኝነት ዙሪያ ከተደራጁት ያነሰ ኢትዮጵያዊ እንደማያደርጋቸውም ያምናል። ይሁንና ሃገራዊ አደረጃጀትን በሚመርጡት በኩል ያለው ዋንኛ ስጋት ዲማክራሲያዊ የፖለቲካ አመለካከት እና አሠራር ስር ባልሰደደባቸው፣ ብዙ ብሄረሰቦች በሚገኙባቸው በሃውርታዊ (multinational) በሆኑ የአፍሪካ አገሮች (ኢትዮጵያንም ጨምሮ)፣ ከክልል ብሄረተኝነት ሃገራዊ አደረጃጀትን በሚመርጡት በኩል ያለው ዋንኛ ስጋት ዲማክራሲያዊ የፖለቲካ አመለካከት እና አሠራር ስር ባልሰደደባቸው፣ ብዙ ብሄረሰቦች በሚገኙባቸው በሃውርታዊ (multinational) በሆኑ የአፍሪካ አገሮች (ኢትዮጵያንም ጨምሮ)፣ ከክልል ብሄረተኝነት የሚመነጨው መንግሥትን በቋንቋና / ብሄረሰብ መስፈርቶች ብቻ የማደራጀቱ ቤተሙከራ  በአንድ አገር ዜጐች መካከል ልዩነቶችን፣ ከፋፋይ እና

ጠባብ አመለካከቶችን በማጉላት ለፖለቲካ መረጋጋት ጠንቅ ይሆናል የሚል ነው። የክልል ብሄረተኝነትን መሠረት በማድረግ የሚፈጠሩ መንግሥታዊ የፌድራል አድያማት በቆዳ ስፋታቸው ወይም ጥበታቸው፣ በያዙት ህዝብ እና የተፈጥሮ ሃብት ክምችት ብዛት፣ ሊለያዩ ስለሚችሉ፣ ጠበብ ላለ የፖለቲካ ስልጣን ጥያቄ ሲባል ፖለቲከኞች ወይም ቡድኖች የአድያሙን (ክልላዊ-መንግሥቱን) ህዝብ በተለያየ መልክ በመቀስቀስ እና ለጠባብ ዓላማ በማሰለፍ ከአጐራባች ብሄረሰብ/ብሄረሰቦች ጋር እንዲጋጭ እና የእርስ በእርስ ፍጅት እንዲፈጠር ያደርጋል። ከሃገራችን ጂኦፖለቲካ እና ታሪካዊ ውርስ አንፃር ይህ ዓይነት ፖለቲካ ኢትዮጵያ እንድትከፋፈልና እንድትዳከም ለሚፈልጉ የአካባቢና የሩቅ የውጭ ሃይሎች በር ይከፍታል የሚል ብርቱ ስጋት አለ። ይህ ከፖለቲካ እንደምታው አንፃር ያለ ስጋት ነው።

ከኢኰኖሚ እንደምታው አንፃር ሲታይም ቋንቋ/ብሄረሰብን ብቸኛ መመዘኛ ያደረገ ፌደራላዊ አወቃቀር ችግሮች አሉበት። "የክልላዊ መንግሥቱ የተፈጥሮ ሃብት ለክልሉ ህዝብ"* የተሰኘውን መፈክር የክልል ብሄረተኞች በብዙ የአፍሪካ አገሮች እያነሱ የህዝብን ሰላማዊ ኑሮ የሚያውኩበት፣ ይባስ ብለውም በዚህ ሳቢያ የሚነሳው አለመግባባት ወደ እርስ በርስ ጦርነት እንዲያመራ የሚያደርጉበት መፈክር ሁኖ እንደቆየ ይታወቃል። በናይጀሪያ በቢያፍራ የዘይት ሃብት አጠቃቀም ዙሪያ 1960-1963 የተካሄደው የመገንጠል እንቅስቃሴና በዚህም ምክንያት የተካሄደው የርስ በርስ ጦርነት ብዙ ሺህ ህዝብ ከጨረሰ እና ሃገሪቱንም የመገነጣጠል አፋፍ ላይ ካደረሳት በኋላ ነው ሊገታ የቻለው። የጦርነቱ አንዱ ዓይነተኛ ምክንያት በብሔራዊ ክልሉ በተገኘው የነዳጅ ሀብት የክልሉ ሕዝብ ይበልጥ ተጠቃሚ ሊሆን ይገባል የሚል ነበር።

ናይጀሪያ በእንግሊዝ የቅኝ አገዛዝ አስተዳደር ስር በነበረችበት ጊዜ (እንደ አ. አቆጣጠር ከ1954 በፊት) በሶስት ክፍለ ግዛቶች ማለት የእስላምና እምነት ተከታይ በሆነው የሰሜኑ ሃውሳ-ፋላኒ ብሄረሰብ ግዛት፣ የክርስትና እምነት ተከታይ በሆነው የደቡብ ምስራቁ የኢቦ ብሄረሰብ ክፍለ ግዛት እና ምእራባዊ ክፍለ ግዛት በመባል በሚታወቀው እና እስልምና እና ክርስትናን በሚከተለው የያሩባ ብሄረሰብ ክፍለ ግዛት የተከፈለች ነበረች። እነዚህ ሶስቱ ክፍለ ግዛቶች በህዝብ ቁጥር እና በመሬት ስፋታቸው፣ በያዙት ሃብት መጠን ያልተመጣጠኑ ነበሩ። ይህ መሠረታዊ ያለመመጣጠን ያስከተለው ችግር ከነፃነት በኋላ በኢቦ ብሄረሰብ በተነሳው የመገንጠል እንቅስቃሴ ግልፅ በመወጣቱ የናይጀሪያ ፌደራል አወቃቀር መጀመሪያ ወደ 12 በኋላም ወደ ሰላሣ ስድስት ተመጣጣኝ ወደ ሆኑ እና የብሄር ስም ወደ አልተሰጣቸው ፌደራላዊ መስተዳድሮች ሊለወጥ በቅቷል። (Turten 2006:6-8) ይህ የናይጀሪያ ፌደራላዊ አወቃቀር ከህገ መንግሥታዊ ውጭ የተካሄዱ ሁለት ሶስት ወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥቶችን እንዲሁም በምርጫ ስልጣን ላይ የወጡ የሲቪል አስተዳደሮችን በማፈራረቅ በአንፃራዊነት ረዘም ላለ ጊዜ የቆዩ ብቸኛ ከአፍሪካ ምድር የበቀለ የፌደራሊዝም ልምድ ጠቃሚ ትምህርት ሊገኝበት ይችላል።

አቶ ገብሩ አስራት <u>በኢትዮጵያ የፌድራል መንግሥታዊ ስርዓት አወቃቀር ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች</u> በተሰኘ ጥናትዊ ፅሁፋቸው ውስጥ *"በብሄር ብሄረሰብ ላይ የተመሠረተ ፌደራሊዝምን መከተል አለመከተልን በሚመለከት የሚራመዱ ደጋፊና ተቃዋሚ ሐሳቦች ቢኖሩም በአሁኑ ጊዜ በብሄር ብሄረሰቦች ላይ የተመሠረተ የፌድራል ስርዓት በዓላማችን እየተለመደ እንደመጣ ግምት ውስጥ ማስገባት ጠቃሚ ይሆናል። እንደነ ስዊዘርላንድ፣ ካናዳ፣ ቢልጅየም የመሳሰሉ የምእራብ አገሮች ብሄር ብሄረሰብ ላይ የተመሠረተ የፌድራል ስርዓት እየተከተሉ ነው። ከደቡብ ዓላማችን ክፍልም ህንድና** ናይጀሪያ ተመሳሳይ መንገድ ተከትለዋል"* በማለት ፅፈዋል። (ገብሩ አስራት 2001:7-8) ይሁንና አቶ ገብሩ በጠቀሱት መፅሀፍ ውስጥ ስለምእራብ አገሮች በሃውርታዊ ፌደራሊዝም ልምድ በሳል ፅሁፍ ያቀረቡት ዊል ካያሚልካ በፅሁፋቸው መጨረሻ ላይ የኢትዮጵያ የብሄር ፌደራሊዝም ከተሳካው የምእራብ አገሮች በሃውርታዊ ፌደራሊዝም ልምድ አንፃር እንዴት እንደሚታይ ሲያጠቃልል የሚከተለውን አስፍሯል።

> "እርግጥ በአንዳንድ የምእራብ አገሮች የበሃውርታዊ ፌደራሊዝም (Multi-nation federalism) የተሣካ ውጤት አስመዝግቧል። እነዚህ አገሮች በሃውርታዊ ፌደራሊዝም በፈቃዳቸው እና በሰላማዊ መንገድ ሊተገብሩ የቻሉባቸው ቅድም ሁኔታዎች ግን በኢትዮጵያ ውስጥ የሉም። ስለዚህ በኢትዮጵያ ውስጥ እየተተገበረ ያለው ክልላዊ ፌደራሊዝም (ethnic Federalism) በቀላሉ ሊሰባበር (Fragil) የሚችል ቤተሙከራ እንደሆነ አድርጐ መውሰድ ይቻለል።" (Kymlicka 2004:58)

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለረዥም ጊዜ በአሃዳዊ ብሄረ-መንግሥት የምስረታ እና የግንባታ ሂደት ያለፉ አንዳንድ የምእራብ አገሮች (ከናዳ፣ ቤልጅየም፣ ስፔን፣ ወዘተ...) የበሃውርታዊ ፌደራልዝም (Multinational Federalism) የመንግሥት አደረጃጀት መርሆዎች መከተል ጀምረዋል።

---------------------

* በሃገራችንም ኦብነግ በኦጋዴን የሚገኘው የነዳጅ ሃብት የኢትዮጵያ ሳይሆን የሱማሌ ክልል ህዝብ የብቻ ሃብት ነው በሚል የውጪ የነዳጅ ፈላጊ ኩባንያዎች ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር መደራደሩ ዋጋ እንደሌለው አስጠንቀቆ እንደነበረ ሚያዝያ 6/2001 የወጣው መሰናዘሪ ጋዜጣ (ገፅ 3) አትቶበታል።

** በ1950 በፀደቀው የህንድ ሕገመንግሥት የተዋቀረው ፌደራለዊ መንግሥት ለአሰራር በሚያመቹ ፌደራላዊ አድያማት የተከፋፈለ እና ለፌድራል መንግሥቱ በርከት ያለ ስልጣን የሰጠ ነበር። በ1966 ህንድ ቋንቋን መሠረት ባደረጉ የፌድራል አድያማት ልትከፍለ በቅታለች። በዚህ መልኩ የህንድ ፌደራሊዝም አሁን ካለው የኢትዮጵያ ፌደራሊዝም ጋር የሚቀራረብ ቢሆንም የህንድ ህገ-መንግሥት የመገንጠልን መብት አይፈቅድም። የህንድ በቋንቋ ላይ የተመሠረተ ፌደራሊዝም ሊሰመር የቻለው እንደ ምእራብ አውሮፓ ሃገሮች በዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ ልምድ ላይ የተገነባ በመሆኑ ነው። (ተርተን 2006:10)

ይህንን አዲስ ክስተት እንደምሳሌ በመጥቀስ የኢህአዴግን በቋንቋ/ብሄረሰብ ላይ የተመሠረተ የብሄረሰብ ፌደራሊዝም በመርህም ሆነ በተግባር ሊደገፍ ይገባል የሚል አመለካከት ነው በመድረክ ውስጥ የተሰባሰቡ የክልል የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚያራምዱት፡፡ ይሁንና የአንዳንድ ምእራብ አገሮች የበሃውርታዊ ፌደራሊዝም መንግሥታዊ አወቃቀር ልምድ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ የአፍሪካ አገሮች ቃል በቃል ሊገለበጥ የሚችልበት ሁኔታ እንደሌለ "Ethnic Federalism – The Ethiopian Experience in Comparative Perspective"* በተሰኘው መፅሃፍ ውስጥ ጥናታዊ ፅሁፎቻቸውን ያካተቱት ዲቪድ ተርተን እና ዊል ኪያሚልካ አስገንዝበዋል፡፡

ኪያሚልካ የምእራቡ ዓለም የበሃውርታዊ ፌደራሊዝም ልምድ በአፍሪካ ውስጥ ብርቱ ተቃውሞ የቀሰቀሰበትን ሁኔታ በሚከተለው አኳሃን አብራርቶታል፡፡ እነዚህን በአፍሪካ የሌሉ በምእራቡ ዓለም ግን የተለመዱ ቅድመ ሁኔታዎች በተመለከተ ተርተንም ሆነ ኪያሚልካ ተንተን አርገው አቅርበቸዋዋል፡፡

> በብዙ የአፍሪካ አገሮች በሃውርታዊ ፌደራሊዝም ጠንካራ ተቃውሞ እየገጠመው ነው፡፡ በምእራቡ ዓለም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተተገበረ ያለው በሃውርታዊ ፌደራሊዝም (Multinational Federalism) በአንድ ብሄር መንግሥት (Nation-state) ስር ለተነሱ "ተፎካካሪ ብሄረተኝነቶች" (competing nationalsims) ምላሽ የሰጠ አካሂድ ነው፡፡ … በአፍሪካ የተከሰቱ የብሄረሰብ ግጭቶች በአብዛኛው ከተፎካካሪ ብሄረተኝነት የመነጩ አይደሉም፡፡ ከተፎካካሪ ብሄረተኝነት ጋር ሊመሳሰሉ በሚችሉባቸው (እንደ ኢትዮጵያ) ባሉ የአፍሪካ አገሮችም ቢሆን፣ የበሃውርታዊ ፌደራሊዝም ልምድ መፍትሄ ይሆናል ለማለት ያስቸግራል፡፡ በምእራብ አገሮች ላጋጠማቸው ችግር የተጠቀሙበት  የበሃውርታዊ ፌደራሊዝም አግባብ መፍትሄ ሊሆን የቻለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች በአፍሪካ ውስጥ የሉም፡፡ (Turton & Kymlicka 2006: 1-58)

1. ስር የሰደደ የዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ አሠራር ባህል መኖር፣ የፖለቲካ ጥያቄን በሰላማዊ አግባብ እና በድርድር የማስፈፀም ባህል መኖር ሃገራዊም ሆነ ክልላዊ እይታ ያላቸው ፖለቲከኞች ምሁራን የለዘብተኛ ዲሞክራሲ ፖለቲካ ባህል ወራሽ እና ተጋሪ መሆን፣

2. ከብሄረሰብ መብት ጋር የተያያዙ ጥያቄዎች በዲሞክራሲያዊ አግባብ በነፃ እና ፍትሃዊ ምርጫ እንጅ በሀይል እና በጠመንጃ አለማስተናገድ፣

3. ረዘም ላለ ጊዜ በተግባር በተፈተነ የለዘብተኛ ዲሞክራሲ ህገ መንግሥት አማካይነት የግለሰብ መብት ሙሉ በሙሉ የተከበረበት ሁኔታ መኖር፣ በማናቸውም ጊዜ የግለሰብ ሰብዓዊ፣ ፖለቲካዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ሊጣሱ ይችላሉ የሚል ስጋት የተወገደ መሆን፣

4. ኢኮኖሚ ብልፅግና እና ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል የሰፈነበት ሁኔታ መኖር፣

5. እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች አንድ የህብረተሰብ ክፍል ወይም ብሄረሰብ በሌላው ማህበረሰብ ላይ የበላይነቱን ሊጭን የሚችልባቸውን ሁኔታዎች መሠረት ያሳጡ እና እንዳይፈፀም የሚከላከሉ መሆናቸው፣

6. የብሄረሰብ መብት የሚያቀነቅኑ የፖለቲካ ሃይሎች አሁን በምእራቡ ዓለም ባለው ተጨባጭ የፖለቲካ ሁኔታ የሃገር ደህንነት ስጋት ለሚፈጥሩ አጐራባች አገሮች ወይም የአካባቢ ወታደራዊ ትብብሮች (Political — Military Blocks) የውስጥ አርበኛ ወይም መሣሪያ ሊሆኑ የሚችሉበት ሁኔታ ሙሉ በሙሉ የተወገደ መሆኑ የተሰኙ ናቸው፡፡ (kymlicka 2006: 42-44)

በአንፃሩ በኢትዮጵያ የብሄረሰብ ፌደራሊዝም መተግበር የተጀመረው በህዝብ ፍላጐት እና ምርጫ ሳይሆን ደርግን በሃይል አስወግዶ ስልጣን በያዘው በኢህአዴግ ተፅእኖ ነው፡፡ ዲቪድ ተርተን የወቅቱን የኢትዮጵያ ፌደራሊዝም መለያ ምልክቶች ሲያብራራ (ተርተን 2006፡5)

1ኛ/ በኢትዮጵያ የፌደራላዊ የራስ ገዝነት ደረጃ ያገኙት ክልሎች ይህን መብት ያገኙት የየክልሉ ህዝብ ባነሳው ጥያቄ መሠረት ሳይሆን በኢህአዴግ ችሮታ እና ባደራጃቸው ግንባሮች ተባባሪነት መሆኑ፣

2ኛ/ በእያንዳንዱ ክልል ያለው ዋንኛ ብሄረሰብ በክልሉ ባሉ ሌሎች በሄረሰቦች ላይ ሙሉ የበላይነት እንደኖረው መደረጉ እና የሌሎች ማህበረሰቦች መብት ህገመንግሥታዊ ድጋፍ አለማግኘቱ፣

-------------------------

* ይህ ፅሁፍ የቀረበው"Ethnic Federalism – The Ethiopian Experience in Comparative Perspective" በተሰኘ መፅሃፍ ውስጥ ነው፡፡ መፅሀፉ በዚህ ርእስ ላይ በ1998 በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በተዘጋጀ ሲሚናር ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ፅሁፎችን ያካተተ እና የአርትኦት ሥራው በዲቪድ ተርተን ተደርጐ የታተመ መፅሀፍ ነው፡፡ ለሴሚናሩ የገንዘብ እርዳታ ያደረገው በአዲስ አበባ የሚገኘው በእንግሊዝ ካውንስል ሲሆን፣ ሲሚናሩ ከእንግሊዝ ካውንስል በተጨማሪ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ እና በፌድራል ጉዳዩች ሚኒስትር መ/ቤት በጣምራ የተዘጋጀ ነው፡፡ በሲሚናሩ በተጠቀሰው ርእስ ዙሪያ የተዘጋጁ በጣም በሳል እና ትምህርት የሚገበይባቸው ጥናታዊ ፅሁፎች ቀርበዋል፡፡ የቀረቡት ፅሁፎች ተጠቃለው ርእሱ ከላይ በተጠቀሰው መፅሃፍ መልክ ተዘጋጅተው ቀርበዋል፡፡

3ኛ/ እያንዳንዱ በዚህ መልክ የተዋቀረ ክልላዊ መንግሥት መጠሪያ በክልሉ ውስጥ ሙሉ የበላይነት በተሰጠው ብሄረሰብ ስም እንዲጠራ መደረጉ እንደሆኑ አስምሮበታል።

ይህ ዓይነቱን የኢትዮጵያ ፌደራሊዝምን ነው ኪ.ያሚልካ "ከፍተኛ ስጋትን ያዘለ አካሄድ" (Kymilica 2006: 51) በማለት ያስቀመጠው።

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ፌደራላዊ የመንግሥት አወቃቀር አግባብነት ያለው ነው። የፌድራሉ አድያማት የሚካለሉበትን መስፈርት፣ በተመለከተ ቋንቋ/ ብሄረሰብ ዓይነተኛ መመዘኛ መሆኑ ቢታመንበትም፣ ብቸኛ መመዘኛ መሆኑ ግን በአንድነት ሃይሎች ዘንድ ተቀባይነት የለውም። የቅንጅትም ሆነ የአንድነት ፕሮግራም ይህን አቋም ቁልጭ አድርገው የሚያሳዩ ናቸው። ለፌደራል አድያማት የሚሰጠው ስያሜም በግድ ከብሄረሰብ ስያሜ ጋር እንዲቆራኝ መደረጉም አግባባብነት የለውም። በአጭሩ በሀገራችን ለፌድራል አድያማት አከላለል የሚመረጡ መስፈርቶች ከምስራቁም ሆነ ከምእራቡ ዓለም እንዳሉ ሊገለበጡ አይገባም። የፌደራላዊ ጽንሰ ሃሳብ ዋንኛ ገጽታ የሆነው አካባቢያዊ ራስ ገዝነት ለኢትዮጵያ አዲስ ክስተት አይደለም። ከኢትዮጵያ አዒያዊ ማእከላዊ መንግሥት እኩል የቆየ ታሪክ ያለው ነው። የቆዬ ታሪክ የሌለው እና የጣሊያንን ወረራ ዱካ ተከትሎ ወደ ሃገራችን የገባው ጣሊያን ለከፋፍሎ መግዛት ፖሊሲው ዓይነተኛ መሳሪያ አርጐ ሊጠቀምበት አስቦ የተለመው የክልል ብሄረተኝነት (ethnic nationalism) ነው። በዚህ አብይ ጥያቄ ዙሪያ ሊተለም የሚገባው ፖሊሲ ከቆዬ የመንግሥታዊ ታሪካችን፣ ከህዝቡ ፍላጐት እና የፖለቲካ ባህል፣ ባጭሩ ከሃገራችን አፈር መመንጨት ይኖርበታል።

ለኢትዮጵያ መንግሥታዊ አወቃቀር የፌድራሉ ዘይቤ ተመራጭነት የሚኖረው በኢትዮጵያ ውስጥ ላለው የብሄረሰቦች ግንኙት ፍትሃዊ መደላድል ለመፍጠር ቢሆንም፣ የፌደራላዊ መንግሥታዊ አወቃቀር አስፈላጊነት በዚህ ላይ ብቻ አያቆምም። የኢትዮጵያ አንድነት ሃይሎች ዛሬም ሆነ ነገ የኤርትራ ህዝብ ኢትዮጵያዊ ነው ብለው ያምናሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ትግሬ፣ አፋር፣ ሳሆ እና አገው ኤርትራ ውስጥ ያለውን ትግሬ፣ አፋር፣ ሳሆ እና አገው በምንም መልኩ በቅኝ ተገዥነት ሊይዘው አይችልም። ይህ የጣሊያን ከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ ሰለባ የሆኑ የኤርትራ የክልል ብሄረተኞች የሚያቀነቅኑት አመለካከት ታሪካዊነትም ሃቀኝነትም የጐደለው ነው።በዚያው ልክ ህወሃት ኤርትራን በተመለከተ የሻእቢያን አቋም በመቀበል ሲያራምደው የነበረው "የብሄራዊ ቅኝ ግዛታዊ ጥያቄ" (National Colonial Question) የተሳሳተ እና ከኢትዮጵያ እውነተኛ ታሪክ ያፈነገጠ ነው።

እርግጥ በኤርትራ ውስጥ ለክልል ብሄረተኝነት መንሰራራት ዋንኛ ምክንያት ሁነው ያገለገሉት፡-

1ኛ/ በንጉሱ ስርዓት የኤርትራ የፌድራል ህገ መንግሥት ያለአግባብ መጣስ ነው። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ በወቅቱ በተቀረው ኢትዮጵያ ከኤርትራ ፌደራላዊ ስርዓት ጋር የሚመጥን የመንግሥታዊ አወቃቀር ባለመኖሩ እና እንዲኖርም ባለመፈለጉ ነው። በአንድነት ሰንደቅ ዙሪያ በተዋደቁ ልጆቿ ትግል ኤርትራ ከተቀረው ኢትዮጵያ ጋር ከተቀላቀለች በኋላ አፄ ሃይለ ሥላሤ የአንድነት ሃይሎችን በማግለልና ፀረሀአንድነት የነበሩት በማቅረብ የተጫወቱት የስልጣን ፖለቲካ ነው።

2ኛ/ በኋላም የደርግ መንግሥት ለኤርትራ ጥያቄ በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ስር የፖለቲካ መፍትሄ ለማስገኘት ይቻልባቸው የነበሩ አጋጣሚዎችን ሁሉ ባለመጠቀም፣ እስከ መጨረሻው ድረስ ጉዳዩን በሃይል ለመፍታት መሞከሩ ችግሩን ይበልጥ አባብሶት መጨረሻ ደረጃ ላይ እንዲደርስ አብቅቶታል። በደርግ ዘመን ከአንድንም ሁለት ጊዜ ወደ መንግሥት አድልቶ በነበረው የወታደራዊ ሃይል ሚዛን ሳቢያ ሻኢቢያ በኢትዮጵያ አንድነት ጥላ ስር የቀድሞውን የፌደሬሽን መብት ለመቀበል ዝግጁ ሁኖ እንደነበር ይታወቃል።* ደርግ በወቅቱ ለኤርትራ "ሪጅናል አውቶኖሚ" መብት እንጅ የፌደራል መብትን አልሰጥም ማለቱ ይታወቃል። የፌደሬሽኑን ጉዳይ ደርግ ብቻ ሳይሆን ህወሃትም በወቅቱ እንዳልደገፈው ይነገራል። በዚያን ወቅት በህወሃት ውስጥ በከፍተኛ የአመራር ቦታ ላይ የነበሩ እንደመሆናቸው ሁኔታው እውነትነት ካለው አቶ ስዬ አብርሃ እና አቶ ገብሩ አስራት በዚያ ታሪካዊ አጋጣሚ የህወሃትን አቋም ትክክለኛ ገፅታ ገሃድ ማውጣት እና አሁን ላይ ቁመው ያንን የድርጅታቸውን አቋም እንዴት እንደሚገመግሙት ማብራራት ይጠበቅባቸዋል።

-----------------------

* በወታደራዊ መልኩ በ1978 ደርግ በሻቢያ ላይ ሙሉ የበላይነት ተቀዳጅቶ እንደነበር ጀነራል መኰንኖቹ በወቅቱ በሚስጥር የሚያወሩት ጉዳይ ነበር። ፖስትፋሽ በተሰኘ የስዊዘርላንድ ከተማ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እየታተመ ይወጣ በነበረው አድማስ በተሰኚ መፅሄት በኰማንደር አበበ ሃይሌ ተዘጋጅቶ "የምዕዋ ታሪክ" በሚል ርእስ በቀረበው ፅሁፍ ውስጥ የሚከተለው አባባል ሠፍሮ ይገኛል። **"በ1978 ዓ.ም በዘመቻ ቀይ ባህርና ዘመቻ ባህረ ነጋሽ አማካይነት የኤርትራ ጦርነት መደምደሚያ ደረጃ ላይ ደርሶ እንደነበረ፣ ሳዋ ፎርቶ የተባለው ከፍተኛ የሻብያ የጦር ግምጃ ቤት ተይዞ ሻብያ ተስፋ ቆርጣ መሳሪያና ድርጅት እያቃጠለች ወደ ሱዳን ሽሽታ ነበር። "ተከታትሎ ጦርነቱን መጨረስ ሲቻል ጦርነቱ ከቆመ ግማሽ ሚሊዬን በላይ የሚሆነው ሠራዊ ምን ይደረጋል? ከሚል ስሌት የክትትል እንቅስቃሴ እንዲቆም ተረገ። ... በ1980 (ከነጀነራል ታሪኩ በሊቀመንበሩ ትእዛዝ መገደልና ከጦሩም ሞራል መላሸቅ በኋላ) ሳይታሰብ ሻዕቢያ 22ኛ ክፍለ ጦርን አፋቤት ላይ እንዳልነበረ አድርጋ መስሐሊትን ያዘች።"** (አድማስ መፅሄት፣ ህዳር 1985፣ቁጥር 6፣ ገፅ 24)

የኢህአዴግ መንግሥትም የኤርትራን እና የኢትዮጵያን ግንኙነት ከመጀመሪያው ጀምሮ ስርዓት ባለው፣ ከታሪካዊ እውነታ ባልፈነገጠ እና ከስልጣን ፖለቲካ ጋር ባልተቆራኘ፣ መርህን በተከተለ ሁኔታ ሊመራው ሲገባ ይህን አላደረገም። ኤርትራን በተመለከተ ኢህአዴግ በመጀመሪያ ላይ የተከተለው የማባበያ ፖሊሲ (Appeasment Policy)፣ ወደኋላ ደግሞ ይህን ፖሊሲ ለመቀልበስ መገደዱ በ1990-91 ለተከሰተው ጦርነት አይነተኛ ምክንያት እንደሆነ ይታመናል። በዚህ ቅድመ ሁኔታ ላይ የዋንኛው ክልላዊ ብሄረተኛ የሻእቢያ ጠብ ጫሪነት ተደምሮበት ጦርነቱ ሊጀመር በቃ። የኤርትራ እና የኢትዮጵያ ግንኙነት ለሁለቱ አገሮች ሠላም መደፍረስ እና ልማት መጓተት፣ ለቀጠናው ፀጥታ መደፍረስ ምክንያት ሆነ።

ቀድሞውንም በሁለቱ አገሮች መካከል የተደረገው ጦርነት የድንበር ግጭት ተባለ እንጅ ከመጋረጃው በስተጀርባ መሠረታዊ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ፖሊሲ ልዩነቶች እንዳሉት ይታወቃል። መሠረታዊ ችግሮቹ ሳይፈቱ የድንበር ውዝግቡ ለብቻው ሊፈታ የሚችልበት ሁኔታ ያለ አይመስልም። መሠረታዊ ምክንያቶቹ ደግሞ የመነጬት ኤርትራን ለግል ኢትዮጵያን ለጋራ ከተሰኜው የሻእቢያ ፖሊሲ እና ህወሃት/ኢህአዴግ በመጀመሪያዎቹ የስልጣን አመታቱ በነበረው የሃይል አሰላለፍ ውለታን በመመለስ መልክ ስልጣኑን ለማደላደል ለተጠቀሰው አካሄድ ድጋፉን በመለገሱ ነው። ይህ የፖለቲካ ድርጅትን ዓላማ ከሚመሩት አገርና ከወገን ጥቅም የማስቀደም አካሄድ ሕወሃት ለሁለት ከመከፈሉ በፊት የተከናወነ ነው። በወቅቱ አቶ ስዬ አብርሃ እና አቶ ገብሩ አስራት የሕወሃትም ሆነ የኢህአዴግ የፖለቲካ ቢሮ አባላት ነበሩ። ለዚያ ለተሳሳተ እና የጦርነቱ ቅድመ ሁኔታ በሆነ አካሄድ ላይ በድርጅታቸው ውስጥ በወቅቱ ተቃውሞአቸውን ስለመግለጻቸው የታወቀ ነገር የለም። የሕወሃት መከፋፈል በጦርነቱ መሠረታዊ ምክንያቶች ላይ ሳይሆን ጦርነቱ በተነሳበት ጊዜ እና ከተነሳ በኋላ በነበረው አካሄድ ላይ ብቻ ከሆነ፣ ልዩነቱን የተሟላ ልዩነት አያደርገውም። በሁለቱም በኩል የፈሰሰው ደም የወንድማማቾች ደም በመሆኑ፣ጦርነቱ ግዙፍ መስዋእትነት የጠየቀ እንደመሆኑ፣ የልዩነቱ ምክንያት እስከምን ድረስ የደረሰ እንደነበረ ለማሳወቅ ማብራሪያ መስጠት ይጠይቃል።

ለማናቸውም ይህ ጽሁፍ የኤርትራ እና የተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪካዊ ቁርኝት በሁለቱም አገሮች በስልጣን ላይ ባሉ የገዥ ፓርቲዎች የስልጣን ፖለቲካ ውሉን ስቶ መቅረት አይኖርበትም ብሎ ያምናል። ስለሆነም አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ የሁለቱም አገሮች ገዥ ፓርቲዎች ባይቀበሉትም በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን የደፈረሰ ግንኙት ለማሻሻል፣ የተቋረጠው የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት እንዲጀመር ለማድረግ፣ለጦርነት የሚደረገው ዝግጅት እንዲቆም እና የሁለቱም አገሮች ሃብት ወደ ልማት እንዲዞር በሁለቱ አገሮች መካከል የስርዓተ-መንግሥት ጥምረት (Confideration Arrangement) ሊከናወን እንዲችል ውይይት መጀመሩ በሁለቱም አገሮች ያሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሊያነሱት እና ወደ ህዝብ ጆሮ እንዲደርስ ሊያደርጉት የሚገባ ወቅታዊ የፖለቲካ አጀንዳ ነው ብሎ ያምናል።የድንበሩም ጉዳይ ሆነ የአሰብ ወደብ ጉዳይ መፍትሄ ሊያገኙ የሚችሉት በዚሁ የስርዓተ መንግሥት ጥምረት አማካይኝት ነው ብሎ ይህ ጽሁፍ ያምናል።

አሁን እንደሚታየው የተወሳሰበ ደረጃ ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያና የኤርትራ ግንኙነት በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የብሄር/ብሄረሰቦች ጥያቄ በምን ሂደት አልፎ እዚህ ሊደርስ ቻለ? የጥያቄው አነሳስ ንድፈ ሃሳባዊ አቀራረብ እንዴት ተጀመረ? አሁን ሊደርስ የቻለበት ደረጃ ላይ ሊደርስ የበቃበትን ምክንያት ሚያዝያ 1985 የወጣው የመድረክ መፅሄት በሚከተለው አኳኋን አቅርቦት ነበር።

> ከኤርትራም ሆነ ከተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ መሠረታዊ ጥቅም አንፃር እጅግ ወሳኝ የሆነውን የአንድነት እና የህብረትጥያቄ፣ የሚመለከተውን ኽዝብ ከተሳትፎ ባገለለ መልኩ ሶስት ተከታታይ መንግሥታት በቅብብሎሽ የመሰላቸውን እርምጃ በመውሰድ አሁን ያለበት ደረጃ ላይ አድርሰውታል። ከዚ ሁኔታ መረዳት የሚቻለው ቁምነገር አሁንም ሆነ ቀደም ሲል የኢትዮጵያ ችግር መሠረታዊ ምክንያት ሕዝብና ስልጣን ሊገናኙ ካለመቻላቸው የመነጨ ነው። (መድረክ፣ 1985:57)

ኢትዮጵያ የብሄር/ብሄረሰብ መብት ጥያቄ ንድፈሃሳባዊ ክርክር የተጀመረው በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ ሲሆን፣ ለብሄር ድርጅቶች መመስረት ፖለቲካዊ ግፊት የሰጡት የተማሪው እንቅስቃሴ ውጤቶች የሆኑት ኢህአፓ እና መኢሶን ናቸው የሚል አመለካከት አለ። በኢህአፓ እና በመኢሶን ውስጥ አመራሩን በመያዝ፣ አብዛኛውን ለውጥ ፈላጊ ተማሪ እንደጋሪ በመንዳት የስርነቀል ፖለቲካ ሰለባ ያደረጉት በህብረ ብሄራዊነት ካባ ተከልለው የክልል ብሄረተኝነት አቋማቸውን ሲያራምዱ የነበሩት የሁለቱ ድርጅቶች አመራሮች ነበሩ የሚሉ አሉ። ወደ የ1966 አብዬት ስንቃረብ፣ በሁለቱም ድርጅቶች ውስጥ ከክልል ብሄረተኝነታቸው ይልቅ የኢትዮጵያ ብሄረተኝነት ስሜታቸው ያየለባቸው ወገኖች ሲጠናከሩ፣ የክልላዊ ብሄረተኝነት ስሜታቸው ያየለባቸው የኢህአፓን የፖለቲካ ቅኝት መሠረት በማድረግ የትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅትን፣ ሌሎቹ ደግሞ የመኢሶንን የፖለቲካ ቅኝት መነሻ በማድረግ የኦሮሞ ነጻ አውጭ ግንባርን መሠረቱ። ኢህአፓ እና መኢሶን በተናጠል በደርግ ተመተው ከፖለቲካ ውጭ እንዲሆኑ ሲደረግ (1968-1970) አብዛኞቹ አባሎቻቸው የክልል ብሄረተኛ ድርጅቶች ወደሆኑት ወደ ህዝባዊ አርነት ትግራይ እና ወደ ኦሮሞ ነፃነት ግንባር ተቀላቀሉ። አስገራሚ በሆነ ሁኔታም ህብረብሄራዊ ለነበሩት የቀድሞ እናት ድርጅቶቻቸው ደመኛ ጠላቶች ሊሆኑ በቁ። ኢህአዴግ መጀመሪያ የአንድ በኋላም የሁለት በኋላም የሶስት በኋላም የአራት በብሄረሰብ ደረጃ የተደራጁ ድርጅቶች ግንባር ነው። በአንድ ወጥ ህብረ ብሄራዊ ድርጅት መልክ ሊደራጅ አለመቻሉ ለክልል ብሄረተኝነት ያለውን ፅኑ ታማኝነት ያመለክታል።

ከ1963 ጀምሮ እስከ 1966 አብዮት ፍንዳታ ድረስ በሰሜን አሜሪካ እና በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ESUNA እና

ESUE መጽሄቶች (ቻሌንጅ እና ታጠቅ) ላይ ይወጡ የነበሩ ጽሁፎችን ለሚያስታውስ፣ ወይም መጽሄቶቹን አገላብጦ ለተመለከተ፣ በጽሁፎቹ ውስጥ ይንጸባረቅ የነበረው የፖለቲካ ክርክር በኢትዮጵያ ብሄረተኝነት እና በክልል ብሄረተኝነት አራማጆች መካከል እንደነበር ለመገንዘብ ይችላል።

ከ1960ዎቹ መጀመሪያ ጀምሮ እስከ 1966 አብዮት ድረስ የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ፖለቲካዊ ተጽእኖ ከፍተኛ ደረጃ የደረሰበት ወቅት ነበር። በወቅቱ የተማሪውን እንቅስቃሴ ከበስተጀርባ በመሆን ሲያሽከረክሩት የነበሩት ከውስጥም ሆነ ከውጭ የእንቅስቃሴውን አመራር በውል ጨብጠው የነበሩት ስርነቀል የግራ ፖለቲከኞች በማርክሲስት ሌኒኒስት ርእዮት ሽፋን የብሄረሰብ ጥያቄን ከሁሉ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ጥያቄዎች ከፍ አድርገው እና አጡዘው አቀረቡት። ኢህአፓ እና መኢሶን አደረጃጀታቸው ሃገራዊ፣ በፕሮግራማቸው ላይ ያሰፈሩት ዓላማ ህብረብሄራዊ ሆኖ ሶሺያሊስት ኢትዮጵያን መመሥረት ነበር። የሌኒዝም - ስታሊኒዝም ትሩፋት በሆነው "የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል" የሚለው የመነጠል እና የመገነጣጠል ፖለቲካ አራማጆች ስለነበሩ፣ድርጊቱ ካለፈ በኋላ ሲገመገም በተጨባጭ ያከናወኑት ነገር በኢትዮጵያ ብሄረተኝነት ኪሣራ የክልል ብሄተኝነትን ማንገስ ነበር።

የ1966 ህዝባዊ አብዬት ከፈነዳ በኋላ ለደርግ በስልጣን ላይ መቆናጠጥ ዋንኛው ምክንያት የኢህአፓ እና የመኢሶን አለመስማማት፣ መናቆር እና ብሎም እርስበርስ መጠፋፋት ነው። ደርግ በቀዳማዊ ሃይለ ሥላሤ ዘመነ መንግሥት በዘመናዊ የጦር ሃይልነት ከተደራጀው የኢትዮጵያ ሠራዊት የተወጣጣ ነው። የዘመኑን ትምህርት በቀሰሙ የጦር አዛዦች የሚመራ እና በውትድርና ሙያ የሰለጠነ፣ በኢትዮጵያ ብሄረተኝነት ዙሪያ ተኰትኩቶ የተደራጀ ሠራዊት ነበር። ደርግ የዚህ ሠራዊት ተወካይ በመሆን ለስልጣን ሲበቃ፣ ተኰትኩቶ ባደገበት ስልጠና መሠረት የ"ኢትዮጵያ ትቅደም" ሰንደቅ አራማጅ ሆነ። የደርግ ብሄረተኝነት አክራሪ እና ጦረኛ ስለነበር አፍራሽ ጐኑ አመዘነ እንጅ "ኢትዮጵያ ትቅደም" በተሰኘ መፈክሩ ይመራ የነበረ ሃይል እንደመሆኑ፣ ለኢትዮጵያ ብሄረተኝነት የቆመ ሃይል ነበር።

ደርግ የኢህአፓን እና የመኢሶንን መሪዎች የመገንጠል እና የመገነጣጠል ንድፈሃሳብ አራማጆች፣ የሻእቢያ፣ የህወሃት እና የኦነግ የርዕዩተዓለም ነፍስ አባቶች ናቸው ብሎ ያምን ነበር። በመሆኑም ብርሃነ መስቀል ረዳን እና ሃይሌ ፊዳን ይዞ ኢሰብዓዊ እና ሕገወጥ በሆነ ሁኔታ በአንድ ቀን ረሽኖ በአንድ ጉድጓድ ውስጥ ቀበራቸው። ይህ የሆነው በ1971 ሲሆን፣ በዚህ ድርጊቱ ደርግ የክልል ብሄረተኝነትን ለአንድ ጊዜ እና ለመጨረሻ ጊዜ የቀበረ መስሎት ነበር። ሃይማኖታዊ እምነትን በሃይል ለመጨፍለቅ እንደማይቻል ሁሉ የጸና የፓለቲካ አመለካከትን በሃይል ለማስለወጥ አይቻልም። ደርግ አመለካከቱን በተቃዋሚዎቹ ላይ በሃይል ለመጫን መሞከሩ ክፉኛ እንዲሳሳት አድርጐታል።

የታሪክ ግጥምጥሞሽ (The irony of History) የሚባለው ክስተት በተለየ መልኩም ቢሆን ታሪክ ራሱን የሚደግም በመሆኑ ነው። ደርግ የክልል ብሄረተኝነትን ቀበርኩ ካለበት ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠር ልክ በ25 ዓመቱ በግንቦት 1997 ህወሃት/ኢህአዴግ የሚያራምደው የክልል ብሄረተኝነት አመለካከት፣ ውጤቱ በውል እንዳይታወቅ በተደረገ የህዝባዊ ምርጫ አማካኝነት በቅንጅት ኢትዮጵያዊ ብሄረተኝነት ክፉኛ ተንገጫገጨ። ልክ ደርግ ከሃያ አምስት አመት በፊት እንዳደረገው፣ በኢህአዴግም ጊዜ የኢትዮጵያ ብሄረተኝነትን ለአንድ ጊዜ እና ለመጨረሻ ጊዜ ለመቅበር በማሰብ ምርጫችን ይከበር ብለው ሰልፍ የወጡ ዜጐች በግፍ ተገደሉ። የቅንጅት መሪዎች ብቻ ሳይሆን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አባላቱን እና ደጋፊዎቹን ለእስር ተዳረጉ። ቅንጅትን ህጋዊ እውቅና ነሳው። ይባስ ብሎ ስሙና የምርጫ ምልክቱ ተቀምቶ ለማይገባቸው ሰዎች ተሰጠ። የፖለቲካ አመለካከትን በሃይል ለማጨናገፍ እና ለማምከን የማይቻል መሆኑን ኢህአዴግ ሩቅ ሳይሄድ እራሱ ከገለበጠው መንግሥት ልምድ መማር ነበረበት። ህዋሃት/ኢህአዴግ ቅንጅትን በማፍረስ ድርጅቱ የሚወክለውን በዲሞክራሲያዊ አግባብ እና በግለሰብ የዜግነት እኩልነት ላይ የተመሠረተውን የኢትዮጵያዊ ብሄረተኝነት ዓላማ በማጨናገፍ አመክናለሁ ብሎ መነሳቱ ግምኛ* ስህተት ላይ እንዲወድቅ አድርጐታል። አሁን በያዝነው በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን በአፍሪካ ውስጥ ካሉ ቁጥራቸው በየጊዜው እየቀነሰ በመሄድ ላይ ከሚገኙ የፖለቲካ ሃይሎች እና ከጥቂት በአምባገነናዊ የፖለቲካ ስርዓት ከሚመሩ አገሮች በስተቀር መላው ዓለም ተፃራሪ የሆኑወይም የተለያዩ የፖለቲካ አስተሳሰቦች መካከል የሚካሄደው የፖለቲካ ፍልሚያ መሳሪያ እና ሃይል በመጠቀም አይደለም። ተፃራሪ የሆኑ የፖለቲካ አመለካከቶች መፍትሄ የሚያገኙት በዲሞክራሲያዊ አግባብ ለህዝብ ነፃ ምርጫ ቀርበው በህዝብ ውሳኔ መሠረት አሸናፊው አስተሳሰብ መንግሥት የሚመራበት ዘይቤ መሆኑ በዘመናችን አጠቃላይ ተቀባይነት አግኝቷል። ከዚህ ውጭ ያለው አካሄድ ለህዝብም ለሃገርም ለራስም የሚበጅ አይደለም።

------------------

*ክፉኛ እና ግምኛ ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ቃላቶች ናቸው፣ የፊትኛው የሸዋ የኋለኛው የጐንደር አማርኛ ነው።

ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ በኋላ በኣንድ በኩል ለቁጥር የሚታክቱ በርከት ያሉ በክልል ብሄረተኝነት ዙሪያ የተደራጁ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ግንባሮች ወዘተ ... ሲኖሩ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን በኢትዮጵያ ብሄረተኝነት ላይ ያዋቀሩ የተወሰኑ ሃገረአቀፍ የፖለቲካ ድርጅቶች መኖራቸው ይታወቃል። በኢህኣዴግ የሽግግር መንግስትነት ዓመታት የነበሩትን ለቁጥር የሚታክቱ የፖለቲካ ድርጅቶች ትተን በኢህኣዴግ የቋሚ መንግስትነት ጊዜ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙትን መነሻ መሠረታቸው ብሄረሰብ/ክልል የሆነ የፖለቲካ ድርጅቶች ብንመለከት በርከት ያሉ ሁነው እናገኛቸዋለን። ኢህአዴግም ሆነ በሱ አመራር ሰጭነት የተቋቋሙት ኦፒዲኦዎች፣ ከኢህአዴግም ውጭ የተቋቋሙት ኦነግ፣ መአህድ፣ ደቡብ ህብረት፣ ኦብኮ (ኦህኮ) ኦሮሞ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ፣ የሱማሌ ዲሞክራሲያዊ አንድነት ሃይሎች፣ የኦጋዴን ነፃ አውጭ ግንባር፣ አረና ትግራይ፣ የአፋር ነጻነት ግንባር፣ የሲዳማ ህዝብ ነጻነት ግንባር፣ የሐረሬ ሊግ በመረጃ አለመገኘት ስማቸውን ለመጥቀስ ያልተቻለ ሌሎች ፓርቲዎች ናቸው። መነሻ መሠረታቸው ህብረ-ብሄራዊ አቋም እንደሆነ የሚገልጹት ኢዲህ፣ መኢአድ፣ ኢዲፓ፣ ቀስተ ዳመና ሊግ ሲሆኑ ከኢዲህ በስተቀር የተቀሩት አራቱ በ1997 ምርጫ ዋዜማ የቅንጅት አባል ድርጅቶች የነበሩት ናቸው።

ከ1997 የምርጫ ዋዜማ ቀደም ብሎ የተቋቋመው ኢዲአፓ-መኢህንና መኢአድ ጅምሩ ላይ ህብረብሄራዊ ከሆኑ ከእነኢህአፓ እና መኢሶን ጋር መሠረታቸው ብሄረሰብ ከሆነ ከነደቡብ ህብረት እና ኦብኮ ጋር የተጣመሩበት ግንባር ነበር። ይህ ግንባር የ1997 ምርጫ እየተቃረበ ሲመጣ በምርጫ መሳተፍ እና አለመሳተፍ ጥያቄ ዙሪያ ውጭ ያሉት እነ መኢሶን እነ ኢህአፓ እና ሃገር ውስጥ ካሉት የብሄረሰብ ድርጅቶች ማለትም ከኦብኮ እና ደቡብ ህብረት ጋር ሊስማሙ ባለመቻላቸው ለሁለት ተሰንጥቋል። ደቡብ ህብረት እና ኦብኮ በውጭ ካሉት ተነጥለው ህብረት በተሰኘው ጥምረት ተሰባስበዋል።

በተለይ ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ የክልል በሄረተኝነትን ከኢትዮጵያ ብሄረተኝነት በላይ ከፍ አርጎ ለማስቀመጥ ወይም ይህ በማያዋጣበት ጊዜ የአቻነት ስፍራ ለመስጠት ሲያደረግ የቆየው ጥረት በቅረጹ በኢትዮጵያ የብሄረሰብ የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል እየተባለ በህዋሃት/ኢህአዴግ ለሚራመደው ፖለቲካ ሁነኛ መፍትሄ ለመስጠት የተነሳ ቢመስልም፣ በይዘት ግን ከመቻቻል እና ከአንድነት ይልቅ መራራቅን እና ልዩነትን እያሰፋ፣ ለአገሪቱ ፖለቲካ አለመረጋጋት ዋንኛ ምክንያት መሆኑ ቀደም ሲልም የተስተዋለ አሁንም እየታዬ ያለ ሁኔታ ነው። ከዚህም የባሰው እና ለኢትዮጵያ ፖለቲካ መረጋጋት ይበልጥ ጠንቅ የሚሆነው በኦነግ እና በኦጋዴን ብሄራዊ ነፃ አውጭ ግንባር (ኦብነግ) እየተራመደ ያለው "ከቅኝ ግዛት ነፃ የመውጣት" በሚል ታሪክን ያላገናዘበ የፖለቲካ አመለካከት ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ኦነግ ይህን አመለካከቱን እያለዘበ መምጣቱ ተስፋ ሰጪ እርምጃ ነው። ይህ የብሄረሰብ ጥያቄን ሽቅብ የማጎን አካሄድ ህዝባዊ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን የ1997 ምርጫ በጉልህ ያሳየው ሃቅ ነው። ረዥሙን የኢትዮጵያ ታሪክ በውል ላስተዋለ፣ ከጥንት ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ ብሄረተኝነት ሲወከል የኖረውን የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት የማዳከም ወይም በሌላ የመተካት ሙከራ ዘላቂታዊነት ሲኖረው አልተስተዋለም።

የዘመናት የህልውና ታሪክ ያለው የኢትዮጵያ አሃዳዊ መንግስት ተመስርቶባቸው የነበሩት ሁለት ምሶሶዎች ነበሩ። አንደኛው በሃገሪቱ ወርድ እና ስፋት የነበሩትን ባላባታዊ ግዛቶች በሃይልና በዲፕሎማሲ ያዋሃዳቸው የዘውድ ምእክልና ነው። ሁለተኛው ለዚህ አገርን የማዋሃድ ሂደት የርእዮተዓለም ድጋፍ ሲሰጥ የቆየው የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ነበር። አሁን የለሙት እና ሃያላን የሚባሉት ሃገሮች ሁሉ በተመሳሳይ የጦርነት እና የዲፕሎማሲ ትግል የተመሠረቱ ናቸው። ከታሪክ ለመገንዘብ እንደሚቻለው የአውሮፓ አገሮች የብሄረ መንግስት ምስረታ ሂደታቸውን የማጠናቀቁ ሂደት በንግድ እና በአጠቃላይ በኢኮኖሚ እድገት መጠናከር፣ በማህበራዊ ለውጥ እና በስነጥበባት መስፋፋት የታገዘ ነበር ። ይህ ዓይነት የሃገር ግንባታ ሂደት ሁሉም ሃገሮች የሚጋሩት ነው። በ1966 ሕዝባዊ አብዮት አማካይነት የዘውድ ምእክልና ተወግዷል፤ መንግስትም በዓለማዊ (Secular) እንጅ በመንፈሳዊ ርእዮት የማይመራበት ሁኔታ ተረጋግጧል። በደቡብ እና በአንዳንድ የመሃል ኢትዮጵያ አካባቢዎች ለኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ እና ባህላዊ ጭቆና መሠረት የነበረው የመሬት ስሪት ስርነቀል በነበረው 1967 የመሬት አዋጅ አማካይነት ላይመለስ ተሽሯል። ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ ወዲህ ደግሞ ሁሉም የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች በቋንቋቸው እንዲገለገሉ እና ባህላቸውን እንዲያዳብሩ አመች ሁኔታ ተፈጥሯል።

ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ ከ1983 ወዲህ የትግራይ የኦሮሞ የአፋር የሱማሌ እና አንዳንድ የደቡብ ኢትዮጵያ ብሄረሰቦች በቋንቋቸው እንዲማሩ እና እንዲተዳደሩ ተደርጓል። ይህ ትክክለኛ እና የሚደገፍ እርምጃ ነው። ታሪክ አቀራርቦ ያስተሳሰራቸውን የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች አፍሪካዊ ከሆነው እና መላ አፍሪካ ከሚኰሩበት የኢትዮፒክ (ግእዝ) ፊደል ውጭ በላቲኑ ፊደል እንዲጠቀሙ መገፋፋት ግን አግባብነት ለሌለው ልዩነት ሁኔታ በማመቻቸት በሕዝቡ አንድነት ተጠብቆ መቆየት ላይ አደጋ እንዲያንዣብብ በር መክፈት ይሆናል። ከኢትዮጵያ የተገነጠለችው እና የዘመን አቆጣጠሯን ወደ ፈረንጅኛ የቀየረችው ኤርትራ እንኳ ፊደሏን አልለወጠችም። የዘመን አቆጣጠሩ ለውጥም ቢሆን አርቲፊሻል ነው። የኢትዮጵያው አዲስ ዓመት የእንቁጣጣሽ በዓል በህዝቡ ዘንድ መከበሩ አልቀረም። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከ1983 ወዲህ የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች

የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ ይህ ትክክለኛ እና የሚደገፍ እርምጃ ነው፡፡ ተደጋፊ ያልሆነው አካሄድ የሁሉም ብሄረሰቦች ተማሪዎች የጋራ መግባቢያ ቋንቋቸው የሆነውን አማርኛን በተገቢ ሁኔታ እንዲማሩ የማድረጉን መንግስታዊ ሃላፊነት መወጣት ያለመቻል ነው፡፡ መስከረም 17/2001 በወጣው አዲስ ነገር ጋዜጣ ላይ ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ አንድ ጸሐፊ የሚከተለውን ጽፏል፡፡

> ተማሪዎች ይህን የጋራ የሆነ መግባቢያ ቋንቋ እንዲማሩ ተፈላጊውን ሐላፊነት ያለመወጣት፣ ተማሪውን አንድ መገልገያ መሳሪያ ከማሳጣትም አልፎ በአገራዊ መግባባት ጉዳይ ላይም ክፍተት መፍጠሩ የማይቀር ነው፡፡ ስለአገር ኢኮኖሚ እድገት ሲታሰብ መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ የአገሪቱ አብዛኛው ህዝብ ሊግባባበት ስለሚችለው ቋንቋም ጭምር ነው፡፡

ይህ ዓይነት የጋራ የሆነን ነገር የማውገዝ እና የማንኳሰስ የክልል ብሄረተኛነት አካሄድ ሃገራዊ ብሄረተኝነትን የሚሻማበት እና የሚጋፋበት ደረጃ ላይ ማድረስን የሚጋብዝ ይሆናል፡፡ ይህ አዝማሚያ የፖለቲካ አለመረጋጋትን ያስከትላል፡፡ የፖለቲካ አለመረጋጋትን አዝሎ ኢኮኖሚ ልማት አስገኛለሁ ማለት ደግሞ ዘበት ይሆናል፡፡ የኢኮኖሚ ልማት አለመረጋገጥ ደግሞ የፖለቲካ አለመረጋጋትን ያስከትላል፡፡ ለስልጣን ሲባል ከመጠን አልፎ እንዲጦዝ በሚደረግ የጎሣ ፖለቲካ አማካይነት የሃገራችን ፖለቲካ ሊረጋጋ ባለመቻሉ፣ ከድህነት አዙሪት ቀለበት ሳንወጣ ልንቀጥል ነው ማለት ነው፡፡

በዚህ ጽሁፍ ተከታይ ክፍል እንደሚመለከተው በሃገራችን በኢትዮጵያ ባሉ የተለያዩ ብሄረሰቦች እና ማህበረሰቦች መካከል በጦርነት አማካይነትም ሆነ በሰላማዊ ሁኔታ ከፍተኛ የህዝብ ፍልሰት፣ የመደባለቅ እና የመወራረስ ሂደት ተከናውኗል፡፡ አሁን የተያዘው የብሄረሰብ ፖለቲካ ካልተለወጠ ከኢኮኖሚ እድገት የሚገኘን ጥቅም በመከፋፈል አንፃር በሚፈፀም የፖሊስም ሆነ የአፈፃፀም ችግር በሕዝብ ውስጥ የመቃቃር ስሜት ሊጠፈር ይችላል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ማህበራዊ ትርምስ እና የርስ በርስ ጦርነት ሊያመራ ይችላል፡፡ በሃገራችን በአሁኑ ወቅት በተወሰነ አካባቢ ከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት አለመገኘቱ ሊያዘናጋን አይገባም፡፡ የሃገሪቱ ዜጐች በሃገሪቱ የቆዳ ስፋት በነፃ ለመንቀሳቀስ፣ ለመስራት፣ ሃብት ለማፍራት ላፈሩት ሀብት የህግ ከለላ ለማግኘት የሚችሉበት ሁኔታ ሲመቻች፣ የሃገሪቱ ሃብት በየትኛውም ክልል ይገኝ ለሃገሪቱ ዜጐች የጋራ ጥቅም ሊውል የሚችልበት ሁኔታ ሲፈጠር ነው ሃገራዊ ልማት የሚሳካው፡፡ በአጭሩ በአንድ አገር የተፋጠነ እና የተመጣጠነ እድገት ሊኖር የሚችለው በዜግነት እኩልነት ላይ የተመሠረተ የግለሰብ መብት የሚከበርበት ሁኔታ ሲመቻች ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ለወደፊቱ የሃገር አንድነት አደጋ ላይ እንዳይወድቅ፣ ካሁኑ አካሄዳችንን እናስተካክል የሚል ነው በኢትዮጵያ ብሄረተኝነት ዙሪያ የተደራጁ ሃይሎች ለማስተላለፍ የሚፈልጉት የፖለቲካ መልእክት፡፡

የወቅቱ የኢትዮጵያ ተጨባጭ የፖለቲካ ገጽታ በጥሞና ሲታይ በዚህ ዓብይ ጥያቄ ዙሪያ ያሉት የፖለቲካ አመለካከቶች በሁለት ጎራዎች የተከፈሉ ለመሆናቸው ማስተባበል የሚቻል አይሆንም፡፡ አንዱ ጎራ በኢህአዴግ እና በዚህ ጥያቄ ዙሪያ ከኢህአዴግ ጋር ተመሳሳይ አመለካከት ያላቸው እና በመድረክ ውስጥ የተሰባሰቡት የክልል ብሄረተኝነት ከሃገራዊ ብሄረተኝነት ጋር እኩል ቦታ ሊሰጠው ይገባል የሚሉት ወገኖች ያሉበት ነው፡፡ ሌላው ጎራ ደግሞ የለም፣ ይህ አካሄድ ለሃገራዊ እና ህዝባዊ አንድነት መጠበቅ አይበጅም፡፡ ሁለቱ በእኩል ደረጃ ሊቀመጡ አይገባም፡፡ የዘመናት የታሪክ መሠረት ያለውን የኢትዮጵያ ብሄረተኝነትን በዜግነት እኩልነት ላይ በተዋቀረ ዘመናዊ የዲሞክራሲ የፖለቲካ አሠራር በማደስ እና በዚህ ልዩነት እና መበላለጥን በማይጋብዝ ቀመር በመጠቀም ብቻ ነው በሃገራችን የፖለቲካ መረጋጋትን ለማስገኘት የሚቻለው የሚለውን አመለካከት የሚያራምደው ጎራ ነው፡፡ የዜግነት መብት ሙሉ በሙሉ በተከበረበት ሁኔታ በመርህ ደረጃ የብሄረሰብ መብት (ወይም የወል መብት በጠቅላላ) ሊገፈፍ የሚችልበት ህገ-መንግሥታዊ ማእቀፍ አይኖርም፡፡ በተለዬ ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ (በካናዳ፣ በቤልጅየም በስፔን እንደታዬው) በሕገመንግሥቱ ማእቀፍ መፍትሄ ማስገኘት ይቻላል፡፡ የመብት ገፈፋ በአብዛኛው ከመንግሥት አደረጃጀት፣ አመራር እና አሠራር ጋር፣ ከመንግሥት ዲሞክራሲያዊ መሆን እና ያለመሆን ጋር የተያያዘ ነው፡፡ መንግሥት ዲሞክራሲያዊ በሆነበት፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶች፡ (ፖለቲካዊ እና ሰብዓዊ መብቶች) በተከበሩበት ሁኔታ የመንግሥት አደረጃጀት ቅርፃችን፣ በአንድ አገር ውስጥ ባሉ የተለያዩ ብሄረሰቦች/ ማህበረሰቦች መካከል መበላለጥ እንዳይኖር ፍትህ እና እኩልነት የሰፈነበት አመራር እና አሠራር እንዲኖር የሚያግዙ ፖሊሲዎችን ለመንደፍ እና ተግባራዊ ለማድረግ የሚከለክል ሁኔታ ይኖራል ብሎ ለመገመት ያስቸግራል፡፡

የሁላችንም አገር በሆነችው በኢትዮጵያ ውስጥ በተፈጥሮ የሚገኙ እና ከታሪክ የተወረሱ አሌ ሊባሉ የማይችሉ ልዩነቶች አሉ፡፡ ልዩነቶቹ በፓርቲዎች አማካይነት ነጥረው ወጥተው ሲሆን ፓርቲዎቹ አለበለዚያም ህዝቡ መፍትሄ ሊፈልግላቸው ይገባል፡፡ በሃገራችን ካሉት በርካታ ተጨባጭ ልዩነቶች በተጨማሪ አስፈላጊ ያልሆኑ አርቲፊሻል ልዩነቶችን መፍጠር፣ በእሳት ላይ ነዳጅ ከማርከፍከፍ ውጭ ጠቀሜታ ይኖረዋል የሚል ግምት የለንም፡፡ የሶቭየት ህብረት የ70 ዓመታት የዩጐዝላቢያ እና የቸኰዝሎቫኪያ ሶሺያሊስታዊ የብሄር ፌደራሊዝም የ44 — 48 ዓመታት ልምድ ውጤት የሚያስገነዝበንም ይህንኑ ነው፡፡ በሶቭየት ህብረት በዮጐዝላቪያ እና ቼኰዝሎቫኪያ ለፌደራላዊ አድያሞች አወሳሰን

ጥቅም ላይ የዋሉት የቋንቋ እና የብሄር መመዘኛዎች ፌደራላዊ አድያማት አንድ የሚያደርጉአቸውን ነጥቦች በማጥበብ፣ የልዩነት ነጥቦችን በማበራከት፣ ልዩነቶች ባሉበት ቦታ እንኳ እንዳይቆዩ እየሰፉ እና እየበረከቱ እንዲሄዱ በማድረግ በሂደቱ መጨረሻ ላይ መገንጠልን እንዳስከተሉ በተጨባጭ ታይቷል። የካናዳ፣ የቤልጅየም እና የስፔን የበሃውርታዊ ፌደራሊዝም የተሳኩ ክንውኖች የተገነቡት በቅድሚያ ይህን ዓይነት መብት በሚጠይቁ አካባቢዎች በተረጋገጡ የግለሰብ ፖለቲካዊ እና ስብዓዊ መብቶች ላይ መሆኑ ለዚህ አባባል በቂ ማስረጃ ነው። ይህ በሃገራዊ ብሄረተኝነት ሰንደቅ ስር የተሰለፈው የአንድነት ጎራ አመለካከት ነው።

በዚህ ዓብይ የኢትዮጵያን መጻኢ ህልውና ሰንገ በያዘ ጥያቄ ዙሪያ ሶስተኛ አማራጭ የለም። አለኝ የሚል ወገን ካለም ንጥር ባለ የፖለቲካ ትንተና ሶስተኛ አማራጭ መሆኑን በማብሰር የቆዩትን የፖለቲካ አመለካከቶች ድክመት እየነቀሰ ለማውጣት የሚችል አቀራረብን መሠረት አድርጎ ብቅ ማለት ይጠበቅበታል። ይህ እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ ከሁለቱ መሃል ምርጫውን አርጎ ከአንዱ ጎራ ጋር መቀላቀል ነው እንጅ፣ ሁለቱንም እያጣቀሱ ለመሄድ መፈለግ በሁለቱ መሃል ያለውን ፍትጊያ መልክ በማስያዝ፣ ፖለቲካውን ከጠርዝ ወደ መሃል ለማምጣት እና በሃገራችን የፖለቲካ መረጋጋትን ለመፍጠር አያግዝም።

በ1997 የምርጫ ወቅት የነበረው የፖለቲካ አሰላለፍ በቅርጹ ሶስት የተለያዩ የፖለቲካ ስብስቦችን ያቀፈ ቢመስለም፣ በይዘት ግን አሰላለፉ ከሁለት ጎራ ያለፈ አልነበረም። የወቅቱ አሠላለፍ ኢህአዴግ፣ ቅንጅት እና ህብረትን ያካተተ ነበር። ከነዚህ ከሶስቱ መካከል አንዱ ስብስብ አራት ህብረ ብሄራዊ ድርጅቶች በአንድ ስያሜ እና በአንድ የምርጫ ምልክት ውህድ በመሆን የኢትዮጵያ ብሄረተኝነትን መነሻ መሠረታቸው አድርገው የተነሱበት፣ ቅንጅትን የመሠረቱትን አራቱን የፖለቲካ ድርጅቶች ያካተተው ነበር። ሌላኛው ስብስብ መሠረታቸውን የክልል በሄረተኝነት (Ethnic Nationalism) በማድረግ የተሰለፉት ኢህአዴግ እና ህብረት ነበሩ። ከምርጫው በኋላ የክልል ብሄረተኝነት አራማጅ የሆኑት ኢህአዴግ እና የህብረት አባል ድርጅቶች (ደቡብ ህብረት እና ኦብኮ) አለብዙም ንትርክ በፓርላማ ውስጥ ተሰባሰቡ። ከወደፊቱ ምርጫ በፊት በነጻ ተቋማት የመቋቋም አስፈላጊነት ላይ ስምምነት ሊደረስ ከቻለ፣ በ1997 ምርጫ ላይ ያነሳሁትን ቅዋሜ አነሳለሁ የሚል ሃሳብ ያቀረበው ቅንጅት፣ ጥያቄው በኢህአዴግ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ከፓርላም ውጭ ለመሆን ተገደደ።

## 3. ከ1997 ምርጫ በኋላ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች አሰላለፍ

ከምርጫ 1997 በኋላ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የተከሰቱ ጉልህ ክንውኖች የቅንጅት ወደ ሁለት ድርጅቶች ማለትም ወደ አንድነት እና መኢአድ መበተን፣ ከቅንጅት የወጡት እና በግንቦት ሰባት እንቅስቃሴ አማካይነት ከቅንጅት የተለዩ የትግል ስልት ይዘው ብቅ ማለታቸው፣ በህብረቱ ውስጥ የነበሩት ደቡብ ህብረት እና ኦብኮ ከሌሎች መሰል የብሄረሰብ ድርጅቶች እና ታዋቂ ግለሰቦች ጋር በመሆን መድረክ በተባለው የፖለቲካ ስብስብ ውስጥ መታቀፍ እና የቅንጅት ወራሽ ነኝ ብሎ የተነሳው አንድነት ፓርቲ ህጋዊ እውቅና አግኝቶ ለመደራጀት መቻል ናቸው።

የቅንጅት ለሁለት መበተን በኢትዮጵያ የአንድነት ሃይሎች ላይ ያደረሰው መከፋፈል ከወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር በተከናወነበት መልኩ መከናወኑ የማይታለፍ ክንውን ነበር ብሎ መከራከር ይቻል ይሆናል።* መከራከር የማይቻለው በክፍፍሉ ምክንያት በኢትዮጵያ የአንድነት ሃይሎች ጎራ ላይ የደረሰው ብርቱ ስብራት ከፍተኛ መሆኑን ነው። ሰላማዊ እና ህጋዊ የትግል ስልትን እንከተላለን እያሉ በተጨባጭ ግን በብዙ ድርጅቶች ተከፍለው የሚገኙት ስብስቦች አገራዊ አደረጃጀት የሚከተሉ ሃይሎችን በጋራ ሊያሠራ የሚችል አንድ ግንባር/ስብስብ ሳይፈጥሩ ለኢትዮጵያ ብሄረተኝነት ቅድሚያ የሚሰጡት የአንድነት ሃይሎች የኢትዮጵያ ልጆች ሁነው ለክልል በሄረተኝነት ቅድሚያ እንሰጣለን ከሚሉ ሌሎች ወገኖቻቸው ጋር ሲያካሄዱ በቆዩት አራት አስርት ዓመታትን ላሳለፈው የፖለቲካ ፍትጊያ ሃቀኛ አማራጭ ይዘው ሊቀርቡ ይችላሉ ለማለት ያስቸግራል።

---------------

*የ1997ቱ ቅንጅት ሁለት ክፋዬች አንድነት እና መኢአድ ሲሆኑ በአሁኑ ጊዜ ሁለቱም የቅንጅት ወራሾች ነን እያሉ ነው። በአካል ከቅንጅት ወጥቶ በመስመር ግን ከቅንጅት የተለዬ የፖለቲካ ትግል ስልት ይዞ ብቅ ያለው የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ነው። አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ፣ ከፍተኛ የመንፈስ ጥንካሬ እና ለጥቃት አለመንበርከክን የሚጠይቅ ቢሆንም፣ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ስርዓትን ማስፈን የሚቻለው በሰላማዊና ህጋዊ የትግል ስልት በመጠቀም ነው የሚለው አንድነት ፓርቲ የማያራምደው አመለካከት ነው። መኢአድም የዚህ አመለካከት ተጋሪ ሲሆን፣ ይህን የትግል ስልት ሁለቱም ቢሆን የወረሱት ከቅንጅት ነው። መኢአድ ከአንድነት ጋር የሚለያይበት ፓርቲን በዲሞክራሲያዊ መሠረት ላይ የማዋቀር እና የመምራት ጥያቄ ላይ ነው። በአንፃሩ በግንቦት ሰባት ንቅናቄ በኩል የተተለመው የትግል መስመር ከቅንጅት የተለዬ ነው። የግንቦት ሰባት ንቅናቄ የሰላማዊ ፖለቲካ ትግሉን በር ጥርቅም አድርጐ ከዘጋ እና ለመክፈትም ፈቃደኝነት እንደሌለው በአደባባይ የሚገልፅ መንግሥት ባለበት ሁኔታ በሰላማዊ እና ህጋዊ ትግል በመጠቀም ኢትዮጵያ ውስጥ ዲሞክራሲን ለማስፈን አይቻልም። ኢትዮጵያ ውስጥ ለዲሞክራሲ የተመቻቸ ሁኔታ ለመፍጠር የሚቻለው በቅድሚያ ሰላማዊ እና ህጋዊ ባልሆነ የትግል ስልት ኢህአዴግን መጣል ሲቻል ነው የሚል አመለካከት የሚያራምድ ነው። የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ድርጅታዊ አሠራርም ከትግል ስልቱ ጋር የሚሄደው ሚስጥራዊ አሠራር ነው።

የፖለቲካ ፍልስፍናቸው በክልል ብሄረተኝነት ዙሪያ የተቃኘው ኢህአዴግ እና በመድረክ ውስጥ የተሰባሰቡት የፖለቲካ ድርጅቶች በመሠረታዊ የፖለቲካ አመለካከታቸው የሚመሳሰሉ ናቸው። ከሃገራዊ ሉአላዊነት፣ ከኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት፣ ልማትን ከማፋጠንና የተደላደለ መሠረት እንዲኖረው ከማድረግ አንጻር ወሳኝ ሚና የሚጫወተውን የመንግስት አደረጃጀት በተመለከተ ኢህአዴግ እና በመድረክ ዙሪያ የተሰባሰቡት የፖለቲካ ድርጅቶች እና ግለሰቦች የሚያራምዱት አመለካከት አንድ ወጥ ነው። ይኸውም የኢትዮጵያ መንግስታዊ አወቃቀር ብሄረሰብ እና ቋንቋን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት የሚል ነው።

የዚህ አቋም ደጋፊዎች የታሪክ ግንዛቤ የኢትዮጵያን ምስረታ በአንድ መቶ አመት የሚወስን ነው። የዚህ አመለካከት አራማጆች የሃገሪቱ ታሪክ ጠፍቷቸው አይደለም። ትምህርት እና ስልጣኔ ባልተስፋፋበት አገር ህዝብን ለፖለቲካ ስልጣን መወጣጫነት ለማሰለፍ የሚቀለው መንገድ ማስረጃ ሊቀርብበት የሚችለውን ታሪክ ለህዝቡ በማስጨበጥ እንዳልሆነ ጠንቅቀው ይገነዘባሉ። ህዝብን የወደፊት ተስፋውን ሳይሆን የቆዬ ቁስሉን በመኮርኮር፣ በሰከነ አስተሳሰቡ ሳይሆን በግንፍል ስሜቱ እንዲመራ በመቀስቀስ፣ እርስ በርሱ እንዲጠራጠር እና የቆዬ ታሪካዊ ትስስሩን በውል እንዳይገነዘብ ማድረግ ነው የክልላዊ ብሄረተኝነት ፖለቲካ ዓይነተኛ መለያ።

በመድረክ ውስጥ የተሰበሰቡት ድርጅቶችም ሆኑ ግለሰቦች የዚህ አመለካከት ማህተም ሁኖ የተቀረጸውን የዘመኑን የሃገራችን ህገ መንግስት በቀረበበት መልኩ እና በሰነድነት ደረጃ እንክን ሊወጣለት አይችልም ብለው ያምናሉ። በመድረክ ውስጥ የተሰባሰቡት የፖለቲካ ድርጅቶች በዚህ አብይ ፖለቲካ ጥያቄ ዙሪያ ከኢህአዴግ ጋር ያላቸው ልዩነት በሕገ መንግስቱ ይዘት ላይ ሳይሆን፣ ኢህአዴግ አተገባበሩን እያዛባ ነው የሚል ነው። በህብረተሰባችን ውስጥ በእጅጉ አከራካሪ የሆነው ይህ ጥያቄ እና በዚህ ጥያቄ ዙሪያ በሕገ መንግስቱ ውስጥ የተቀረጹ አንቀጾች እንዲነኩባቸው አይፈልጉም። በታህሳስ ወር አጋማሽ በ2001 ላይ የመድረክ አባል ድርጅቶች በኢምፒርያል ሆቴል ባደረጉት ስብሰባ የአረና ትግራይ ሊቀመንበር አቶ ገብሩ አስራት ባቀረቡት ፅሁፍ ላይ በኢትዮጵያ የመንግሥት አወቃቀርን በተመለከተ የድርጅታቸውን አቋም ሲገልፁ “<u>በኢትዮጵያ በብሄር ብሄረሰብ ላይ የተመሠረተ ፌደራሊዝም መከተልና መተግበር የሕዝቦች ቋንቋ ባህል፣ ማህበራዊ ኢኰኖሚያዊና ፖለቲካዊ መብቶች ከማስከበር አንፃር ትክክለኛ አቅጣጫ ይሆናል</u>” በማለት አስቀምጠውታል።*

በአንጻሩ በሃገራችን የመንግስት አደረጃጀትን እና የፓርቲ አወቃቀርን በተመለከተ የሚያራምዱት ፖለቲካ በኢትዮጵያ ብሄረተኝነት (Supra-ethnic Ethiopian Nationalism) ዙሪያ እንደያጠነጥን የሚፈልጉ የአንድነት ሃይሎች ለመንግስት ፌደራላዊ አደረጃጀት ቋንቋን እና ብሄርን እንደብቸኛ መመዘኛ አድርጐ መጠቀም ፖለቲካ ፓርቲዎችን በዚሁ መርህ መሠረት እንዲደራጁ ማድረግ ለፖለቲካ አለመረጋጋት፣ ለሃገራዊ እና ሕዝባዊ አንድነት መላላት፣ ለተፋጠነ እና ሚዛናዊ ለሆነ ልማት ደንቃራ ይሆናል የሚል ብርቱ ስጋት ያላቸው ናቸው። አንድነት ፓርቲ የዚህ አመለካከት ጽኑ ተጋሪ ነው። በመሆኑም በፕሮግራም ደረጃ የሃገራችን ፌደራላዊ መንግስት አወቃቀር መስፈርቶች መካከል በቋንቋ/ብሄር ዓይነተኛ መስፈርት ቢሆንም ብቸኛ መስፈርት መሆን የለበትም የሚል ጽኑ እምነት አለው። መስፈርቶቹ ከኢትዮጵያ ህዝብ ታሪካዊ አንድነት ጋር የተጣጣሙ፣ ከቆዬ የመንግስታዊ ስርዓት ውስጥ ጠቃሚ የሆኑ ገጽታዎችን ያገናዘቡ፣ የሕዝቡን መዋሃድ (Integration) እና መተጋገዝ የሚያጠናክሩ፣ ጎጅ እና አፍራሽ የሆነ ፉክክርን የማይጋብዙ፣ መቆሚያ ሊገኝለት ወደ ማይችል የድንበር ንትርክ እና የእርስ በርስ እልቂት የማያመሩ እንደ ሃብትና ሕዝብ ብዛትመመጣጠን፣ የተደጋጋፊ ልማት አመችነት፣ የአስተዳደር ቅልጥፍና ላሉ መመዘኛዎች ትኩረት ሊሰጥ ይገባል የሚል የጸና አመለካከት አለው። ይህም ከሃገራችን ታሪክ ትክክለኛ ግንዛቤ የመነጨ አቋም ነው።

በቅንጅት ማኒፌስቶ አራቱም አባል ድርጅቶች ተስማምተው ሕግመንግሥታዊ ማሻሻያ ሊደረግባቸው የሚገባ ዋና ዋና ጉዳዩች በሚል የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብት መከበር አና የፌድራል ክልሎች የሚዋቀሩበትን መስፈርት በተመለከተ ቅንጅት አማራጭ መፍትሄዎች እንዳቀረበ ተመልክቷል። በአንድነት ፕሮግራምም ውስጥ የፌድራል አውቃቀርን በተመለከተ የሰፈረው አባባል ከቅንጅት ማኒፌስቶ ቃል በቃል የተወሰደ ሲሆን፣ "**የፌድራሉ ክልሎች የሕዝብ ፈቃደኝነትን፣ ታሪካዊ እና ባህላዊ ትስስርን፣ ቋንቋን፣ የሕዝብ አሠፋፈርን፣ መልከዓ**

——————

*እንደ ዶ/ር መራራ ጉዲና የመድረኩ ሌላ አይዲዎሎግ እንደሆኑ የሚገመቱት አቶ ስዬ አብርሃ በቅርቡ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፣ በተቀረጸበት ወቅት እሳቸው ንቁ ተሳታፊ በነበሩበት በአሁኑ የሃገራችን ህገ መንግስት ላይ ትልቅ እምነት እንዳላቸው ገልጸዋል። (በነሐሴ ወር 2000 ዓ.ም ሁለተኛ አጋማሽ ላይ የምክክር መድረኩ ምን ለመስራት እንዳሰበ የሰጠውን ጋዜጣዊ መግለጫ ይመልከቱ)

**ምድራዊ አቀማመጥን፣ የልማት አመችነትን እና የአስተዳደር ቅልፍጥናን እና የመሳሰሉትን መመዘኛዎች ያገናዘበ ይሆናል ይላል።** (የቅንጅት ማኒፌስቶ 1997፡89) (የአንድነት ፕሮግራም 2000፡5) በፌድራል አወቃቀር መስፈርቶች ላይ በውጭ ምሁራን የተደረጉ ጥናቶች ቀደም ሲል በቅንጅት አሁን ደግሞ በአንድነት ፕሮግራም ውስጥ የሰፈሩትን የፌድራል አወቃቀር መስፈርቶች ሲያጠቃልሉ በአካባቢያዊ - ክፍለሃገራዊ መርሆ (Regional – Territorial Principle) ውስጥ ያካትቱታል። ይህ የፌድራል አወቃቀር ዘይቤ እያንዳንዱ ሃገር በታሪኩ ያላፈበትን የመንግሥታዊ አወቃቀር ልምድ ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ነው። የተወሰነ ጆግራፊያዊ ክልልን ህዝብ በህግ ከሚሰጠው የውስጥ አስተዳደር ነፃነት ጋር የሚያጣምር ፌደራላዊ አደረጃጀት ነው። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ይህ መርሆ ሲተረጐም አሁን በተካለሉበት መልክ የቆዩ ታሪክ የሌላቸው የፌድራሉ መንግሥት ክልላዊ መስተዳድሮች (አዲያማት) በአንቀፅ 39 ከተደነገገው የመገንጠል መብት በስተቀር አሁን ያላቸው ሕገመንግሥታዊ መብት እንደተከበረ ሁኖ፣ እያንዳንዳቸው <u>የብሄር ስም ወደማይሰጣቸው</u> ወደ ተወሰኑ <u>ጆኦግራፊያዊ/ልማዳዊ/ስያሜ ወደሚሰጣቸው ክልሎች ይከፈላሉ ማለት ነው።</u> ይኸ በመርህ ደረጃ የአንድነት ሃይሎች ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግሥት አከፋፈል እና አወቃቀር የሚያቀርቡት አማራጭ ነው። ለማናቸውም ከላይ በተጠቀሰው የአካባቢያዊ - ክፍለሃገራዊ መርህ መሠረት የሚተለመው የመንግሥታዊ አደረጃጀት ፕሮግራማዊ አማራጭ ዝርዝር ወደፊት የአንድነት ሀይሎች በጋራ በሚያወጡት የምርጫ ማኒፌስቶ ይበልጥ ተብራርቶ እንደሚቀርብ ይጠበቃል። ይህ ዓብይ የፖለቲካ ጥያቄ አንድነትን በሃገር አቀፍ ደረጃ ከተቋቋሙ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር የሚያቀራርብ ሲሆን፣ በአንጻሩ አንድነትን በመድረክ ውስጥ ከተሰባሰቡ የብሄር ድርጅቶች ከሚያራምዱት አመለካከት ጋር የሚለያይ ነው።

በኢህአዴግ እና በመድረክ ዙሪያ የተሰባሰቡትን የፖለቲካ ድርጅቶች የሚያመሳስላቸው ሌላው ከዚሁ የፌደራላዊ አወቃቀር ጥያቄ ጋር የተቆራኜ አመለካከትም አለ። ኢህአዴግ እና የመድረክ የፖለቲካ ስብስብ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት መግለጫ ልዩ ልዩ ሕዝቦች እና ብሄረሰቦች ናቸው የሚል አመለካከት ያራምዳሉ።* በአንጻሩ የአንድነቱ ጐራ የሃገራችን ህዝብ የአንድነት ስሜት ዓይነተኛ መግለጫ የሆነው የኢትዮጵያ ብሄረተኝነት (Ethiopian Nationalism) ለሃገራዊ መንግስታዊ ሉዓላዊነት መሠረት እና ዓይነተኛ መግለጫ ሊሆን ይገባል ብሎ ያምናል። በኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ጉዳዬች ብዙ ፅሁፎችን ያበረከቱት፣ ኢትዮጵያንም በሚገባ የሚያውቋት ፕሮፌሰር ሃሮልድ ማርከስ **"የሃገሪቱ ታሪክ አንድ ትልቅ ታሪካዊና አንድነቱ የተጠበቀ መንግሥት የመኖርን ሃሳብ በተጨባጭ እውነታነት የያዘ ነው። ከጊዜ ወደ ጊዜ ሃገሪቱ ወደ ተለያዩ ግዛቶች የተበታተነችባቸው ወቅቶች ቢኖሩም፣/ኢትዮጵያ/ ከህዝቡ ህሊና የተፋቀችበት ጊዜ ጨርሶ ካለመኖሩም በላይ አንድነቷም በተደጋጋሚ ሲረጋገጥ መቆየቱም የታዬ ሐቅ ነው፤"** በማለት ያሰፈሩት ሃሳብ እየተዘጋጀ በነበረው ህገመንግሥት ውስጥ እንዲካተት በወቅቱ ሃሳብ ቀርቧል። (መድረክ 1986፡ (1)2፡ 67) ይህ ሳይሆን ቀረ። በመሆኑም የአንድነት ሀይሎች በህገ መንግስቱ ውስጥ የሰፈሩ በዚህ አብይ አገራዊ ጉዳይ ዙሪያ የተቀረጹ አንቀጾች በዲሞክራሲያዊ እና በሰላማዊ ፖለቲካዊ አግባብ ሊሻሻሉ እና ሊለወጡ ይገባል ብለው ያምናሉ። በብዙ የአፍሪቃ አገሮች ህገ መንግሥቶች ዘላቂ ያልሆኑት እና በየጊዜው የሚለወጡት ወይም እንዲሻሻሉ የሚደረግበት ምክንያት 1ኛ/ በጦርነት አሸናፊ ሁነው ስልጣን የሚይዙ ሃይሎች ፍላጐት ብቻ እንደማህተም የሚቀረፅባቸው በመሆኑ 2ኛ/ በየሃገሮቹ ውስጥ ያሉ ሁሉንም ማህበረሰቦች ጥቅም በሚዛናዊነት የሚያስጠብቁ ሁነው አለመቀረፃቸው ነው። በሃገራችንም የአንድነት ሃይሎች በሰላማዊ እና ህጋዊ አግባብ የሕገ-መንግሥት መሻሻልን (Constitutional Reform) ከሚጠይቁባቸው በዚህ ፅሁፍ ውስጥ በየቦታው ከተዳሰሱ ጉዳዬች በተጨማሪ፣ በእያንዳንዱ የፌድራል መስተዳድር አሃድ (Federal Unit) ውስጥ የህዝብ ብዛትን በተመለከተ አነስ ባለ ቁጥር የሚገኙ ማህበረሰቦች ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ቋንቋን ጨምሮ ባህላዊና ማህበራዊ መብቶቻቸውን ግልፅ በሆነ እና በማያሻማ ሁኔታ (Minority protection rights) በሕገ-መንግሥቱ ውስጥ ማካተቱ አስፈላጊነት ሆኖ በመገኘቱ ነው። ከዚህ ድምዳሜ ላይ የተደረሰውም ከኢትዮጵያ ታሪክ ሊቀስም ለሚገባው በጎ ግኝት ተገቢውን አክብሮት በመስጠት እና በጎ ጎን ያልነበራቸው የታሪክ ክንውኖች እንዳይደገሙ ዘመኑ ያፈራውን የመንግስት ስልጣን የሚገደብባቸውን ዘይቤዎች በተግባር ለማዋል በቁርጠኝነት መነሳት የሚያስፈልግ መሆኑን በመገንዘብ ነው። የዚህ ጥያቄ አፈታት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ስምምነት ወይም የውሳኔ ሕዝብ ውጤት የሚጠይቅ ነው።

የግለሰብ እና የቡድን መብትን በተመለከተ በመድረክ ስብስብ የፖለቲካ ድርጅቶች እና አንድነትን ጨምሮ ሌሎች በሃገር አቀፍ ደረጃ በተቋቋሙ የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል በየፕሮግራሞቻቸው ያሠፈሩበት ሁኔታ ይለያያል። ለምሳሌ የቅንጅት የምርጫ ማኒፌስቶ "... እጅግ ውድ የሆነው የሰው ልጅ እሴት ነፃነት እንደመሆኑ፣ ለሁሉም መስክ የግለሰብ ነፃነት ቀዳሚ ስፍራ ይይዛል፤ ... የአንድ ማህበረሰብ የተወሰኑ ክፍሎች የጋራ መብቶች የግለሰብን ነፃነት በማይሸረሽርና አደጋ ላይ በማይጥል መልኩ መከበር እንደሚገባቸው ቅንጅት ያምናል፤" ይላል(ገፅ 7)። የአንድነት ፕሮግራም "አንድነት በግለሰብ ነፃነት ላይ በተመሠረተ የዲሞክራሲ መሠረታዊ መርሆዎች እና ፍልስፍና ይመራል። ሆኖም ከሶሺያል ዲሞክራሲ እና ከስምምነት (ኰንሴንሰስ) ዲሞክራሲ አመለካከቶች መካከል ለሃገራችን እድገትና ብሄራዊ ግንባታ ጠቃሚ የሆኑ እሴቶችንም ይቀበላል፤" ይላል(ገፅ 4)። በሌላ በኩል "የዜጐች እና ሕዝቦች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ይከበራሉ" (የኤፍድሪ ሕገመንግስት ገፅ 10) ከሚለው ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ በመነሳት የመድረክ ስብስብ የፖለቲካ ድርጅቶች የግለሰብ፣ የብሄረ ብሄረሰቦች እና የቡድን መብቶች በተጓዳኝነት መከበር

አለባቸው ብለው ያምናሉ።

የልማታዊ መንግሥት የአስራ ዘጠነኛው ክ/ዘመን የመጀመሪያዋ ተምሳሌት ከሁለተኛ ዓለም ጦርነት በኋላ ፖለቲካዋን እና ኢኮኖሚዋን በአዲስ መልክ አደራጅታ ብቅ ያለችው ጃፓን ናት። ከጃፓን ጋር በልማታዊ መንግሥትነት የሚታወቁት እና የመጀመሪያው ዙር የእስያ ነብሮች ተብለው የሚጠሩት ታይዋንና ደቡብ ኰሪያ ናቸው። ሁለተኛው ዙር የእስያ ነብሮች ተብለው የሚታወቁት ታይላንድ፣ ማሌቪያ እና የከተማ-መንግሥታት (city-states) የሆኑት ኰንግ ኰንግ  እና ሲንጋፖር ናቸው። ሁሉንም አንድ የሚያርጋቸው በኢኮኖሚው መስክ 1ኛ/ በገበያ ኢኮኖሚ በመመራት በየሃገሮቻቸው ለካፒታሊስት የኢኮኖሚ ግንኙነት መንሰራፋት የቆሙ መሆናቸው እና 2ኛ/ የካፒታሊስቱ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ስርዓት አካል መሆናቸው 3ኛ/ ከጀፓን በስተቀር በሁሉም በተጠቀሱት አገሮች ለኢኮኖሚ ልማቱ አመራር የሰጡት በፖለቲካው ዘርፍ የአንድ ፓርቲ የበላይነት አገዛዝ በሰፈነበት ሁኔታ መሆኑ ነው። ከ1990ዎቹ ወዲህ በአንድ ፓርቲ ፈላጭ ቆራጭነት ሥር የኢኮኖሚ ልማት ያስመዘገቡት ቻይና እና ቬየትናም በልማታዊ መንግሥት ፈርጅነት የሚመደቡ ናቸው። ጃፓንን በዚህ ረገድ ለየት የሚያደርጉት ገዥው የሊበራል ዲሞክራቲክ ፓርቲ በአንድ ወቅት አስር ወር ለማይሞላ ጊዜ ስልጣን ለተቃዋሚ ፓርቲው ቢለቅም፣ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጀምሮ እስካሁኑ ወቅት ድረስ በየጊዜው እንከን የማይወጣለት ነፃ እና ፍትሃዊ ምርጫ በማድረግ በተከታታይ በህዝብ እየተመረጠ ስልጣን ላይ ለመቆየት መቻሉ ነው። ከጃፓን በተጨማሪ በዲሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግሥትነት የሚታወቁት፣ አየርላንድ፣ ብራዚል፣ እስራኤል (1950-1973) ከአፍሪካ ደግሞ ሞሪሽስ ቦስትዋና ሲሆኑ፣ የደቡብ አፍሪካ መንግሥትም እየተቋቋመ ያለ የዲሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግሥት የሚል መጠሪያ ተሰጥቶታል።

ከኢኮኖሚ ፍልስፍና አንፃር ኢህአዴግ አሁን እያደረገ ያለው የአብዬትዊ ዲሞክራሲ የኢኮኖሚ እና ፖለቲካ አመለካከትን በሃያኛው ክ/ዘመን የልማታዊ መንግሥት አመለካከት መቀየር ነው። ከላይ ለማመልከት እንደተሞከረው አብዮታዊ ዲሞክራሲና ልማታዊ መንግሥት የመነጩባቸው የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ፍልስፍናዎች ለየቅል ቢሆኑም፣ ከፖለቲካው አንፃር ሁለቱም ለአንድ ፓርቲ የፖለቲካ የበላይነት የቆሙ መሆናቸው በቅርፅ አንድ እንዲሆኑ አድርጕአቸዋል። የልማታዊ መንግሥት ፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚ መርሆዎች የካፒታሊስቱን ስርዓት መሠረት ያደረጉ ናቸው። በአንፃሩ የአብዬታዊ ዲሞክራሲ ኢኮኖሚያዊ አመለካከት መሠረት አድርጕ የተዋቀረው በማርክሲስት ሌኒኒስት የፖለቲካ አስተምህሮ ላይ ነው። ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት፣ ከሶቪያሊስቱ ዓለም መንኰታኰት፣ ሩስያና ቻይና ኢኮኖሚያቸውን በካፒታሊስቱ ዓለም ከሚመራው እና ከተዘረጋው የዓለም ገበያ ጋር ማስተሳሰራቸው እና ሃገራዊ ኢኮኖሚያቸውንም በገበያ ኢኮኖሚ መሠረት እንዲንቀሳቀስ ማድረግ ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ የአብዬታው ዲሞክራሲ ኢኮኖሚያዊ አመለካከት ከመሠረቱ የተገነጠለ እና የሚቀመጥበት የሌለው ግንጥል ጌጥ ሁኖ የቀረ ክስተት ነው።

የአብዬትዊ ዲሞክራሲ ፖለቲካዊ መሠረት የመነጨው ከማርክሲዝም ሌኒኒዝም የአብዬትዊ ሶሽያል ዲሞክራሲ (Revolutionary Social Democracy) አስተምህሮ ነው። እንደሚታወቀው የሶሽያል ዲሞክራሲ የፖለቲካ ሞዴል የቶማስ ሀብስና የዣን ዣክ ሩሶን የፖለቲካ ፍልስፍና መሠረት አድርጕ የተነሳ እና በማርክስ እና ሌኒ ፅንፈኛ (አብዬታዊ) አመለካከት ማሳረጊያ ያገኘ ነው። የሶሺያል ዲሞክራሲ ፖለቲካ ግለሰብ በከባቢው ካለው ማህበረሰብ አንፃር የተወሰነለትን ቦታ ይዞ እንዲኖር  በማድረግ ረገድ መንግሥት ከፍተኛ ሚና ሊኖረው ይገባል፣ ይህም መንግሥት ከግለሰብ ነፃነት እና መብትን ከማስጠበቅ ይልቅ ለማህበረሰቡ የጋራ ፍላጐት ወይም መብት ቅድሚያ መስጠት አለበት የሚል አመለካከት የሚያራምድ ነው።

በአንፃሩ የለዘብተኛ (Liberal) ዲሞክራሲ የፖለቲካ ሞዴል የጆን ሎክን የፖለቲካ ፍልስፍና መሠረት አድርጕ የተነሳ ሲሆን፣ ግለሰቦች የራሳቸውን ጥቅም ለማሳካት በሚያደርጉት ጥረት ምንም ዓይነት ገደብ ሊደረግባቸው አይገባም። መንግሥት እንደ መብት አስከባሪነቱ በግለሰቦች ጥረት ላይ ጣልቃ መግባቱ የሚደገፈው የአንዱ ግለሰብ መብት የሌላውን ግለሰብ መብት በሚጋፋበት ጊዜ ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ የግለሰብ መብቶች ክቡርና በተፈጥሮ የተሰጡ፣ ከመንግሥት ውጭ ህልውና ሊኖራቸው የሚገባ በመሆናቸው በመንግሥት ሊደፈሩ አይገባም። እነዚህን መብቶች የሚደፍር መንግሥት መቃወም ተፈጥሯዊ ነው የሚል አመለካከት የሚያራምድ ነው።

ሁለቱም ማለትም የለዘብተኛ ዲሞክራሲ እና የሶሺያል ዲሞክራሲ የፖለቲካ ሞዴሎች ከየፖለቲካ ሞዴሉ ጋር የሚሄድ የኢኮኖሚ ሞዴል አላቸው። ለህብረተሰቡ የጋራ ፍላጐት መከበር ቀዳሚ ትኩረት የሚሰጠው፣ መንግሥትም የዚህ የጋራ መብት አስከባሪ እንደሆነ አድርጕ የሚወሰደው ሶሺያል ዲሞክራሲ ከለዘብተኛ ዲሞክራሲ የፖለቲካ ፍልስፍና አንፃር በተቃኜ ህገመንግሥታዊ ስርዓት ለመመራት ፈቃደኛ ወደ ማይሆንበት ደረጃ ሲሸጋገር አብዬትዊ ሶቪያል ዲሞክራሲ ይሆናል። ሌኒን ከምእራብ አውሮፓ ሶሺያል ዲሞክራቶች የተገነጠለበት ታሪካዊ ሁኔታ ይሄን አይነት መልክ የያዘ ነበር።

በአንደኛው የዓለም ጦርነት ዋዜማ ካፒታሊዝም በከፍተኛ ደረጃ ዳብሮባቸው የነበሩ የምእራብ አውሮፓ አገሮች ሶሺያል ዲሞክራቶች

በኢኮኖሚው መስክ ካፒታሊዝምን ማሻሻል እንጅ መሻር ወይም በኮሚኒዝም መተካት አያስፈልግም ብለው ካምፓቸውን ለዩ፡፡ በወቅቱ ከምእራብ አውሮፓ አንፃር በሩስያ የካፒታሊዝም እድገት በዝቅተኛ ደረጃ ይገኝ ስለነበር፣ የሩሲያ አብዮታዊ ሶሻል ዲሞክራቶች (እነ ሌኒን) ከመደባዊ እና ብሄራዊ ጥንቅር አንፃር ለሩሲያ አብዬት ድጋፍ ለማስገኘት ካፒታሊዝምን ማስወገድ እንጅ መጠገን አይቻልም የሚል አቋም ያዙ፡፡ የሶሺያሊስቱ የኢኮኖሚ ስርዓት ይህን የማርክስን እና የሌኒንን ኢኮኖሚያዊ አመለካከት መሠረት በማድረግ ተዋቀረ፡፡ ከኢኮኖሚ ግንኙነት አንፃር ከሩሲያ ጋር ሲነፃፀር በቻይና አብዬቱ በአሸናፊነት በወጣበት በ1949 የካፒታሊስቱ ስልተ ምርት እድገት በጣም ዝቅተኛ ስለበር፣ የሶሺያሊዝም ማህበራዊ መሠረት የሆነው ወዝአደር ቁጥር በእጅጉ አናሳ ነበር፡፡ በመሆኑም በቻይና ሶሺያል ዲሞክራሲ ቦታ አልነበረውም፡፡ በወቅቱ ቻይና የገበሬ አገር ስለነበረች የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዬት የሚባለው ፅንሰ ሃሳብ ተፈለሰፈ፡፡ ሶሺያሊዝም ሊገነባ የሚችለው በቅድሚያ የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዬትን በማካሄድ እንደሆነ ተበሰረ፡፡ በተግባርም በቻይና የተፈፀመው ይኸው ነበር፡፡ አብዬትዊ ዲሞክራሲ የካፒታሊስት የኢኮኖሚ ግንኙነትን ወደ ጐን በተመተው የሶሺያሊስት የኢኮኖሚ ግንኙነት የሚመሰረትበት ድልድይ ነው፡፡ የሶሺያሊስት የኢኮኖሚ ግንኙነትን (Socialist Relations of Production) የመመስረት የፖለቲካ ዓላማ በሌለበት ሁኔታ ስለ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዬት ወይም በአጭሩ ስለአብዬታዊ ዲሞክራሲ ኢኮኖሚም ሆነ ፖለቲካ ሞዴል ማውራት አይቻልም፡፡

አሁን በሃገራችን ባለው ተጨባጭ የኢኮኖሚ ሁኔታ ኢህአዴግ የሃገራችንን ኢኮኖሚ ከገበያ ኢኮኖሚ አንፃር (Capitalist Relations of production) እያዋቀረ እንደሆነ በይፋ እየገለፀ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ኢኮኖሚውን መቃኘት የሚቻለው ከገበያ ኢኮኖሚ መርህ ወይም ይኸን መርህ መሠረት አድርጐ ከተነሳው የሃያኛው ክፍለ ዘመን የልማታዊ መንግሥት ኢኮኖሚያዊ ሞዴል አንፃር እንጅ ከአብዬታዊ ዲሞክራሲ የኢኮኖሚ ሞዴል አንፃር ሊሆን አይችልም፡፡

በኢኮኖሚው መስክ የአንድነት ፓርቲ አቋም የሚከተለው ነው፡፡ የአጠቃላይ ኢኮኖሚውን (Macro Economy) መስተጋብር በመምራት እና በመቆጣጠር ረገድ፣ ሃገራዊ ገቢን ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ በህብረተሰቡ ውስጥ በማከፋፈል ረገድ የመንግስት ሚና እንደተጠበቀ ሁኖ፣ ሃብትን የማደራጀት፣ የመያዝ እና የማሰማረቱን (resource allocation) ሚና በምንም መለኩ ባልተገደበ፣ ከፓርቲም ሆነ ከመንግስታዊ ኢኮኖሚያዊ ተቋማት ጣልቃ ገብነት ነጻ ለሆነ የገበያ ስርዓት እንዲተው የሚል የጸና አቋም አለው፡፡ ስለሆነም በኢኮኖሚው ዘርፍ የአንድነት ፓርቲ የኢኮኖሚ ፍልስፍና የለዘብተኛ እና የሶሺያል ዲሞክራሲያዊ የኢኮኖሚ አመለካከት ቅይጥ ነው፡፡ ስለሆነም የአንድነት ፓርቲ የኢኮኖሚ ፍልስፍና ከአብዮታዊ ዲሞክራሲ አመለካከት ጋር የተለየ ነው፡፡

የመሬት ጥያቄን በተመለከተ ኢህአዴግ እና በመድረክ ውስጥ የተሰባሰቡት አብዛኞቹ የፖለቲካ ድርጅቶች ተመሳሳይ አቋም የሚያራምዱ ናቸው፡፡ የኢኮኖሚ ፖሊሲን በተመለከተ የኢህአዴግ አቋሞች ግልጽ ናቸው፡፡ "መሬት፣ የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦች እና ሕዝቦች የጋር ንብረት ነው" (ኢፍድሪ ሕገመንግሥት ገፅ 28)፡፡ የኢህአዴግ የኢኮኖሚ አመለካከት ዋንኛ ገላጭ ባህሪ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ፍልስፍና ነው፡፡ (የኢህአዴግ ፕሮግራም 1987) በጽንሰሃሳብ ደረጃ አብዮታዊ ዲሞክራሲ በልማታቸው ወደ ኂላ የቀሩ አገሮች ካፒታሊስታዊ ያልሆነ ጎዳና ተከትለው ወደ ሶሺያሊዝም ሊሸጋገሩ ይችላሉ የሚለውን በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት በሶሺያሊስቱ ዓለም ሲራመድ የነበረውን አስተምህሮ የተከተለ ወደ ሶሺያሊዝም የሚያመራ የቅድመ ሶሺያሊስት የእድገት ጎዳና ነው፡፡ መሬትን ጨምሮ፣ ዋና ዋና የፋይናንስ የማምረቻ እና የአገልግሎት ሰጪ ተቋሞች ከመንግስት ቁጥጥር ስር መውጣት የለባቸውም ብሎ የሚያምን፣ የሳይንሳዊ ሶሺያሊዝምን ዋና ዋና መሠረት ሃሳቦች የሚቀበል ነው፡፡ በዚህም ከደርግ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡

እስከ ግንቦት 1997 ድርስ የኢህአዴግ የኢኮኖሚ ፍልስፍና በአብዬታዊ ዲሞክራሲ የፖለቲካ አመለካከት ዙሪያ የተቃኘ ነበር፡፡ ከግንቦት 1997 ምርጫ በኂላ የኢህአዴግ ኢኮኖሚያዊ ፍልስፍና በልማታዊ መንግሥት ላይ ያጠነጠነ ሁኗል፡፡ ይኸ የቅርፅ እንጅ የይዘት ለውጥ አይደለም፡፡ (ከጃፓን በስተቀር የመጀመሪያ ዙርም ሆነ የሁለተኛ ዙር የእስያ ነብሮች የሚባሉት የልማታዊ መንግሥት ዓይነተኛ መግለጫ የሆኑት የእስያ አገሮች በኢኮኖሚ ልማት እምርታ ያስገኙት በፖለቲካው ዘርፍ በአንድ ፓርቲ አምባገነናዊ አዛዝ ስር ነው፡፡ ልዩነቱ የጃፓኑ ሊበራል ዲሞክራቲክ ፓርቲ ጐላ ብሎ የተገኘ ፓርቲ (Dominant Party) ሲሆን፣ የተቀሩት በፈላጭ ቆራጭ የአንድ ፓርቲ (authoritarian one-party state) አገዛዝ ስር የነበሩ መሆናቸው ነው፡፡ በሌሎቹ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ልማት ባስመዘገቡ የእስያ ነብር አገሮች ማለትም በደቡብ ኮሪያ፣ ታይዋን፣ ሲንጋፖር፣ ማሊዥያ፣ ኢንዶኒዢያ የኢኮኖሚ ልማት ባስመዘገቡባቸው ጊዜያት ፖለቲካቸው ዲሞክራሲያዊ መሆን የጀመረው ቆየት ብሎ በተመዘገበው የኢኮኖሚ ልማት ሳቢያ በተፈጠረው የመካከለኛ መደብ ግፊት ነው፡፡ የፖለቲካ እና ዲሞክራሲያዊ መብታቸውን የተጐናፀፉት የኢኮኖሚ ልማቱ ቀድሞ ግቡን ከመታ በኂላ በተፈጠረው አስገዳጅ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ሁኔታ ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ለጃፓንን ሞዴል የተለየ ግምት እንደሚሰጡ ባዘጋጁት ጥናታዊ ፅሁፍ ላይ ገልፀዋል፡፡ በጃፓን ለገዥው የሊበራል ዲሞክራቲክ ፓርቲ የፋይናንስ አስተዋፅኦ ሲያበረክቱ የነበሩት በዋንኛነት በቤት ግንባታ (Real Estate) እና በኮንስትራክሽን ዘርፍ

የተሠማሩ ባለሃብቶች ነበሩ። በሀገራችንም በአሁኑ ወቅት ከሌሎች ክፍላተ ኢኮኖሚዎች ይልቅ በሚደረግላቸው ድጋፍ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙት እነዚሁ የኢኮኖሚ መስኮች ናቸው። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በልማታዊ መንግሥት ልምድ ቀዳሚዋ እና በእጅጉ የተሳካላት ጃፓን ናት። በኛም አገር የጃፓንን አርአያነት ለመከተል ታስቦ ከሆነ ጥሩ ነው። የጃፓንን ልማታዊ መንግሥት አርአያነት ለመከተል ከታሰበ ግን ከአብዮትዊ ዲሞክራሲ አስተምህሮ ጋር አብሮ ሊሄድ ስለማይችል አብዮታዊ ዲሞክራሲን በመስኮት አሽቀንጥሮ መጣልን ይጠይቃል። ከምርጫ 97 በኂላ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እያደረጉ ያሉትም ይህንኑ ይመስላል። ኢህአዲግ ከአብዮታዊ ዲሞክራሲ የኢኮኖሚያዊ አመለካከት ወደ ልማታዊ መንግሥት ኢኮኖሚያዊ አመለካከት እየተሸጋገረ ነው። ይሁንና ሽግግሩ አሁን ወደ ያዝነው የሃያ አንደኛው ክ/ዘመን ልማታዊ መንግሥት ሳይሆን ወደ ታለፈው የሃኛው ክ/ዘመን የልማታዊ መንግሥት ሞዴል ነው። ኢህአዴግ የልማታዊ መንግሥት አመለካከቱን በሃያኛው ክፍለ ዘመን ላይ ተክሎ ወደ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የልማታዊ መንግሥት አመለካከት አልሸጋገርም ማለቱም ምክንያት አለው። የሀያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የልማታዊ መንግሥት ትንታኔ የኢኮኖሚ ልማትን ኢኮኖሚያዊ እድገትን (Economic Growth) ከማስመዝገብ በእጅጉ የሰፋ፣ ነፃ እና ፍትሃዊ ምርጫን ጨምሮ ለኢህአዴግ የማይመች ሰፋ ያለ ትርጉም ስለሚሰጠው ነው።

በመድረክ ውስጥ የተሰባሰቡት የፖለቲካ ድርጅቱች መሪዎች እና ታዋቂ ግለሰቦች ታህሣሥ 18/2001 በኢምፔሪያል ሆቴል በተደረገ ስብሰባ ላይ ጥናታዊ ፅሁፎች አቅርበዋል። ፅሁፍ ካቀረቡት መካከል ዶ/ር መራራ ጉዲና እና አቶ ገብሩ አስራት በኢህአዴግ አብዩትዊ ዲሞክራሲ የፖለቲካ ገፅታ ላይ የሰላ እና የተሚላ ትችት አቅርበዋል። የዶ/ር መራራ ጥናታዊ ጽሁፍ ትኩረት ሙሉ በሙሉ በኢህአዴግ አብዩታዊ ዲሞክራሲ የፖለቲካ ገጽታ ላይ ያተኮረ ነው። የአገራችንን የወቅቱን የኢኮኖሚ ሁኔታ በጽሁፋቸው ውስጥ አልዳሰሱትም። ስለ ኢህአዴግ የኢኮኖሚ አመለካከትና ስለ ልማታዊ መንግሥት ትንታኔው ባቀረቡት ሌላ ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ ዳሰሳ ያደረጉት አቶ ገብሩ አስራት ናቸው። አቶ ገብሩ ኢህአዴግ እየተጓዘበት ያለውን የኢኮኖሚ አቅጣጫ ዋና ዋና ችግሮች በመጠቀም ፍትሃዊነት የጐደለው ነው በማለት በትክክል አስቀምጠውታል። ይሁንና ከኢኮኖሚ ፍልስፍና አንጻር ለኢህአዴግ ኢኮኖሚያዊ አመለካከት በጥናታዊ ጽሁፋቸው ውስጥ አማራጭ አላቀረቡም። በቅርቡ የተከበሩ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ ከቪኦኤ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ የመድረኩ ስብስብ ዋንኛ ምሶሶዎች ሊበራል ዲሞክራሲና የብሄር ፌደራሊዝም ናቸው ብለዋል። ሊበራል ዲሞክራሲ ከወል መብት ይልቅ ለግለሰብ መብት ቅድሚያ የሚሰጥ ፍልስፍና ነው። የብሄር ፌደራሊዝም ደግሞ ለውል መብት ቅድሚያ የሚሰጥ ነው። ለምሳሌ የሊበራል ዲሞክራሲ የኢኮኖሚ ፍልስፍና መሬት የግል ንብረት እንዲሆን፣ እንዲሸጥ እንዲለወጥ የሚፈቅድ ነው። የብሄር ፌደራሊዝም ደግሞ መሬት የሕዝብ ወይም የመንግሥት ሀብት ሆኖ እንዲቆይ ወይም ባጭሩ በወል ይዞታ ስር እንዲካተት የሚጠይቅ ነው። በብሄር ፌደራሊዝም አመለካከት መሬት የግል ሀብት ሊሆን አይችልም። ለዚህም ነው በይዘት የኢህአዴግ እና የመድረክ ስብስብ የፖለቲካ ድርጅቶች የኢኮኖሚ ፍልስፍና በመሠረታዊ ይዘቱ ልዩነት የለውም ለማለት የሚያስደፍረው።

ኢህአዴግ በተለይ ከ1997 ምርጫ ወዲህ እያራመደ የሚገኘው የልማታዊ መንግስት ፖለቲካ ኢኮኖሚ ቀደም ሲል እንደተገለፀው ከአብዮትዊ ዲሞክራሲ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ፍልስና ጋር በተወሰነ መልኩ የሚመሳሰል ነው። እንደመሆኑም አንደኛው መለያ ጠባዩ ከፓለቲካ ተሃድሶ (Political reform) ወይም የፖለቲካውን ምህዳር ከማስፋት እና ዲሞክራሲያዊ ከማድረግ ይልቅ፣ የፖለቲካውን ምህዳር አፍኖ በመቆጣጠር የኢኮኖሚ እድገት ያስገኛሉ ተብለው በሚታሰቡ ፖሊሲዎች አማካይነት በኢኮኖሚው ውስጥ የመንግስትን ቀጥተኛ ጣልቃ ገብነት(Interventionist) በማጠናከር ለኢኮኖሚ እድገት (economic growth) ልዩ ትኩረት የሚሰጥ ነው። የኢህአዴግ ልማታዊ መንግስት ሌላው መለያ ጠባይ መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ ሊኖረው ከሚገባው የገበያ ስርዓቱን እንዳይዛባ በማድረግ ከሚጫወተው የተቆጣጣሪነት ሚና እና በልዩ ልዩ ፖሊሲዎች በመጠቀም ሊጫወት ከሚገባው የገቢ አደላዳይነት ሚናው ዘሎ በእጅ አዙር በገበያው ውስጥ ተዋናይ ሁኖ የመሳተፍ ዝንባሌ ነው። ይህም ማለት ከኢኮኖሚ ተቆጣጣሪነት ይልቅ የኢኮኖሚ አልሚነት ሚናው ልቆ እንዲገኝ በማድረግ መንግስት የኮርፖሬት ባህሪ እንዲላበስ ያደርገዋል። ይህ ዝንባሌ ከመደበኛ የልማታዊ መንግሥት ጠባይ ለየት ያለ መልክ ይሰጠዋል። በፖለቲካው ዘርፍ መንግሥት ዲሞክራሲያዊ በሆነ አሠራር የማይመራ እስከሆነ ድረስ፣ በኢኮኖሚው መስክ የመንግስታዊ ኮርፖሬቲዝም ዝንባሌ በግሉ የኢኮኖሚ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ጎጅ ተጽእኖ ማሳደሩ የማይቀር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ዲሞክራሲያዊ ያልሆነ የልማታዊ መንግስት አመለካከት ኢህአዴግ ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ ከሚያራምደው የአብዩታዊ ዲሞክራሲ ፍልስፍና ጋር ሲነጻጻር ብዙም የማይርቅ እና የሚደጋገፍ ነው። በኢህአዴግ በኩልም የተመረጠበት ያንኑ የሙጥኝ ብሎ የያዘውን የቀዬ አመለካከቱን የማያናጋበት በመሆኑ ነው።

የሚመሩትን ፓርቲ እና መንግሥት በመወከል ሳይሆን በግላቸው ጠቅላይ ሚ/ር መለስ ዜናዊ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በነሐሴ 2006 በእንግሊዝ አገር ማንቸስተር ከተማ ላይ ለተደረገ ስብሰባ ስለልማታዊ መንግሥት ጥናታዊ ጽሁፍ ማቅረባቸው ይታወሳል። ከጽሁፉ ውስጥ ለትንታኔ የሚያስፈልገኝን ለመጥቀስ ዳድቶኝ ነበር። ግና በጽሁፉ ሽፋን ላይ "ለጥቅስ መጠቀም አይቻልም!" አራት ነጥብ የሚል መመሪያ አለበት። "አለንጋ እስኪመጣ በክርን ያዝግሙብኝ" የተሰኘውን ባህላዊ አነጋገር ተግባራዊነት ላለመጋበዝ መመሪያውን ማክበሩ አስፈላጊ በመሆኑ

በቀጥታ ከመጥቀስ እቆጠባለሁ። ጠቅላይ ሚ/ሩ በጽሁፋቸው ውስጥ በግል የሚያምኑባቸውን አመለካከቶች ዘርዘር አድርገው አቅርበዋል። በታዳጊ አገሮች በመሠረታዊ የፖሊሲ ጉዳዬች ዙሪያ በፖለቲከኞች እና በህዝቡ መሃል ሙሉ መግባባት ሊደረስ የሚችልበት ሁኔታ መገኘቱ አጠራጣሪ መሆኑን፣ አንድ መንግሥት ዲሞክራሲያዊም ልማታዊም ሁኖ ብቅ ሊል የሚችለው ገኖ በወጣ ፓርቲ (Dominant party) ወይም ገኖ ቢወጣ የዲሞክራሲ ሃይሎች ጥምረት (Dominant Coalition democracy) አማካይነት መሆኑን፣ ደሃ በሆኑ ታዳጊ አገሮች ልማታዊ መንግሥት የተፋጠነ የኢኮኖሚ ልማት እና የተረጋጋ ዲሞክራሲ ተነጣጥለው ሊታዩ የማይገባቸው ስለመሆኑ፣ በመጨረሻም በድሃ አገሮች የተረጋጋ ዲሞክራሲ እድል እውን ሊሆን የሚችለው ከልማታዊ መንግሥት ማቆጥቆጥ እና ከሱጋር ተያይዞ መገኘት ከሚገባው የተፋጠነ ልማት ጋር በተሣሠረ ሁኔታ (as a package) መሆኑን አብራርተዋል። ከነዚህ እሳቤዎችም በመነሳት ለልማታዊ መንግሥት የሚያመች ሁኔታ በሌለበት የተረጋጋ ዲሞክራሲ ሊኖር ይችላል ብሎ መጠበቅ ዘበት እንደሆነ በትንታኔያቸው አስገንዝበዋል። አያይዘውም ከሁለተኛው አለም ጦርነት ማብቂያ ጀምሮ ጃፓን እስካሁን ድረስ ከስልጣን ባልወረደው የሊብራል ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ መሪነት ተደናቂ እና አፋጣኝ የኢኰኖሚ ልማት እና እድገት እንደተቀዳጀች በማብራራት ፅፈዋል። የኢኰኖሚ ልማትና እድገትን ለማስገኘት ጐልቶ የወጣ ፓርቲ (Dominant party) መሪነት አስፈላጊ እንደሆነ፣ ሃገራችንም ከዚህ ትምህርት መቅሰም እንደሚኖርባት በማብራራት ፅፈዋል።

ከ1950 - እስከ 1970 ድረስ ታይዋንና ደቡብ ኰሪያ በአምባገነናዊ የአንድ ፓርቲ አገዛዝ ስር ወድቀው በነበረበት ጊዜ ከፍተኛ የኢኰኖሚ እድገት እና እምርታ እንዳስመዘገቡ የታወቀ መሆኑንም ጠቅሰዋል። ከ1997 ምርጫ በኂላ ደግሞ ፈጣን የኢኰኖሚ ልማት ለማስገኘት የቻይና የልማት ሞዴል በኢህአዴግ መጠቀሱ እየተዘወተረ መጥቷል። ይህ ሁሉ ከተባለ በኂላ ጠቅላይ ሚ/ር ስለልማታዊ መንግሥት ማንቸስተር ላይ ባቀረቡት ጥናታዊ ፅሁፍ ለኢትዮጵያ ተመራጭ የሚሆነው የጃፓንን ሞዴል መሠረት ያደረገው የዲሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግሥት እንደሆነ፣ ኢህአዴግ ያለምንም ስጋት ብዙሃኑን ገበሬ ከጀርባው በማሰለፍ እንደ ጃፓኑ ሊብራል ዲሞክራቲክ ፓርቲ በነፃ ምርጫ ለተከታታይ ዓመታት ለማሸነፍ ይችላል ብለው ተንብየዋል። ምርጫው ነፃ መሆኑ ይረጋገጥ እንጅ በነፃና እና ትክክለኛ ምርጫ (Free and Fair election) ኢህአዴግ የማሸነፍ እድል ቢገጥመው በፀጋ መቀበል ትክክል ነው። ችግሩ በፅሁፋቸው ውስጥ አትኩረው ያሰመሩበት ጐልቶ የወጣ ፓርቲ (Dominant Party) ዲሞክራሲያዊ ባልሆነ ሁኔታ እንዲቀጥል ከተደረገ እንደበፊቶቹ ምርጫዎች መጭውም ምርጫ በቅድሚያ የከሸፈ ሊሆን ይችላል የሚል ጠንካራ ስጋት መኖሩ ነው። የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥናታዊ ፅሁፍ ከሚያራምዳቸው ሃሳቦች ጋር መስማት የማይቻለው በኢኰኖሚ መስክ በዲሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግሥት አስፈላጊነት ላይ ሳይሆን፣ በዲሞክራስያዊ መንግሥት ትርጉም እና ተግባራዊ ክንዋኔ ይዘት ላይ ነው።

ወደ ልማታዊ መንግሥት ኢኰኖሚያዊ ይዘት ስንመለስ ኢህአዴግ ወይም ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ ስለልማታዊ መንግሥት ሲያወሱ ስለ 20ኛው ክ/ዘመን ልማታዊ መንግሥት እየተናገሩ መሆኑ ግልፅ ነው። ስለሃያ አንደኛው ልማታዊ መንግሥት ለማውራት የሃገሪቱ የእድገት ደረጃ አይፈቅድም። የ21ኛውን ክፍለ ዘመን ልማታዊ መንግሥት ከ20ኛው ክፍለ ዘመን ልማታዊ መንግሥት የሚለየው ሚናቸው የተለያየ በመሆኑ ነው። የሃያኛው ክፍለ ዘመን ልማታዊ መንግሥት ባለሃብቶች ወደ ውጭ የሚላክ ተጨማሪ የኢንዱስትሪ ምርት ለማምረት እንዲችሉ አቅማቸውን በመገንባት ረገድ ማገዝ ነበር። በአንፃሩ የ21ኛው ክፍለ ዘመን ልማታዊ መንግሥት ዓይነተኛ ጠባይ የማምረት አቅምን በማገዝ ላይ ያተኰረ ሳይሆን የቴክኒዎሎጅ ውድድርን ለማሸነፍ የሚያግዘውን አዲስ አስተሳሰብ እና መረጃ (‘bit-driven growth’ growth driven by ideas and information) በማጠናቀር፣ተቋማዊ ለውጥን በማስገኘት እና ለዚህ ሁሉ ቁልፍ የሆነውን የሰለጠነ የሰው ሃይል በማፍራት ረገድ ተገቢውን የአመራር ሚና መጫወት ነው። ኢህአዴግ የሚያወሳው ስለ ሃያኛው ክ/ዘመን ልማታዊ መንግሥት ከሆነ ደግሞ መንግሥት ሃገራዊ እይታ ካለው ብሄራዊ ከበርቴ ጋር ግንባር መፍጠርን የሚጠይቅ ነው። (Evans 2007: 21-27)

በባህላችን ሲተርት "ንጉሥን መንቀፍ ነብር ማቀፍ" ይባላል። ይሁንና በአሁኑ ጊዜ ዘመኑ ሃሳብ በነፃ የሚገለፅበት የዲሞክራሲ ዘመን ነው የሚል አዋጅ ስላለ ከዚህ ቀጥሎ የቀረበው ነቀፌታ በዚሁ አዋጅ መሠረት የቀረበ ነው። ኢህአዴግ በተፈጥሮው የኔ ናቸው ከሚላቸው ጥቂት ባለሃብቶች ውጭ ብሄራዊ እይታ ያላቸውን ሃገራዊ ከበርቴዎች መኰትኰት ላይ ችግር አለበት። የሀገራዊ ብሄረተኝነት አራማጅ ሃይል የዲሞክራሲ እንቅስቃሴ ማህበራዊ መሠረት ሊሆን ይችላል የሚል ስጋት ስለአለው ሊደግፈው አይሻም። ለዚህም ነው ኢህአዴግ ከሱ ተፅእኖ ነፃ በሆነ ሁኔታ ከሚንቀሳቀሱ ብሄራዊ ከበርቴዎች ይልቅ ለቻይና፣ ለህንድ እና ለሱዳን ባለሃብቶች ኢትዮጵያ ውስጥ መንቀሳቀስ ሁኔታዎችን ማመቻቸት የሚቀለው። እርግጥ የውጭ ባለሃብቶች የሃገርን ልማት በሚያግዙ የምርት እና የአገልግሎት ዘርፎች ለመስራት የራሳቸውን የውጭ ፋይናንስ፣ እውቀት እና የአሠራር ልምድ ይዘው በመምጣት በሃገር ውስጥ መስራታቸው የሚደገፍ ነው። ይሁንና በውጭ ባለሃብትነት ታፔላ በሃገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱበትን ገንዘብ ካሃገር ውስጥ ባንኰች በመበደር የሚያሚሉ፣ አዲስ እሴት በማይፈጥሩ በምግብ ቤቶች፣ በክሊኒኰች አልፎ ተርፎ በእህል ንግድ ተሰማርተው የሚታዩ ከሆነ፣ የሃገሬውን ባለሃብት ከመሻማት ውጭ ለሀገር ልማት ጠቀሜታ ያለው አስተዋፅኦ አያበረክቱም። ስለሆነም የኢህአዴግ ልማታዊ መንግሥት መፈክር ቢበዛ በአየር ላይ የተንጠለጠለ አለዚያም ራሱ አደራጅቶ ባለሃብት

ለሚያደርጋቸው እና በሱ ቁጥጥር ስር ላሉ "ባለሃብቶች" ሁኔታዎችን ከማመቻቸት የሚዘል አይሆንም፡፡

ይህን የልማታዊ መንግሥት ርእስ ከመቋጨታችን በፊት አንድ ግልፅ ሊሆን የሚገባው ተጨማሪ ጉዳይ አለ፡፡ የመጀመሪያ ዙር የኤሽያ ነብሮች ይባሉ ከነበሩት መካከል ጃፓንን ተተን ታይዋንና ደቡብ ኮሪያ፣ የሁለተኛው ዙር የእስያ ነብሮች የተሰኙት ታይላንድ ሲንጋፖር፣ ማሊጂያና ኢንዶኒጂያ በአንድ ፓርቲ አምባገነናዊ አመራር ስር ሁነው የኢኮኖሚ ልማት አስገኝተዋል፡፡ በቅርቡ ደግሞ ቻይና እና ቪየትናም በለየለት ኮምኒስታዊ የአንድ ፓርቲ ፈላጭ ቆራጭነት ውስጥ ወድቀው የኢኮኖሚ ልማት አስመዝግበዋል፡፡ ከ1950ዎቹ ጀምሮ እስከ 1990ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ ድረስ የኢኮኖሚ ልማት (Economic Development) የተሰኘው ፅንሰሃሳብ ትርጉም ጠበብ ባለ መልኩ ብቻ ነበር የሚተረጐመው፡፡ ይኸውም በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ከአንድ አገር ህዝብ ነዋሪ መካከል አብዛኛውን ከድህነት አረንቋ በማላቀቅ መሠረታዊ የምግብ የመጠለያ እና የሥራ እድል ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል ተደርጐ ነበር የሚወሰደው፡፡ ይህም ሂደት በተፋጠነ የኢኮኖሚ እድገት (Economic growth) የታገዘ ነበር፡፡ ይኽ መመዘኛ በሁለቱም ማለትም በካፒታሊስትም ሆነ በሶሺያሊስቱ ስርዓት የተሟላ ነበር፡፡ ከ1990ዎቹ አጋማሽ ወዲህ ግን የኢኮኖሚ ልማት አተረጓጎም ተለውጧል፡፡ በተፋጠነ የኢኮኖሚ እድገት አማካይነት ድህነትን ማስወገድ ልማትን በተሟላ መልኩ አያስገኝም፡፡ ከዚህ ትርጉሙ በተጨማሪ የኢኮኖሚ ልማት የግለሰብ የፖለቲካ እና የሲቪል መብቶች እና ደህንነት መከበርን (civil & political rights and personal security) የብሄራዊ ሃብት ክፍፍል ሚዛናዊነትን (distributive equity) ማህበራዊ ፍትዓን (social justice) የአካባቢ ሁኔታ በዘላቂ ሁኔታ መጠበቅ (Environmnetal sustainability)የፆታዎች እኩልነት መከበር (gender equality) ሙሰናን ትርጉም ባለው ሁኔታ መዋጋት፣ የመንግሥት አካላትን አሠራር ማስተካከል (Overhauling governance) እና ፖለቲካን ዲሞክራሲያዊ ማድረግን የሚያጠቃልል ሁኖአል፡፡ የተዋጣለት ዲሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግሥት ለመሸጋገር በሶስት ዘርፎች ማለትም

ሀ/ በመንግሥት ዘርፍ

ለ/ በፖለቲካ ፓርቲ ዘርፍ

ሐ/ በሲቪል ማህበረሰብ ዘንድ ተቋማዊ ግንባታ (Institution Building) ማድረግን ይጠይቃል፡፡ (Mkandawire 2001:25(3) 289-31)(Weiss 2000: 23-28)

የልማት አራማጅ ሃይል እንዲሆን የሚጠበቀውን መንግሥትን በተመለከተ፣ በአገር ውስጥ ካሉ ኪራይ ሰብሳቢ ክፍሎች ከዓለም አቀፍ የፋይናንስና የእርዳታ ሰጪ ተቋሞች ተጽእኖ ነፃ መሆን (Autonomus) እና በነፃነት ከተደራጁ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር የተቆራኘ ትስስር (Embeddedness) እንዲኖረው የግድ ይላል፡፡ በመንግሥት ተቋማት የሰው ሃይል ምደባ ችሎታን/ብቀትን መሠረት ያደረገ (Meritocracy) ሊሆን ይገባል፡፡ (Evans 2007)

ፖለቲካ ፓርቲዎች በተመለከተ ለፖለቲካዊ አስተሳሰብ እድገት እና ለዲሞክራሲያዊ ፖለቲካ ማበብ ወሳኝ ናቸው፡፡ የልማት አቅጣጫን በመንደፍ ረገድ ግንባር ቀደም ሚና የሚጫወቱ ፖለቲካ ፓርቲዎች ናቸው፡፡ ይሁንና ይህን ሚናቸውን በሚገባ ለመወጣት በዲሞክራሲያዊ መንገድ ተቋማዊ አቅማቸውን መገንባት አለባቸው፡፡ የግለሰብ እና የቡድን አምባገነናዊ አሠራር እንዳያቆጠቁጥ መከላከል አለባቸው፡፡ በመንግሥት ላይ ካላቸው ጥገኝነት መላቀቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነዚህን የተጠቀሱ መመዘኛዎች ሊያሟሉ የሚችሉት በጥቅማጥቅም ፖለቲካ (Clientelistic/patronage politics) ማለትም የፓርቲ አባልነት መመዘኛ ሃይማኖት፣ ጐሣ፣ ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅም ወዘተ… ሳይሆን በሃገራዊ ራዕይ ላይ የተገነባ መሆን ይጠበቅበታል ማለት ነው፡፡ (Randall 2007)

በአጠቃላይ አነጋገር ኢኮኖሚያዊ ነክ ጉዳዬችን በተመለከተ በኢህአዴግ እና የለዘብተኛ ዲሞክራሲን እና የሶሽያል ዲሞክራሲ ቅይጥ የኢኮኖሚ አመለካከት በሚያራምደው አንድነት ፓርቲ መካከል ልዩነት አለ፡፡ አንድነት ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት በፖለቲካ ተሃድሶ ያልተደገፈ ማናቸውም ዓይነት የኢኮኖሚ ልማት ቀመር ግቡን ይመታል የሚል እምነት የለውም፡፡ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ልማታዊ መንግሥቱ ዲሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግሥት እስካልሆነ ድረስ ዘላቂ ልማት ሊኖር አይችልም የሚል አመለካከት አለው፡፡ በመድረክ ውስጥ የተሰባሰቡት ድርጅቶች ስለኢህአዲግ ልማታዊ መንግሥት የሚኖራቸው አመለካከት ወደፊት በውይይት መብራራት ይጠበቅበታል፡፡ የመሬት ፖሊሲን በተመለከተ ግን ኢህአዴግ እና የመድረክ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተመሳሳይ አቋም ሲኖራቸው፣ የአንድነት ፓርቲ አቋም የተለየ ነው፡፡

ኢህአዴግ እና አንድነት ስለ ልማት ያላቸው አመለካከትም ተጻራሪ ነው፡፡ ከላይ ለማመልከት እንደተሞከረው ኢህአዴግ በይፋ ባይናገረውም በፖለቲካ ነጻነት ያልተደገፈ የኢኮኖሚ ልማት ማስገኘት ይቻላል ብሎ ያምናል፡፡ ቀደም ሲል በደቡብ ኮሪያና ታይዋን አሁን ደግሞ ከቻይና ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር እንደሠራ ቢታይም፣ የአንድነት ፓርቲ ኢትዮጵያ ከደቡብ ኮሪያና ታይዋን እንዲሁም ከቻይና እና ቪየትናም ጋር

የምትለያይባቸው በርከት ያሉ ሁኔታዎች እንዳሉአቸው በመገንዘብ፣ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ግን ይህ አካሄድ ሊሠራ አይችልም ብሎ ያምናል። አንዱን ዋንኛ የሆነውን ልዩነት እንውሰድ። ደቡብ ኰሪያም ሆነ ታይዋን ሁለቱም ከአንዳንድ ብሄር በላይ የላቸውም። ቻይናም ቢሆን ከ90 በመቶ በላይ የሃን ብሄር ያለባት አገር ናት። የቪየትናምም ሁኔታ ተመሳሳይ ነው። አራቱም አገሮች ፖለቲካቸው የተረጋጋ እና በብሄረሰብ ፖለቲካ የማይናወጥ ነው። መላ ትኩረታቸው በልማት ላይ በመሆኑ በአጭር ጊዜ በኢኮኖሚ ልማት እና እድገት ሊገፋ ቻሉ። ከጥንት ጊዜም ጀምሮም ቢሆን በቻይና ፖለቲካ የማእከላዊ መንግስታዊ ስልጣንን የሚገፋ ወይም የሚቀናቀን ክልላዊ ሃይል አልታየም። በተጠቀሱት አገሮች የሀገር አንድነት ሊጠበቅ በሚችልበት የፖለቲካ ቀመርም ሆነ ዘላቂነት ያለው የኢኰኖሚ ልማት የሚገኝበትን ስልት በተመለከተ በፖለቲካ ልሂቃን ዙሪያ የአመለካከት ልዩነት የለም። በኢትዮጵያ ፖለቲካ ግን ከጥንት ጀምሮ የተለያዩ ሃገራዊ ሥልጣን ይገባናል የሚሉ ማእከሎች በመኖራቸው፣ ማእከላዊ መንግስታዊ ስልጣንን ያለመቀበል፣ የመጋፋት እና የመፎካከር ባህል የተለመደ ነው። አሁንም ቢሆን በአገራችን ዋና ዋና ጉዳዬች ዙሪያ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ልሂቃን አንድ ወጥ አመለካከት የላቸውም። የላቸውም ብቻ ሳይሆን የሚያራምዱአቸው አመለካከቶች ተጻራሪዎች ናቸው። የዚህ ዓይነት ሁኔታ መኖር ደግሞ የፖለቲካ አለመረጋጋትን በማስፈን ለልማት ጠንቅ ይሆናል።

በኢኰኖሚው መስክ መሬት በመንግስት ብቸኛ አዛኘርነት ስር መሆኑን እስከቀጠለ ድረስ፣ የኢኮኖሚ መገልገያ (Factor of production) መሆን ሲገባው የፖለቲካ መሳሪያ መሆኑን እንደቀጠለ ነው። የኢትዮጵያ ገበሬ ነጻ እና እንደማናቸውም ሰብዓዊ ፍጡር ለኢኮኖሚ ጥቅሙ የሚቆም መሆኑ ተቀባይነት ባለማግኘቱ ለፖለቲካ መጠቀሚያ ሲባል በመንግስት ሞግዚትነት ስር እንዲቀጥል በመደረጉ በነፃነት በምርቱ ሂደት ላይ ለመወሰን ያለው መብቱ ተነጥቋል። የበሬ ግንባር እያከለች የመጣችው የገበሬ ማሳ በገበያ ሕግ መሠረት ሰፋ ወደአለ እና ዘመናዊ የእርሻ ተክኖሎጂን በተገቢ ሁኔታ ሊያስተናግድ ወደ ሚችል ይዞታ ለማሰባሰብ እስካልተቻለ ድረስ፣ ረዘም ላለ ጊዜ ተሰጠ በሚባል የይዞታ ሰርተፊኬት አማካኝነት ገበሬውን በመሸንገል የገጠር መሬትን ከመንግሥት ይዞታነት ለማላቀቅ እስካልተቻለ ድረስ፣ ሃገራችን ከርሃብ እና ከኢኮኖሚ ኋላቀርነት ትላቀቃለች ማለት ዘበት ነው።

የመሬት ይዞታ ፖሊሲን ጉዳይ ይበልጥ አንገብጋቢ የሚያደርገው ዲሞክራሲያዊም ሆኑ ዲሞክራሲያዊ ያልሆኑ ልማታዊ መንግሥቶች የገቢ ንግድ እቃዎችን የሚተካ በወጪ ንግድ ላይ የተመሠረተ የኢንዱስትሪ ልማት (Import substitution - cum - Export led Industerialization) መሠረት የጣሉት በቅድሚያ ለእርሻው ዘርፍ ምርተማነት እና ገቢ መጨመር የሚያመች የመሬት ይዞታ ፖሊሲ ቀይሰው ተግባራዊ ለማድረግ በመቻላቸው ነው። አለ ሰፊ የሃገር ውስጥ ገበያ የኢትንዱስትሪ ልማት የሚታሰብ አይደለም። የረጋ (inactive) ሳይሆን ሁኔታዎች ሲቀየሩ አብሮ የሚቀየር (dynamic) እና በምርታማነት እድገት ላይ የተዋቀረ፣ አዳጊ ገቢው በዘርፉ በስፋት የተሰራጨ የእርሻ ዘርፍ ለተፋጠነ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማት የሃገር ውስጥ ገበያ መሠረት ነው። ከውጭ ውድድር በመንግሥት የሚከለሉ ታዳጊ ኢንዱስትሪዎች የቴክኒዎሎጂ ውድድርን ለመቋቋም (catching up with the techneological frontier) የሚያስችላቸውን መጠኑ በሚጨምርበት ወቅት አዋጭነቱ የሚጨምር የማምረት አቅም (economies of scale) የሚያካብቱቱ በሰፊ የሃገር ውስጥ ገበያ የታገዙ እንደሆነ ብቻ ነው። ሰፊ የሃገር ውስጥ ገበያ ሊፈጠር የሚችለው ደግሞ የእርሻውን ዘርፍ ምርታማ በማድረግ ብቻ ነው (Grabowski 1994, pp420-421)። በሃገራችን ይህን እውን ለማድረግ በተለይ መንግሥት በመሬት ባለቤትነት እና ተያይዞ በሚመጣው የአጠቃቀም ፖሊሲን በተመለከተ፣ በአጠቃላይ መሬትን የኢኮኖሚ ሣይሆን የፖለቲካ መሣሪያ ያደረገው የአሁኑ ፖሊሲ መለወጥ ያስፈልገዋል። በወል ንብረትነት የተያዘው የአርብቶ አደሮች የግጦሽ የመሬት ይዞታም ወደ ዘመናዊ አሰራር ሊሸጋገር የሚችልበት ግልጽ የሆነ ፖሊሲም አይታይም። እስካሁን ያለው መረጃ በመሬት ጥያቄ ላይ በመድረክ ውስጥ የተሰባሰቡ የፖለቲካ ድርጅቶች እና ግለሰቦች አመለካከት ከአንድነት ይልቅ ከኢሕአዴግ አቋም ጋር የሚመሳሰል ነው። ልዩነት አለ ከተባለ ማብራሪያ የሚያስፈልገው ቁልፍ ጥያቄ ነው።

የአንድነት ፓርቲ የፖለቲካ አመለካከት በለዘብተኛ ዲሞክራሲ የፖለቲካ ፍልስፍና ላይ የተመሠረተ ነው። የግለሰብ ዜጋ የመብት አድማስ እና የመንግሥት ስልጣን ገደብ በህዝብ ያለተገደበ ተሳትፎ በሚረቀቅ፣ ከማንም የፖለቲካ ፓርቲ ተጽእኖ ነጻ ሁኖ በሚዘጋጅ ህገመንግስት አማካይነት ዳርድንበር ሊበጅላቸው ይገባል የሚል እምነት የሚያራምድ ነው። በዚህም ላይ በመመስረት የአንድነት ፓርቲ በኢትዮጵያ ለእውነተኛ ዲሞክራሲያዊ እና ህገመንግስታዊ ስርዓት መስፈን በጽኑ የቆመ ነው። የአንድነት ፓርቲ የፖለቲካ አመለካከት በኢትዮጵያ የይስሙላ ሳይሆን የሃቀኛ የብዙሃን ፓርቲ ስርዓትን የሚደግፍ ነው። አንድነት ፓርቲ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሊረጋጋ የሚችለው፣ እውነተኛ የዲሞክራሲያዊ ፖለቲካ ስርዓት በሃገራችን ሊሰፍን የሚችለው የነጻ እና የዲሞክራሲያዊ ተቋሞች መቋቋም እና መጠናከር ሲቀድም ነው ብሎ ያምናል።

ከመንግስት አወቃቀር በተጨማሪ የአንድነት ሃይሎች የኢትዮጵያ የፖለቲካ ስርዓት እይታ ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ እስካሁን ከሚያራምደው አመለካከት ጋር የሚጣጣም አይደለም። ለምሳሌ ያህል በኢትዮጵያ ሁኔታ በእድገት ወደ ኋላ በቀሩ አገሮች የፖለቲካ ፓርቲዎች መሠረት ብሄረሰብ/ቋንቋ መሆኑ ጠቃሚ ነው የሚል እምነት የላቸውም። ከዚህ መመዘኛ ይልቅ የፓርቲዎች መሠረት የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ

ፍልስፍና ቢሆን፣ በሃገራችን የሰፈነው ጎጅ ጎኑ አመዝኖ የሚገኘው የጽንፈኝነት ፖለቲካ (politics of extrimism) ጠቃሚ ጎኑ ወደ ሚያመዝነው የመሃል ፖለቲካ (centrist politics) በመሸጋገር ለሃገሪቱ ፖለቲካ መረጋጋት አመች ሁኔታ ይፈጥራል የሚል እምነት አላቸው።

በህገ መንግሥቱ ውስጥ ቀደም ሲል ከተጠቀሱት አወዛጋቢ አንቀፆች በተጨማሪ የመንግሥት ስልጣን ክፍፍል መርሆን እና የእርስ በርስ ቁጥጥር በተመለከተ፣ የመድበለ ፓርቲ ስርዓት የሚረጋገጥበት ሁኔታን በተመለከተ፣ የምርጫ ስርዓትን በተመለከተ፣ የመሬት ጉዳይን በተመለከተ ህገ መንግሥታዊ ማሻሻያ የሚቀርብበትን ሁኔታ በተመለከተ በምርጫ በጋራ እንቀርባለን የሚሉ ፓርቲዎች በቅድሚያ ተወያይተው አቋሞቻቸውን መፈተሽ እና ማቀራረብ ይጠበቅባቸዋል።

የሃገራችን ታሪክ ግንዛቤም ሁለቱን ጐራዎች ማለትም ብሄር-ዘለል አመለካከት ያላቸውን የፖለቲካ ፓርቲዎች በብሄር/ክልል ዙሪያ የሚያጠናን አመለካከት ካላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የፓርቲ ስብስቦች ጋር የማይስማሙበት ዐብይ የልዩነት ርእስ ነው። "የኢትዮጵያ ታሪክ የሚባለው የትግሬ እና የአማራ ታሪክ ነው፣ የኢትዮጵያ ባህል የሚባለውም የነሱ ነው። ከምኒሊክ በፊት ግዛታቸው ከትግሬ እና ከአማራው ክልል ያለፈ አልነበረም። ከዚያ ውጭ የሆነው ሕዝብ ነጻ ነበር። ኢትዮጵያ የወረራ ውጤት ናት። ታሪኳም ከመቶ አመት ያለፈ አይደለም። ኢትዮጵያ የምትባለው አገር በ19ኛው ምእተዓመት መገባደጃ ላይ ኢምፔርያሊስቶች አድበልብለውና አሽሞንሙነው የፈጠሯት አገር ናት"(Hollcom and Ibssa, 1990) የሚል ነው የክልላዊ ብሄረተኝነት የ'ታሪክ' ግንዛቤ። ከዶ/ር መራራ ጉዲና ውጭ ያሉት በመድረክ ስር የተሰባሰቡት የብሄረሰብ ድርጅቶች እና ታዋቂ ግለሰቦች የዚህ አመለካከት ተጋሪዎች ይመስላሉ።

> በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚችለው ትክክለኛው የኢትዮጵያ ታሪክ ግን ባጭሩ የሚከተለውን ይመስላል።
>
> እውነተኛው የኢትዮጵያ ታሪክ በስፋት ሲታይ እስከ ስድስት ሺህ ዓመት የሚደርስ፣ በጠባቡ (ከመንግሥት ምስረታ አንፃር) ሲታይ ደግሞ ከ2000-2500 ዓመታት የሚሆን ነው።(Baheru Zwede: 1992)

ዶ/ር ላጲሶ ዲሌቦ ከጻፉት የታሪክ መጽሃፍ ላይ የሚከተለው ታሪካዊ ጭብጥ ሰፍሮ ይገኛል።

> የግዛት ክልሉ እንደየጊዜው ሁኔታ በመጥበብና በመስፋት የተለዋዋጭነት ባህሪ ያሳዬ ቢሆንም፣ በኢትዮጵያ የተማከለ የአጼ መንግስት ያላቋረጠ የ2500 ዓመታት ያህል ታሪክ ያለው ነው። በዚህ የተማከለ የአጼ መንግስት አገናኝነት የኩሽ፣ የሴም፣ የአባይ ሰሃራዊና የኦሞቲክ የቋንቋ ቤተሰብ ተናጋሪዎች የሆኑት የኢትዮጵያ ሕዝቦች ረዥም ዘመናትን ያስቆጠረ የቋንቋ፣ የባህል፣ የአስተዳደር/ ፖለቲካ/ እና የኢኮኖሚ ግንኙነቶች ሲያደርጉ ኑረዋል። በነዚህ ሁሉ መስኮች በመወራረስ ለዛሬው ህልውናቸው ማንነትና ለተጠናከረ የአንድነት ስሜታቸው ገላጭ ባህሪ የሆነው ኢትዮጵያዊነት የተቋጠረው በሰሜን ኢትዮጵያ ከ2500 ዘመናት በፊት ሲሆን በደቡብ ኢትዮጵያ ደግሞ ከ700 ዓመታት በፊት እንደሆነ ተጨባጭ የታሪክ ማስረጃዎች ይመሰክራሉ። (ላጲሶ ዲሌቦ 1982)

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በርከት ያሉ ክንውኖች የተፈፀሙበት ከ13ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ 16ኛው ክፍለ ዘመን ያለው ጊዜ ነው። ይሄን ዘመን በማስመልከት የታሪክ ተመራማሪ የሆኑት ዶ/ር ባህሩ ዘውዴ ግንዛቤአቸውን ባጭሩ እንደሚከተለው አስቀምጠውታል።

> "ከአክሱም ዘመን ቀጥሎ ለአሁኒቷ ኢትዮጵያ ወሳኝነት ያለው የታሪክ ምእራፍ "የመካከለኛው ዘመን" ተብሎ የሚታወቀው ነው። ይህም ከ13ኛው ምእተዓመት መጨረሻ እስከ 16ኛ ምእተዓመት መጀመሪያ ያለውን ጊዜ ያጠቃልላል። በተለይም ግዛታዊ ቅርፅንና የብሄረሰቦችን ስርጭት በተመለከተ ይህ ዘመን ከአክሱም ዘመን በበለጠ ከአሁኒቱ ኢትዮጵያ የመመሳሰል ባህሪ አለው። የኢትዮጵያ ታሪክ የመቶ ዓመት ታሪክ ነው የሚሉ ወኖች ግን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ይህን ዘመን ማውሳት እምብዛም አይወዱም" (ባህሩ ዘውዴ 1984)።

ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ያለው ሁኔታ ይህንኑ ይበልጥ የሚያጠናክር ነው። ወርቅ በእሳት ይፈተናል እንደሚባለው፣ ከ13ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ዓመታት አንስቶ እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ድረስ የኢትዮጵያ ብሄረተኝነት በሶስት ታላላቅ ጦርነቶች ተፈትኖ ተጠናክሮ የወጣ ሃይል ሊሆን በቅቷል።

የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የተነሱ የእርስ በርስ ጦርነቶች እንደመሆናቸው በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ላይ የተቃጡ አልነበሩም። ከታሪክ እይታ አንፃር አጭር በሆነ የሰላሣ ዓመታት ጊዜ ውስጥ የተካሄደው፣ እጅግ አውዳሚ የነበረው ከሐረር ተነስቶ የቀድሞ ባህረነጋሽ ግዛት ይባል በነበረው እስከአሁኒቱ ኤርትራ ድረስ የዘለቀው እና በግራኝ መሃመድ የተመራው ጦርነት ዓላማ ኢትዮጵያን በእስልምና ስር አንድ አድርጐ ለመግዛት ነበር። ጦርነት የገጠሙት ተፋላሚዎችም የወቅቱ ዓለምአቀፍ እና ሃገር አቀፍ የሃይል አሰላለፍ እንዲፎካከሩ ያደረጉአቸው በኢትዮጵያ እስልምናና ክርስትና ዙሪያ የተደራጁት ሃገራዊ ብሄረተኝነቶች ነበሩ።

ሁለተኛው ጦርነት ከመጀመሪያው ጋር ሲነፃፀር ረዘም ላለ ጊዜ የተካሄደ ቢሆንም፣ ከመጀመሪያው ጋር የሚያመሳስለው የጦርነቱ አውድማ ሃገር አቀፍ ስርጭት የነበረው መሆኑ፣ ለሃገራዊ የበላይነት እንጅ ሃገራዊ ሉዓላዊነት ለማዳከም ወይም ለማጥፋት ያለመ አለመሆኑ ነው፡፡ በሌላ በኩል ከመጀመሪያው በተፎካካሪ ሃይማኖታዊ ብሄረተኝነቶች መካከል የተካኤደ አለመሆኑ ነው፡፡ በቆዬ የገባር ስሪት ላየ የተዋቀረ ባላባታዊ ግንኙነትን (Fedual relations) በሚወክለው ማእከላዊ መንግሥታዊ ስርዓትና በእኩዬሽ ግንኙት (Egaliterian Relations) ላይ በተዋቀረው የነገዳዊ እና የባህላዊ ግንኙነትን በሚወክለው የገዳ ስርዓት መካከል የተካሄደ መሆኑ ነው፡፡ ይህ ጦርነት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ የውጭ እጅ ያልገባበት ነው፡፡

ሶስተኛው እና በ19ኛው ክፍለ ዘመን መሠረሻ እና በ20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ የተከናወነው ጦርነት ከቀዳሚዎቹ ሁለቱ በይዘትም ሆነ በቅርፅ የሚለየው በኢትዮጵያ ብሄረተኝነት ላይ ብቻ ሳይሆን፣ የዚሁ ሀገራዊ የብሄረተኝነት መሠረት በሆነው በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ላይ የተቃጣ፣ ኢትዮጵያን ቅኝ ግዞት ለማድረግ በማለም የተካሄደ የወረራ ጦርነት በመሆኑ ነው፡፡ ለማናቸውም ሶስቱ ታላላቅ ጦርነቶች የተባሉት፡-

1ኛ/ ከአስራ ሶስተኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አንስቶ እስከ 15ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ በዘለቀው በኋላም የዚህ ተከታታይ ጦርነት ማሳረጊያ የነበረው የግራኝ መሃመድ ዘመቻ በኢትዮጵያ እስልምና እና ክርስትና ሃይማኖታዊ እና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች የነበሩት ጦርነት ነው፡፡

2ኛ/ በ13ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ ከደቡብ ቦረና እንደተነሳ የተዘገበው የኦሮሞ ህዝብ ፍልሰት እስከ 16ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ ከደቡብ ቦረና ቆላማ አካባቢዎች አላለፈም ነበር፡፡ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ሲደርስ ይህ በሃይል የታጀበ የማጥቃት ዘመቻ በደቡብ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ ደቡብ ምእራብ እና መሃል ኢትዮጵያ ካሉ በርካታ ጎሳዎች እና ከማእከላዊው የንጉሰ ነገሥት መንግሥት ሠራዊት ጋር እየተጋጨ እስከ 18ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ ወደ ዘለቀ ተከታታይ እና ቁጥር ስፍር የሌለው ጦርነት አመራ፡፡ ይህ ክስተት በቁጥር አንድ ከተጠቀሰው የሃይማኖታዊ ጦርነት ውጤት ጋር በቅርብ የተቆራኘ ነው፡፡ የሰላሣ ዓመቱ ሃይማኖታዊ ጦርነት የማእከላዊውን መንግሥትንም ሆነ የደቡብ ምስራቅ እስላማዊ ግዛቶችን ወታደራዊ እና ኢኰኖሚያዊ ሃይል ክፉኛ አንኰታኩቶት ነበር፡፡ በ16ኛው መቶ ክ/ዘመን ጀምሮ የተከሰተው በጦርነት የታጀበው የኦሮሞ ፍልሰት ፈጣን ግስጋሴ የግራኝ ጦርነት ማብቃት በማእከላዊ መንግሥቱና በደቡብ ምስራቅ እስላማዊ ሱልጣኔቶች ላየ የደረሰውን የሃይል መዳከም ተንተርሶ የተከናወነ ነበር፡፡

3ኛ/ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ጀምሮ በአርባ ዓመታት ልዩነት ውስጥ የኢትዮጵያ አገራዊ ሉዓላዊነት በሚገለጽበት በኢትዮጵያ መንግሥት እና ህዝባዊ አንድነት ላይ የተካሄዱት ሁለት ታላላቅ የኢጣሊያ ወረራ ጦርነቶች ሶስተኛው የጦርነት ዙር ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡ (Bartinic & Niecho 1979)

በክልል ብሄረተኝነት እና በኢትዮጵያ ብሄረተኝነት ዙሪያ የተሰለፉትን ፖለቲከኞች የሚያወዛግባቸው ሁለተኛው ታሪካዊ ክስተት ነው፡፡ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አንስቶ እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ድረስ ወደ ሁለት መቶ ዓመት ለሚጠጋ ጊዜ አረማዊ እና ባህላዊ በነበረው የኦሮሞ የገዳ ስርዓት እና በዘውድ ምእክልና፣ በክርስትና እምነት እና በገባር ስርዓት ላይ በተመሠረተው አጼያዊ ስርዎ መንግሥት መካከል የተደረገው የተራዘመ ጦርነት በሁለቱም በኩል ጭካኔ የተሞላባቸው ድርጊቶች የተመዘገቡበት እንደነበር በታሪክ ተዘግቧል፡፡ የጦርነቱ ግንባር ከደቡብ እስከ ሰሜን፣ ከምስራቅ እስከ ምእራብ የተዘረጋ ነበር፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በተለይም ከ16ኛ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የጎላ ሚና ሲጫወቱ የቆዩት የኦሮሞው መሳፍንታዊ መሪዎች በማእከላዊው መንግሥት ውስጥ የበላይነትን ለመቀዳጀት እንጂ ማናቸውም ቢሆኑ ከማእከላዊ መንግሥት ለተነጠለ ክልላዊ መንግሥት ሲታገሉ አልታዩም የሚል የታሪክ ግንዛቤ ነው የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ ያለው፡፡ የኦሮሞ ልሂቃን (ኤሊቶች)ይህን የኢትዮጵያ ታሪክ በሚገባ ያውቁታል፡፡

ከጥንት ጀምሮ እስከ 19ኛው መቶ ክ/ዘመን ድረስ ኢትዮጵያ በሁለት ስርዓተ ግዛቶች የተከፈለች ነበረች፡፡ አንደኛው ሀገር-መንግሥት እየተባለ ይታወቅ የነበረው ሸዋን፣ ጐጃምን፣ አገው ምድርን በጌምድርን፣ ስሜንን፣ ላስትን የጁን አምባሰልን አማራ ሳይንትን በአጠቃላይ በንጉሡ ጊዜ ወሎ ክ/ሀገር እየተባለ የሚታወቀውን ከአፋር በመለስ ያለውን ግዛት፣ ትግሬን እና የባህረ ነጋሽ ግዛት እየተባለ ይታወቅ የነበረውን የአሁኒቱን ኤርትራን የሚያካትት ሲሆን፣ ሁለተኛው ምድረ ግብር በመባል የሚታወቀውን በደቡብ፣ በምእራብ እና አፋርን ጨምሮ በምስራቅ ኢትዮጵያ ያሉትን እስላማዊ እና አረማዊ ግዛቶች የሚያካትተው ነበር፡፡

በደቡብ በምእራብ እና በመሃል ኢትዮጵያ በገዳ ስርዓት ይመራ የነበረው የኦሮሞው የሉባ ተዋጊ ሃይል በአየለባቸው አካባቢዎች ቀደም ሲል ኦሮሚኛ የማይናገሩ ጐሣዎች ከጦርነቱ ፍፃሚ በኋላ ኦሮሚኛ ተናጋሪ ሊሆኑ በቅተዋል፡፡ ለምሳሌ የአርሲ ህዝብ ከኦሮሞ ነገዶች ፍልሰት በፊት ሐዲይኛ ተናጋሪ እንደነበር የጅማ፣ የሊቃ የጉማ የከፋ ሕዝብም እናርያ በመባል የሚታወቅ ህዝብ እንደነበር የታሪክ ምርምሮች ያስረዳሉ፡፡

ከጦርነቱ በኋላ የሁለቱም አካባቢ ጐሣዎች ኦሮምኛ ተጋሪ ሁነዋል። እስከ 17ኛው ክ/ዘመን መጨረሻ ድረስ በተደረጉ ጦርነቶች በደቡብ ኢትዮጵያ ኦሮምኛ ቋንቋን ያልተቀበሉ በርከት ያሉ ጎሣዎች በወቅቱ የኦሮምኛ አጠራር ተጠቃለው ሲዳማ በመባል ይታወቁ ነበር። የደቡብ ምስራቅ ግዛቶች ከ16ኛው ክፍለ ዘመን በፊት ማእከሉ ሃረር ከነበረው የወላስማ እስላማዊ ሱልጣኔት ንግድ እና የእስልምና ሃይማኖት ጋር የቆዩ ግንኙነት ስለነበራቸው፣ ደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ አካባቢዎችን ያላበሰው የኦሮሞ ህዝብ የቆየውን የገዳ ባህላዊ ልማዱን በመተው በምትኩ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ሆነ።

በሌላ በኩል ወደ ማእከላዊ እና ሰሜን ኢትዮጵያ ያቀናው እና እንደማእበል የነበረው የተለያዩ የኦሮሞ ነገዶች ፍልሰት በማእከላዊው የንጉሡ ነገሥታዊ መንግሥት ወታደራዊ ሃይል ሊገታ አልቻለም። በአንጻሩም የኦሮሞ ነገዶች በአባ ሙዳ እና የሉባ ትውልድ አዝማች ስር፣ በቁሮ እና በቁንዳላ የጦር ስርዓት የተደራጀው ተዋጊ ሃይል፣ ጭፍራ በተሰኘ የጦር ስልት በመጠቀም የአጼያዊ መንግስቱን የወታደራዊ ሃይል በተከታታይ እንዳጠቃው በታሪክ ተዘግቧል።

የኦሮሞው የፖለቲካ የበላይነት ጐንደር ላይ እውን ሆኖ በነበረበት በ17ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ከላይ እንደተጠቀሰው በአፄ እዩአስ የንግስና ዘመን የኦሮሞው የገዳ ስርዓት በዘውዱ ምእክልና ከተገነባው የፖለቲካ ስርዓት ጋር ተፃራሪ መሆኑ ቀርቶ ነበር። ጐንደር ላይ እንደተደረገው የማእከላዊ ኢትዮጵያ የኦሮሞ ነገዶች ሸዋ ላይ የገባር ስርዓቱን እና እንደየሰፈሩበት አካባቢ የኦርቶዶክስ ክርስትናን ወይም ወደ ደቡብ ምእራብ እና ምስራቅ የፈለሱትም እስልምናን በመቀበላቸው፣ ወደ ሰሜን ሂደው ከአማራው እና ትግሬው ጋር የተደባለቁት የኦሮሞ ነገዶች የኢትዮጵያ ዘውዳዊ ስርዓት አካል ሁነው ነበር። በዚህ ሁኔታ ነው የወሎ እና የየጁ የኦሮሞ መሳፍንቶች በዘመነ መሳፍንት ወቀት ለ70 ዓመታት ያህል የጐንደር ቤተመንግሥት እንደራሴ በመሆን በኢትዮጵያ ፖለቲካ የበላይነትን የተቀዳጁት።

በ1769 እንደ ጀመረ በሚነገርለት እና በ1855 በአጼ ቴዎድሮስ ስልጣን መያዝ* በተቋረጠው ዘመነ መሳፍንት እየተባለ በሚታወቀው ዘመን መቀመጫው ጎንደር ላይ የነበረውን የአጼያው ማእከላዊ መንግሥት በእንደራሴነት ያስተዳድሩት የነበሩት የወሎ እና የየጁ የወረሸህ የኦሮሞ መሳፍንቶች ነበሩ። ይህ የወረሽሆች ምስፍንና የተጀመረው የአባ ሰሩ ጓንጉል ልጅ በሆኑት በታላቁ ራስ አሊ ሲሆን፣ ከ70 ዓመታት በኋላ በአጼ ቴዎድሮስ በተሸነፉት በትንሹ ራስ አሊ ተጠናቀቀ።

የወሎ እና የየጁ ኦሮሞ መሳፍንቶች በጎንደር ቤተመንግሥት የፖለቲካ የበላይነት መያዝ የጀመሩት ከዘመነ መሳፍንት በፊት በዳግማዊ እያሱ (1730-1775) ዘመን ነው። ይህም የሆነው በዳግማዊ እያሱ ሚስት እና የወሎ ኦሮሞ ተወላጁ በሆነችው በውቢት አማካይነት ሲሆን፣ ከዳግማዊ እያሱ ሞት በኋላም በአባቱ ዙፋን ላይ በተተካው በእዩአስ ዘመን (1775-1790) በጎንደር ቤተ መንግሥት ውስጥ የኦሮምኛ ቋንቋ በስፋት ይነገር እንደነበር በታሪክ ተዘግቧል።

ቀደም ሲል እንደተገለፀው በሁለቱ ስርዓቶች መካከል የከረረ እና የተራዘመ ጦርነት የተካሄደው በሰሜን ምእራብ በተለይ ደግሞ በማእከላዊ ኢትዮጵያ ሸዋ ውስጥ ነው። ሸዋ ውስጥ በሁለቱም በኩል በርከት ያሉ የማጥቃትና የመከላከል ጦረነቶች ቢደረጉም ለዘለቄታው አሸናፊ እና ተሸናፊ ሊኖረው አልቻለም። ለመሸናነፍ ያልቻለ ሃይል ከመደባለቅ ውጭ አማራጭ አልነበረውም። የሆነውም ይህው ነው። በዚህ ታሪካዊ ወቅት የተከናወነው ግዙፍ የህዝብ ለህዝብ መሰጋሰግ እና መደባለቅ ከተራው ህዝብ ጀምሮ እስከ ቤተመንግሥቱ ድረስ የዘለቀ እንደነበር ከላይ ለማመልከት ተሞክሯል። (Bartinic & Niecho 1979)

ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አንስቶ ከመቶ ሃምሳ ዓመታት ላላነሰ ጊዜ በንጉሥ ነገሥታዊ መንግሥቱ ሠራዊት እና በኦሮሞው የገዳ ስርዓት ተዋጊዎች መካከል ስፍር ቁጥር የሌለው ጦርነት የተካሄደበት ምክንያት ነበረው። በኦሮሞው የገዳ ስርዓት መሠረት በየስምንት ዓመቱ የሚቀየረው አዲስ ትውልድ ሲተካ፣ አዲሱ የግዝረት ትውልድ የአስተዳደር ዘመኑን የሚጀምረው በህብረት ተገርዞ፣ አዲስ ሹም ተክቶ ሁሉም አብሮ በመዝመት አዲስ አካባቢ የማቅናት ባህላዊ ግዴታውን መወጣት ነበረበት። ይህ አካሄድ በዘውድ ምእክልና ላይ የተመሠረተውን መንግሥት፣ ሀገረ-መንግሥት ብሎ የሚቆጥራቸውን ግዛቶች የሚዳፈር፣ ምድረ ግብር በሚል ስያሜ የሚታወቁ ግዛቶቹን በመወረር ግብሩን የሚያሳጣ ስለነበር፣ አፄያዊው ስርዎ-መንግሥት ይህን ግፊት መዋጋቱ እንደ መንግሥታዊ ግዳጁ አድርጐ ይቆጥረው ነበር።

---

*አፄ ቴዎድሮስ ከመንገሳቸው በፊት የኢትዮጵያን የቀይ ባህር በሮች እና የባህረ ነጋሽን (ኤርትራን) ምስራቃዊ ቆላ ይቆጣጠሩ የነበሩት ቱርኮች በወቅቱ ግብፅንም ይቆጣጠሩ ነበር። ቱርኮች በግብፅ ላይ የሾሙት ከዲቭ እስማኤል ሱዳንንም በግብፅ ስር አድርጐ ይገዛ ነበር። አፄ ቴዎድሮስ ለንጉሣዊ ስልጣን ከመብቃታቸው በፊት የጐንደርን ቤተመንግሥት በበላይነት ይመሩ የነበሩት የወሎ እና የየጁ የኦሮሞ መሳፍንቶች ተወላጅ የሆኑት የቴዎድሮስ ሚስት የምንትዋብ አባት ትንሹ ራስ አሊ ነበሩ። አፄ ቴዎድሮስ ልጅ ካሣ ይባሉ በነበረበት ጊዜ ራስ አሊ ክርስትናቸው ለይስሙላ እንጅ በውስጣቸው የእስልምና ተከታይ ናቸው የሚል ጥርጣሬ ነበራቸው። በወቅቱ የግብፅ ጦር በሱዳን በኩል አድርጐ የኢትዮጵያን ምእራባዊ ድንበር እስከ ቋራ ድረስ እየገባ ይዳፈር ነበር። እነ ራስ አሊ የግብፅን የወረራ ግፊት ለመቋቋም እርምጃ ካለመውሰዳቸውም በላይ ራስ አሊ ግብጾች የኢትዮጵያን ምእራባዊ ድንበር ወደ ሱዳን ለመከለል ያደርጉ የነበረውን ጥረት በፅናት ለመቋቋም አይፈልጉም የሚል ብርቱ ስጋት አፄ ቴዎድሮስ ነበረባቸው። በራስ አሊ ላይ እንዲነሱ ዓይነተኛ ግፊት የሰጣቸው አንዱ ምክንያት ይህ ስጋት እንደነበር በታሪክ ተዘግቧል።

የኦሮሞ ህዝብ ለመጀመሪያ ጊዜ በአፍሪካ ቀንድ ህዝቦች ታሪክ ውስጥ ተመዝግቦ የሚገኘው በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው። የሰነድ፣ የቋንቋ እና የባህላዊ ትውፊት ጥናቶች የሚያረጋግጡት ይህንኑ ነው። በመጀመሪያ የኦሮሞ ሕዝብ በቦረና እና በባሬቱማ ዘርፎች የተከፈለ ነበር። በደቡብ በገናሌ ወንዝ እና በአባያ ሐይቅ መካከል ይኖሩበት ከነበረው አካባቢ በመፍለስ ነው ወደ ደቡብ፣ መሃል፣ ምስራቅ እና ምእራብ ኢትዮጵያ ሊናኙ የቻሉት። በኢትዮጵያ ታሪክ በግዙፍነቱ የተመዘገበው የኦሮሞ ነገዶች ፍልሰት የተከናወነው ከ1520 ጀምሮ እስከ 1660 ባለው ታሪካዊ ወቅት ነው። የባሬቱማ ኦሮሞ ወደ ከረዩ፣ ወሎ፣ አርሲ እና ኢቱ ቀዳሚ ነገዶች ተከፍሎ ከደቡብ ጀምሮ ወደ ምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ ኢትዮጵያ የፈለሰ ነው።የነዚህ ነገዶች ፍልሰት ባሌ፣ ደዋሮ፣ አፋር (ዳናክል) አርጐባ፣ ፈጠጋር፣ ይፋት፣ አንጐቶ፣ ላስታ እና እስከ ትግራይ ደቡባዊ ክፍል ድረስ የደረሰ ነበር። የቦረና ኦሮሞ በሜጫ እና ቱለማ ቀዳሚ  ነገዶች የተከፈለ ሲሆን፣ ፍልሰቱ ከደቡብ ተነስቶ የሰሜን እና የማእከላዊ ምእራብ ግዛቶች የነበሩ የሃድያ፣ የሻርካ፣ የማያ፣ የዋጅ፣ የሸዋ፣ የአምሃራ፣ የጅማ፣ እናርያ፣ የግቢ እና ደዲሳ አካባቢዎችን ያካተተ ነበር።

በ1520 አካባቢ ከደቡብ ቦረና እንደተነሳ የሚነገርለት በገዳ ሠራዊት ጥቃት የታጀበው የኦሮሞዎች ፍልሰት እስከ 1660 ድረስ በዘጠኝ ሉባዎች መሪነት የተከናወነ ነው። ቀዳሚው የሚልባሕ ሉባ ሲሆን በተከታታይ የገዳውን ሠራዊት የመሩት ሉባዎች ሙደና፣ ኪሎሌ፣ ቢፎሌ፣ ምስሌ፣ ሃርሙፋ፣ ሮባሌ፣ ቢረመጄ እና ሙልአታ ናቸው። የመጀመሪያው የገዳ ስርዓት የሉባ ዘመቻ ከ1522-1530 የተከናወነ ሲሆን፣ ይህ ዘመቻ የተመራው ሚልባ በተሰኘው ሉባ ነው። ይህ ዘመቻ ከቦረና ተነስቶ የገላናን ወንዝ በመሻገር ምእራባዊ ባሌን ተቆጣጠረ። ሁለተኛው በሙደነ ሉባ (1538-1546) የተካሄደ ሲሆን በዚህ ዘመቻ አማካይነት ባሌ ሙሉ በሙሉ በኦሮሞ ጐሣዎች ቁጥጥር ከመዋሉም በተጨማሪ ዘመቻው ባሌን ተሻግሮ ደዋሮንም ያዘ። ከ1546-1554 በቆየው አራተኛው የቢፎሌ ሉባ የተመራው የገዳ ተዋጊ ሃይል ፈጠጋርን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጠረ። ከ1554 እስከ 1562 ባለው የስምንት ዓመት የስልጣን ዘመን የቆየው አምስተኛው የምስሌ ሉባ የመራው የገዳ ሠራዊት ቀደም ሲል ይዞት ከነበረው ከፈጠጋር በመነሳት የዝዋይ-አዋሽ አካባቢን ተቆጣጠረ። ከ1562 እስከ 1570 በቆየው ስድስተኛው የሃርሙፋ ሉባ የሚመራው የገዳ ስርዓቱ ተዋጊ ሃይል እስከ አንጐት፣ አምሃራና ቤጌምድር ድረስ ዘልቆ ገባ። ከ1570 እስከ 1578 በቆየው ሰባተኛው የሮባሌ ሉባ የተመራው የገዳ ተዋጊ ሃይል ሸዋን ወሮ ከፍተኛ ጥፋት ከማድረሱም በላይ አባይን ተሻግሮ ምስራቅ ጐጃም ድረስ ጥቃት መሰንዘር ጀመረ። ከ1578 እስከ 1586 የገዳ ስርዓቱን በመምራት ስልጣን በያዘው ስምንተኛው የቢርመጄ ሉባ የሚመራው የገዳ ተዋጊ ሃይል በሰሜን ምእራብ እስከ ደምቢያ አልፎም ደቡባዊ ትግራይ ድረስ ዘለቀ። በመካከለኛ ምእራብ ዳሞትን እና ጋፋትን አጠቃ፤ ከአባይ ወንዝ በስተምእራብ የሚገኙትን ሙገርንና ግቤን ተቆጣጠረ። ከ1586 እስከ 1594 የገዳውን ስርዓት የመራው የሙለአታ ሉባ  የገዳ ተዋጌ ሃይል በሰባተኛው የሉባ ዘመን ለተወሰነ ጊዜ  ተቆጣጥሯአቸው በሠርፀ ድንግል ዘመነ መንግሥት መጀመሪያ ላይ በየአቅጣጫው በደረሰበት ወታደራዊ ጥቃት ለቋቸው ወደነበሩት ሸዋ እና ምእራብ ጐጃም በመመለስ በርካታ አካባቢዎችን መልሶ ማጥቃት ጀመረ። (The Great Ethnic Migrations Ca 1520-1660)

አስገራሚው ታሪክ የሚጀምረው አስረኛው ሉባ ላይ ነው። የ10ኛው ሉባ መሪ የሆነው ከ1605 — 1632 ባለው ጊዜ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የነበረው፣ የጐንደሩ ስርዎ መንግሥት (1605-1855)መስራች እንደሆነ የሚነገርለት፣ የደብረታቦር እና የደነቀዝ ከተሞች ቆርቋሪ የሆነው ንጉሠ ነገሥት ሱስኒዮስ ነበር። ልጁ አፄ ፋሲለደስ የጐንደር ከተማን የመሠረተው ነው። ንጉሠ ነገሥት ሶስኒዮስ ገና ልጅ እያለ በአፄ ሠርፀድንግል (1563-1597) ሠራዊት እና በኦሮሞው የገዳ ተዋጌ ሃይል መካከል በርካታ ውጊያዎች ተካሂደዋል።  በ1570ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ ለይ የኦሮሞው የገዳ ተዋጊ ሃይል በአፄ ሠርፀ ድንግል በሚመራው የማእከላዊ መንግሥቱ ሠራዊት ላይ ድንገተኛ ጥቃት በከፈተበት  አካባቢ በተካሄደ አንድ ጦርነት ላይ ህፃኑ ሱስኒዮስ በኦሮሞ ተዋጊዎች ተማረከ። ከአስር ዓመታት ላላነሰ ጊዜ በኦሮሞ ባህል መሠረት በጉዲፈቻ ስርዓት አደገ። የኦሮሚኛ ቋንቋን አሳምሮ ለመናገር ከመቻሉም በላይ የሉባውን የጦር ስልት በሚገባ አጠና። በወቅቱ በዋንኛው ባለአባት የጉዲፈቻ ልጅ በተደረገበት ጊዜ አባቱ ከወለዳቸው ልጆች ቀዳሚ ስለነበር፣ በገዳው ስርዓት ባህል መሠረት ብኩራናው (ቀዳሚ ልጅነቱ) ተከበረለት፣ የጉዲፈቻ አባቱ መብት ወራሽ ሆነ ማለት ነው።

በ1586 በማእከላዊ መንግሥቱ ሠራዊት እና በቢርመጄ ሉባ ተዋጊ ሃይል መካከል በተደረገ ሌላ ውጊያ ላይ ሱስንዩስ በ18 ዓመቱ በሠርፀድንግል ሠራዊት ይያዝና ወደ ሠርፀድንግል ችሎት ይወሰዳል። ሠርፀድንግል እስኪሞት እዚያው በቤተመንግሥቱ ዙሪያ ይቆያል። አፄ ሠርፀድንግል በ1597 ሲሞት፣ ከሶስቱ የዘውድ ተቀናቃኞች መካከል ሶስተኛው ሱስንዩን ነበር። ሱስኒዩስ ከልብነ ድንግል ሃረግ የወረደ እንደመሆኑ የሸዋ ድጋፍ ነበረው። በጐጃሞች ይደገፍ የነበረው ከሠርፀድንግል በፊት የነገሠው የሚናስ ወንድም ልጅ ዘድንግል ሁለተኛው ተቀናቃኝ ነበር። አንደኛው ተቀናቃኝ የትግራይ እና ቤጌምድር ድጋፍ የነበረው የሠርፀድንግል ዲቃላ እንደሆነ የሚገመተው ያእቆብ ነበር። ለማናቸውም በቅድሚያ ያእቆብ (1597-1603) ይነግሣል። በኋላም ዘድንግል (1604-1605) የያእቆብን ደጋፊዎች በጦርነት አሸንፎ ይነግሣል። ብዙም ሳይቆይ የያእቆብ ዓለማዊና እና መንፈሳዊ ደጋፊዎች ሃይል ተጠናክሮ ዘድንግልን በጦርነት ገጥሞ በማሸነፍ በዘድንግል ላይ አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ ግድያ ፈፅሞ

ያእቆብ ተመልሶ እንዲነግሥ ይደረጋል።* በዘድንግል እና በያእቆብ ደጋፊዎች መካከል በተነሳ ጦርነት የሱስኒዩስ የልጅነት ጓደኛ ዘድንግል በአሰቃቂ ሁኔታ መገደሉን የተገነዘበው ሱስኒዩስ ተይዞ በስቃይ ከመሞት ወይም ወደ ወህኒ አምባ ከመወርወር አምልጦ ምዕራብ ጐጃም አካባቢ ወደ ነበሩት አሳዳጊዎቹ ኦሮሞዎች ዘንድ ይቀላቀላል። ቀደም ሲል በጉልማሳነቱ ወቀት በነበረው ብኩርና በመጠቀም የ10ኛው የሉባ መሪ ሁኖ በመመረጥ የሱን ተከታዩች እና የገዳውን ስርዓት ተዋጊ ሃይል አቀናጅቶ በመምራት በ1607 የያእቆብን ደጋፊዎች ጐጃም ላይ በተደረገ ከባድ ጦርነት አሸንፎ የማእከላዊውን የአፄ መንግሥት ዙፋን ይጨብጣል።

ሱስኒዩስ ለሁለቱ ስርዓቶች ያለውን ቅርበት በመጠቀም ዙፋኑን እንደያዘ ብዙም ሳይቆይ የገዳውን የሉባ ሠራዊት የአፄያዊው ማእከላዊ መንግሥት ሠራዊት አካል የማድረግ ጥረቱን ተያያዘው። ከዚህም ጋር የኦሮሞውን ባህላዊ የገዳ ስርዓት ወደ አፄያዊ መንግሥቱ ባላባታዊ (Feudal) የገባር ስርዓት እንዲለወጥ እና እንዲሸጋገር፣ የኦሮሞ ባለአባቶችን በኦርቶዶክስ ክርስትና እንዲጠመቁ የማድረጉን ሂደት ገፋበት። በዚሁ የተቀናጀ እና የተዋሃደ ሠራዊት በመጠቀም ከ1610 ጀምሮ እስከ 1620 ባለው ጊዜ ባለፉት የሉባ ስርዓት ዘመቻዎች ዘመን ከጐጃም እና በጌምድር በተጨማሪ ወሎ እና ትግራይ ድረስ ዘልቆ ከነበረው ከማእከላዊ መንግሥቱ ሠራዊት ጋር አልቀላቀልም ያለውን የገዳ ሠራዊት ተዋጊ ሃይል ጋር ተከታታይ ጦርነት አደረገ። ተዋጊ ሃይሉን ተከትሎ የፈለሰውን እና በሰላም ለመኖር የሚፈልገውን በየሠፈረበት ቦታ ከገዳማት ሳይቀር ቦታ እየነጠቀ በየአካባቢው በመሰግሰግ እንዲሰፍር አደረገ። እምቢ ያለውን ተዋጊ ሃይል ጦርነት እየገጠመ ከትግራይ፣ከቤጌምድር፣ጐጃም፣ከወሎ እና በከፊል ከሸዋ እንዲወጣ አደረገ። ከዚያ በኋላ የገዳው ስርዓት ተዋጊ ሃይል ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ የሚያደርገውን ግስጋሴ አቁሞ በደቡብ፣ በመኻል፣ በምስራቅ እና ምእራብ ኢትዮጵያ በደረሰበት ቦታ ወደ ሚገኙት የዳሞት፣ የጋፋት፣ የጅማ፣ የእናርያ፣ የቦሻ፣ የቢዛሞ፣ የከፋ፣ የሞቻ የኦንጌሎ ማህበረሰቦች ይኖሩባቸው የነበሩ አካባቢዎችን ተቆጣጠረ።(The Great Ethnic Migrations, 1988) በማእከላዊ ኢትዮጵያ (ሸዋ) በማእከላዊ መንግሥቱ እና በሸዋ ነጋሴዎች ሠራዊት በአንድ በኩል፣ በገዳ ስርዓቱ ተዋጊ ሃይል በሌላ በኩል በመሆን ሲካሄድ የቆየው የተራዘመ ጦርነት በ17ኛው ክፍለ ዘመን ማብቂያ ሊገባደድ የቻለው ሁለቱም ወገኖች ሊሸናነፉ ባለመቻላቸው፣ ተደባልቆ አብሮ ከመኖር ውጭ አማራጭ ባለመገኘቱ ነበር። ጦርነቱ መጨረሻ ላይ ጊዜ በወለደው የፖለቲካ ስምምነት ሊፈታ የቻለውም ከአርባ ሰባቱ የኦሮሞ ነገዶች መካከል በእጅጉ ተዋጊ የነበሩት ቀዳሚ አባታቸው ትሎማ ከሆነው አስራ አምስት ነገዶች መካከል አብዛኛዎቹ፣ ቀዳሚ አባታቸው ሜጫ ከሆነው አስራ አምስት ነገዶች መካከል አብዛኛዎቹ፣ቀዳሚ አባታቸው ከረዩ ከሆነው ከአስሩ ጥቂቶቹ፣ ቀዳሚ አባታቸው ወሎ ከሆነው ሰባቱ መካከል ጥቂቶቹ ነገዶች የገዳ ስርዓታቸውን በሂደት በቋሚ የገባር ስርዓት እና የኦርቶዶክስ የክርስትና እምነት እንዲተኩ በማድረጋቸው ነው። በምትኩ የሸዋው አማራ ደግሞ ከአማርኛ ቋንቋ በተጨማሪ ኦሮምኛ ቋንቋን እንደ ተለዋጭ ቋንቋ አርጐ ለመጠቀም በቃ።** በዚህ ጦርነት በወለደው እና ስፋት በነበረው የሕዝብ ለህዝብ መደባለቅ፣ መሰጋሰግ እና ይህም ባስከተለው ሰፊ ባህላዊ መወራረስ ሳቢያ ጦርነቱ ወደ 17ኛው ክ/ዘመን መጨረሻ አካባቢ ሊያከትም ቻለ።

በአጠቃላይ ባለፉት አምስት መቶ አመታት የኦሮሞ ህዝብ በየሰፈረባቸው አካባቢዎች ሁሉ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በባህል፣ በቋንቋ፣ በሀይማኖት እና በትውልድ የተዋሃደ ህዝብ ሆኗል። "የኦሮሞ ሕዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተነጥሎ ለብቻው የመብት ገፈፋ የተፈጸመት ስለሆነ፣ መብቱን ሊያስከብር የሚችለው የራሱን መንግሥት ሲመሠረት ነው" በሚል አካሄድ በዚህ የተዋሃደ ህዝብ መሃል ጥላቻን ማራገብ፣ የመገነጣጠል ሃሳብን ማናፈስ ግን ስርን ከግንድ ለመለየት እንደመሞከር ይቆጠራል። እኛ በተራችን የማንገዛ ከሆነ ኢትዮጵያ የምትባል

-----------------------

*ንጉሠ ነገሥት ዘድንግል (1603-1604) እንደ አፄ ቴዎድሮስ መፈጠር ከነበረበት ጊዜ እጅግ በጣም ቀድሞ የተገኘ፣ ለሃገራቸው እድገት እና ብልፅግና አመች የሆነ ፖሊሲ በመቅረፅ ከሚታወቁት ነገሥታታ ዓይነተኛው እና ለዘመኑ አብዮታዊ ሊባል የሚችል መሪ ነበር። በዙፋን ላይ የቆየው ሁለት ዓመት ለልሞላ ጊዜ ነው። ያም ሁኖ በወቅቱ እጅግ አብዮታዊ ሊባል የሚችል የመሬት አዋጅ አውጥቶ ነበር። አዋጁ "ሰው ነፃ ነው፤ መሬት ግን በገባርነት የተያዘ ነው" የሚል ነበር። (Man is free; Land is tributary) የዚያ የመሬት አዋጅ ፍሬ ነገር በየአካባቢው (በየቀበሌው) የሚጣለው የመሬት ግብር መጠን የአካባቢው አስተዳዳሪ በሚወሰነው መሠረት ሳይሆን በመሬቱ ለምነት መሠረት ይሆናል የሚል ብቻ ሳይሆን፣ መገበር ያልቻለ መሬቱን ለቆ ይሂድ የሚልም ነበረበት። አዋጁ የቤተክህነትንም መሬት የሚጨምር ነበር። በዚህ እርምጃው ዘድንግል በኢትዮጵያ ከላይ እስከታች ያለውን ዓለማዊና የቤተክህነት ሹመኛ ጠላትነት አፈራ። ቀድሞውንም የአፄ የዘርዐድንግል ዲቃላ ነው የሚባለው ያእቆብ ከዙፋን እንዳይወርድ ይታገሉ የነበሩት የትግሬዩ ራስ ክፍለዋህድ እና የቤጌምድሩ ራስ አቅናስዩስ በንጉሠ ነገሥት ዘድንግል ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ ቀሰቀሱበት። የቤተመንግሥቱ ሹመኛ ጐጃሜው ደጃዝማች ዘሥላሲ የጐጃምን ገኘሮዎች ለዘድንግ ያላቸው ድጋፍ እንዲያነሱ እንዲቀሰቅስ የአመፀ ተባባሪ አደረጉት። ዘድንግል እና የጦር አበጋዙ የፈረንጅ እምነት ተቀብለዋል የሚል ወሪ በስፋት እንዲናፈስ በማድረግ በወቅቱ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መሪ የነበሩት አቡነ ጴጥሮስ በዘድንግል ላይ ውግዘት እንያሳርፉበት አስደረጉ። በዘድንግል ሠራዊት እና በአማፂው ሃይል መካከል በ1604 ደምቢያ ውስጥ ባርጫ በምትባል ቦታ በተደረገው ጦርነት ዘድንግል ተሸነፈ። ከአማፄው ወገን ካህናትና መነኰሳት ሳይቀሩ የጦርነቱ ተካፋይ እንደነበሩ በታሪክ ተዘግቧል። እፍኝ የማይሞሉ አውሮፓውያን እና እነሱ ያመጡለትን 200 የአውሮጻ ጠበንጃዎች የያዙ፣ ሌሎች ለንጉሡ በታማኝነት የቆሙ ወታደሮች ሲቀሩ፣ ዘድንግል ለይ በተላለፈው ውግዘት ሳቢያ በረከት ያሉ ወታደሮቹ በጦርነቱ ዋዜማ ከድተዋል። "ንጉሠ ነገሥት ዘድንግል እስከ መጨረሻው ተዋግቶ በዚሁ ጦርነት ላይ ወደቀ። ከሞተ በኋላ የአልማዝ ቀለበት ያጠለቀበትን እጣቱን ቆረጡት። ዓይኑን ጉልጉለው አወጡት፣ ሬሣው በፈረስ ቱማታ ተረገጠ፤ ከዛፍ ላይ እንዲሰቀልና የክብር ቀብር እንዳያገኝ ተደረገ። ከዘድንግል ሞት በኋላ ያእቆብንም መልሰው ለሁለተኛ ጊዜ ዙፋን ላይ አወጡት።" (ማንቴል ኔችኮ እና አንድሪዬ ባርቲኒክ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ፣ 1978 ከጀርመንኛ አማርኛ ተተርጉሞ ለህትመት የተዘጋጀ መፅሐፍ) ከዚህ ዓይነቱ የዘድንግል አሰቃቂ ሞት በኋላ ነው የያእቆብ የዙፋን ተፎካካሪ የነበረው እና የኦሮሞው የገዳ ስርዓት የ10ኛው ሉባ መሪ እንደነበር የተነገረለት ሱስኒዩስ ከቤተመንግሥቱ በማምለጥ ወደ ኦሮሞ አሳዳጊዎቹ ሂዶ የተቀላቀለው።

** ከአራቱ የዘመናዊት ኢትዮጵያ መሪዎች መካከል ንጉሠ ነገሥቶቹ ዳግማዊ አፄ ምኒሊክ እና ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሤ ኦሮምኛ ቋንቋ አጥርተው ይናገሩ እንደነበረ በአንዳንድ ታሪካዊ ሰነዶች ላይ ተዘግቧል። የሜጫ እና ትሎማ መሪ የነበሩት ጀነራል ታደሰ ብሩ የሜጫ እና ትሎማ ማህበርን ለመመስረት ስለፈለግን ይፈቀድልን ብለው ለንጉሡ ጥያቄአቸውን ባቀረቡበት ጊዜ "ከኛም በላይ ኦርሞ ላሣር ነው" የሚል አጭር መልስ በንጉሡ እንደተሰጣቸው ተዘግቧል። በሌላ በኩል ሪፓብሊካኖቹ የዘመናዊት ኢትዮጵያ መሪዎች ኘሬዚዳንት መንግሥቱ ሃይለ ማርያም እና ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የከተማ ልጆች እንደመሆናቸው "ጆሮአቸውን ቢቆርጧቸው" ኦሮምኛ አይሰሙም። ኘሬዚዳንት መንግሥቱ ሃይለማርያም የአማራ እና የኮንሶ ተወላጅነት እንዳላቸው በቅርብ የሚያውቋቸው ሰዎች ይናገራሉ። የኦሮሞ ፍልሰት ትግራይ ድረስ የደረሰ ቢሆንም፣ በራያና አዘቦ አውራጃ ዋጅራት (በኦሮምኛ-ዋጅራ) ላይ በሱስኒዩስ መሪነት እና በወቅቱ በነበሩ የትግራይ መሳፍንቶች ግንባር ቀደምትነት በተደረጉ ጦርነቶች በመገታቱና አድዋ ባለመድረሱ፣ ጠቅላይ ሚ/ር መለስ ዜናዊ ኦሮምኛ ቋንቋ ለመልመድ አጋጣሚ አላገኙም።

አገር ልትኖር አይገባም በሚል አመለካከት ዙሪያ የሚያጠነጥነው ተራ ጠብቆ የመግዛት ፖለቲካ ትልልከኛም ዘመናዊም አካሄድ አይደለም። ትክክለኛው አካሄድ በኢትዮጵያ ምድር ለዲሞክራሲ በአጠቃላይ ለነፃ እና ፍትሃዊ ምርጫ በተለይ በጋራ መታገል ነው። ስልጣን በዚህ መንገድ ብቻ መያዝ እንዳለበት መተማመን ካለ ችግሩ ይቃለላል። አሰባሳቢ ሊሆን የሚገባው የወቅቱ የፖለቲካ አጀንዳ ይኸ ነው።

በታህሣሥ ወር 2001 ዓ.ም አጋማሽ ላይ የመድረክ አባል ድርጅቶች በጋራ በኢምፔሪያል ሆቴል ባካሄዱት ስብሰባ ላይ የአረናረ ትግራይ ሊቀመንበር አቶ ገብሩ አስራት እና የምክክር መድረኩ አባል ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ያላቸውን ግንዛቤ የሚገልፁ ፅሁፎች አቅርበዋል። አቶ ገብሩ አስራት <u>በኢትዮጵያ የፌድራል መንግሥታዊ ሥርዓት አወቃቀር ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች </u>በሚል ርእስ ለተሰብሳቢው ባቀረቡት ጽሁፍ በገፅ 2 ላይ የሚከተለው አባባል ይገኝበታል።

> "ሚኒሊክ ግዛታቸውን ከመካከለኛው የደጋው አካባቢ ወደ ደቡብና ምስራቅ የኢትዮጵያ አካባቢ በማስፋፋት የአሁኑን ዳር ድንበር የያዘች ከ80 በላይ ብሄር ብሄረሰቦችን ያቀፈች ኢትዮጵያ መሠረቱ። በጣም ጠንካራ ባህላዊ ንግሥናዎች፣ <u>አንዳንዶቹ ከዛ በፊት በደጋው ግዛት ሥር ያልነበሩ እንደ ኦሮሚያ፣ ወላይታ፣ ሲዳማ፣ ጉራጌ፣ ከፋ ወዘተ </u> በማሸነፍ በቁጥጥር ስር አስገቡ።" (ገፅ 2)

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ደግሞ በዚሁ ስብሰባ ላይ <u>"የብሄርና የግለሰብ መብት ጥያቄ በኢትዮጵያ ትናትና ዛሬ"</u> በሚል ርእስ ባቀረቡት ፅሁፍ የኢትዮጵያን ታሪክ እንዴት እንደሚገነዘቡት ባብራሩበት ክፍል ከዚህ የሚከተለው አባባል ይገኝበታል።

> ከዛሬይቱ ኢትዮጵያ ግዛት (state) ጋር በተያያዘ አብዛኛው ብሄር ብሄረሰቦች ሕዝቦች የምንላቸው ማህበረሰቦች በ19ኛ መቶ ዓመት መጨረሻ አካባቢ በግዛቷ ተጠቃለዋል። (ገፅ 1)... አንዳንድ የጭቁን ህዝቦች መብት ጥያቄን የሚያነሱ (ይኸን ይህን የቅኝ አገዛዝ ስርዓት ነበር ይሉታል።) … <u>በኔ አረዳድ የዚህ ዓይነት የማህበረ ኢኮኖሚ አረዳድ ባህላዊና የፖለቲካ ስርዓት በላቲን አሜሪካ በደቡብ አፍሪካ እና በፓልስታይን ከታየው ሰፋሪ ኰሎኒያሊዝም (settler colonialism) ጋር ይመሳሰላል።</u> (ገፅ 15)

በኢትዮጵያ ከአስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የነበረውን ታሪክ እንዴት እንደሚገነዘቡት ዶ/ር ነጋሶ በዚሁ ከላይ ርእሱ በተጠቀሰው ፅሁፋቸው አማካይነት ሲያቀርቡ፡-

> ከአስራ ስድስተኛው መቶኛ ክፍለ ዘመን በኋላ ሌላ ሂደት መከሰት ጀመረ በሸዋና በሙዝሊሙ ሱልጣኔቶች ዘመን ክርስቲያንም እስላምም ያልሆኑ ኦርምኛ ተናጋሪ የነበሩ ማኅበረሰቦች <u>በዛሬይቱ ደቡብ ምስራቅ፣ ደቡብ እንዲሁም እስከ ሸዋና ወሎ በግብርናና በከብት እርባታ ላይ ተመስርተው ይኖሩ ነበር።</u> እነዚህ የኦሮሞ ማህበረሰቦች በያሉበት አካባቢ በገዳ ስርዓት ላይ የተመሠረተ አስተዳደር መስርተው ሲኖሩ የነበረ ቢሆንም ማእከሉን ኦዳ ነቤ (ዱከም) አካባቢ የነበረ የገዳ ኮንፈድራላዊ አገዛዝ (state) በአጼ አምደ ጽዮን ጊዜ እንደነበረ ታሪክ ይጠቁማል። ሆኖም ግን በሰሜን ክርስቲያናዊ ነገሥታት በሌላም በኩል ከምሥራቅ የሙዝሊም ሱልጣኔቶች ሲያደርሱበት በነበረው ጥቃትና ተፅዕኖ ምክንያት <u>የኦሮሞ ከንፈድራሉ ማዕከል ወደ ባሌው ወላቡ ተዘዋውሮ ነበር። በጊዜ ሂደት ኮንፈደራሲው እንደ አዲስ በመደራጀት በ16ኛው ክፍለ ዘመን ወደ ምዕራብ፣ ወደ ሰሜንና ወደ ምስራቅ በማጥቃት የዛሬውን ኦሮሚያ አብዛኛውን አካባቢ መልሶ ከቁጥጥሩ ስር በማስገባት ከዚያም ባሻገር በምዕራብ፣ በሰሜንና በምስራቅ በሌሎች</u> ስርአቶች ስር የነበሩት አካባቢዎች ለመያዝ ችሎአል። ከዚያም በኋላ እስከ 19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ክርስቲያናዊ የድሮ ኢትዮጵያ መንግሥት ግዛት በደቡቡ የዛሬውን የአማራ ሰሜን ሸዋን፣ በምዕራብ ጎጃን፣ በሰሜን ወሎ፣ ላስታ፣ የጁ፣ ራያ ሰሜንና ትግራይን እና ባሕረ ነጋሽ <u>ብቻ</u> ያጠቃለለ ነበር።"

በማለት አስቀምጠውታል።

የአፄ አምደፅዮን ዘመን መንግሥት በ1314 ጀምሮ እስከ 1344 ድረስ የቆዩ ነው። በዚያን ጊዜ ደግሞ የኦሮሞ ነገዶች ፍልሰት በደቡብ እና ምስራቅ ኢትዮጵያ ሃይላቸውን አጠናክረው በነበረው የሐረሩ እስላማዊ ሱልጣኔት ተገቶ ስለነበር፣ ከደቡብ ቦረና ቆላማ አካባቢዎች እንዳላለፈ ነው በታሪክ የተዘገበው።

የኦሮሞ ጐሣዎች ፍልሰት  ከቦረና አካባቢ ደቡባዊ ክፍል በ1520 ገደማ ተነስቶ እስከ 1660 ባለው ጊዜ በዘጠኝ ሉባዎች ዘመቻ አማካይነት በአጭር ጊዜ ውስጥ ደቡብ ኢትዮጵያን አቋርጦ ወደ መሃል ኢትዮጵያ ሊደርስ የቻለው የደቡባዊ ምስራቅ እስላማዊ ግዛቶች እና ማእከላዊ መንግሥቱ ለተከታታይ ሁለት መቶ አመታት ባካሄዱት ጦርነት በተለይም ደግሞ የዚህ ጦርነት ማሳረጊያ በነበረው የግራኝ መሃመድ ጦርነት ካበቃ በኋላ ነው። ቀደም ሲል እንደተጠቀመው በሃይማኖታዊ ጦርነቱ የተሰለፉት ሁለቱም ሃይሎች በወታደራዊ ሃይልም ሆነ በኢኮኖሚ አቅም በመዳከማቸው እና የኦሮሞው የገዳ ሠራዊት ተዋጊ ሃይልን ለመቋቋም ባለመቻላቸው ፍልሰቱ በተፋጠነ ሁኔታ ተከናውኖ ወደ 1620 አካባቢ ሰሜን ኢትዮጵያ ሊደርስ እንደቻለ የታሪክ መፅሐፍት በሰፊው ዘግበውታል።

ስለሆነም ዶ/ር ነጋሶ ከላይ በተጠቀሰው ፅሁፋቸው እንዳሰፈሩት የኦሮሞው የገዳ ስርዓት ተዋጊ ሃይል ወደ መሃል ኢትዮጵያ የተዳረሰው በ13ኛው ክፍለ ዘመን እንደነገሠ በሚታወቀው በነበረው በአፄ አመደፅዬን ዘመነ መንግሥት ሳይሆን በ16ኛው ክፍለዘመን መጀመሪያ ላይ

ማለትም ከ1563 እስከ 1597 በቆዬው የአፄ ሠርፀድንግል ዘመነ መንግሥት ነው፡፡ በአፄ ስርፀ ድንግል ዘመነ መንግሥት በማእከላዊ መንግሥቱ የጦር ሃይል እና በኦሮሞው የገዳ ስርዓት ተዋጊዎች መካከል ከደቡብ ኢትዮጵያ ጀምሮ በኢትዮጵያ በስምጥ ሸለቆ ውስጥ እስከሚገኙት ሐይቆች ድረስ በርካታ አውዳሚ እና ከባድ እልቂት ያስከተሉ ጦርነቶች ተደርገዋል፡፡ በዚያ ወቅት ከደቡብ ተነስቶ ወደ መሃል ኢትዮጵያ የተመመው የኦሮሞ የገዳ ሰርዓት ተዋጊ ሃይል በአፄ ሠርፀድንግል ሠራዊት የተገታው ዶ/ር ነጋሶ በፅሑፋቸው እንዳመለከቱት ዱከም ላይ ሳይሆን ዝዋይ ሃይቅ አካባቢ እንደሆነ የፖላንድ ዜጐች እና የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራመሪዎች በሆኑት በፕሮፌሰር ማንቴል ኒዩችኮ እና ፕሮፌሰር አንድሬ ባርቴንክ "የኢትዮጵያ ታሪክ" በተሰኘው መፅሐፍ በዝርዝር ተዘግቧል፡፡ ከአፄ ሠርፀድንግል ዘመነ መንግሥት በፊት ከደቡብ ወደ መሃል ኢትዮጵያ እየፈለሱ ይመጡ የነበሩት ውልደታቸውን በተለያዩ ቀዳሚ አባቶች የሚቆጥሩት የኦሮሞ ነገዶች መካከል በየደረሱብት እርስ በርሳቸው በግጦሽ መሬት እና በመሳሰሉት ይዋጉ ነበር፡፡

እርግጥ ወደ መሃል ኢትዮጵያ የሚያደርጉትን በጦርነት የታጀበ ሕዝባዊ ፍልሰት ተከታታይነት እንዲኖረው ለማድረግ እና ከማእከላዊው የአፄያዊው መንግሥት ሠራዊት ጋር የሚያረጉት ወታደራዊ ፍልሚያ እንዲሰምር የየነገዱ የገዳ ሠራዊት አልፎ አልፎ እየተቀናጀ በማእከላዊ መንግሥቱ ይዞታ ላይ ይዘመት ነበር፡፡ በተለይ በአፄ ሠርፀድንግል ዘመነ መንግሥት የተሰነዘረባቸውን ከባድ ወታደራዊ ዘመቻ ለመቋቋም የተወሰኑ የኦሮሞ ነገዶች ፈጥረውት የነበረውን ግምባር ከሆነ ዶ/ር ነጋሶ <u>በገዳ ስርዓት ላይ የተመሠረተ የገዳ ኰንፌደራላዊ አገዛዝ ወይም መንግሥት</u> (state)" የሚሉት ሪቻርድ ግሪንፊልድ "የኢትዮጵያ አዲስ የፖለቲካ ታሪክ" ከተሰኘው መፅሐፉ ላይ ያሰፈረውን አባባል ይዘው ይመስላል፡፡ ይሁንና ግሪን ፊልድ የጂኦግራፊ ባለሙያ እንጅ የታሪክ ተመራማሪ አይደለም፡፡ ለዚያውም እሱም ቢሆን የኦሮሞ ነገዶች ፍልሰት በ16ኛው ክፍለ ዘመን እንደጀመረ፣ በ17ኛው ክፍለ ዘመን አብዛኛው የሃገሪቱ ደቡብ እና ምእራባዊ ግዛቶች በኦሮሞዎች ቁጥጥር ስር እንደዋለ… ሲዳሞ በመባል የሚታወቁ ግዛቶች በጊዜ ሂደት ወደ ኦሮሞነት እየተለወጡ እንደሄዱ እና የኦሮሞ ነገዶች እየተጣመሩ የንጉሠ መንግሥቱን ሃይሎች እና ለማእከላዊ መንግሥት የሚገብሩ በደቡብ፣ ምስራቅ እና ምእራብ የነበሩ ግዛቶችን ያጠቁ እንደነበረ ፅፏል፡፡

በሌላ በኩል ስፔንሰር ትሪሚንግሃም የተሰኘው የኢትዮጵያ እስልምና ታሪክ እውቅ ተመራመሪ "እስላም በኢትዮጵያ" በተሰኘው መፅሐፉ

> "የኢማም አህመድ (ግራኝ) ጦርነት ካስከተለው ከፍተኛ ጥፋት በኂላ፣ ይህም ጥፋት (በማእከላዊ መንግሥቱ ላይ) ያስከተለውን ግራ መጋባት እና ማህበራዊ ባዶነት በመጠቀም የኦሮሞው ፍልሰት ግድቡን ጥሶ እንደሚፈስ የባህር ውሃ በኢትዮጵያ ላይ በአንድ ጊዜ ተንሰራፉ፡፡ በዚህ ወቅት (በ16ኛው ክፍለ ዘመን) ልል በሆነ ኰንፌደሬሽን መልክ የተሣሠሩ የኦሮሞ ነገዶች (a loosely-net confederation of oromo tribes) ነበሩ፡፡ የዳበረው የፖለቲካ አደረጃጀታቸው (የገዳውን ስርዓት ማለታቸው ነው) የህዝቡ ቀልብ የተማከለበት የነገዳዊ መለያ ምልክት (Symbol) ነበር"

በማለት ፅፏል፡፡

ስለዚህ ዶ/ር ነጋሶ ስለኢትዮጵያውያን ኦሮሞዎች ታሪክ ሲያነሱ የሚጠቅሱት በሙያ ደረጃ የታሪክ ተመራማሪዎች የፃፋቸውን ሳይሆን ሙያው ጅኦግሪፊ የሆነ ሰው የፃፈውን የፖለቲካ ዘገባ ከሆነ፣ ታሪክን በተከናወነበት መልኩ ለማቅረብ እንዳልፈለጉ፣ በአንፃሩ ታሪክን ከፖለቲካ አመለካከታቸው አንፃር በሚስማማ መልኩ ለማቅረብ መምረጣቸውን ያመለክታል፡፡ የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ለፖለቲካ አቋማቸው በድፍረት መቆምን መሠረት ላደረገው ስብእናቸው እጅግ ከፍተኛ አክብሮት እንደአለው ለመግለፅ ይፈልጋል፡፡ ይኸ አክብሮት በፖለቲካ አቋማቸው ሳይፈሩ እና ሳያፍሩ በፅናት የሚቆሙትን የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ሁሉ ያካትታል፡፡ ይሁንና ታሪክን ለፖለቲካ ፍላጐት ማስገዛት እና ለህዝቦች ዘላቂ ጥቅም ወይም ፍላጐት እንዲያገለግል ማድረግ ለየቅል መሆናቸው መገለፅ ይኖርበታል፡፡ በዚህ አጋጣሚ የዚህ ፅሁፍ አቅራቢም ሆነ ዶ/ር ነጋሶ ወደ አራት አስርት ዓመታት ለተጠጋ ጊዜ የፖለቲካ እና የኢኰኖሚ ፍልስፍናው አቀንቃኝ እና አራማጅ ሁነን እንድንቆይ ያደረገን ካርል ማርክስ ሰዎች ስለታሪክ ሊኖራቸው የሚገባውን ግንዛቤ አስመልክቶ የፃፈውን እና ምናልባትም ሁለታችንም አሁንም ቢሆን እንደምናምንበት የምገምተውን አባባል ለመጥቀስ እፈልጋለሁ፡፡ ማርክስ፣ <u>*አስራ ስምንተኛ ቡሪሜር*</u> በተሰኘው ዝነኛ ጽሁፍ የመጀመሪያ ገፅ ላይ፡

> *ሰዎች የራሳቸውን ታሪክ ራሳቸው ይሠራሉ፡፡ እንደፈለጉ አድርገው ግን ሊሠሩት አይቻላቸውም፡፡ ራሳቸው በመረጡት ሁኔታም ሊሠሩት አይችሉም፡፡ ታሪክን ሊሠሩ የሚችሉት በወቅቱ በተጨባጭ ከሚያጋጥማቸው፣ <u>ቀደም ሲል ከተረከቡት እና ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን መሠረት በማድረግ ነው፡፡</u>* ***/ስርዝ የተጨመረ/***

በመጀመሪያ ደረጃ በ1983 ኢህአዴግ የመንግሥት ስልጣንን በኃይል ከያዘ በኂላ ድርጅቱ ሲመሰረት አንስቶ አልሞ የተነሳበትን ስትራቴጂክ የፖለቲካ ግብ ለማሳካት በማሰብ የአማራ ክልላዊ መንግሥት የኦሮሞ ክልላዊ መንግሥት ወዘተ… የተሰኙ ክልላዊ መንግሥታት እስከአቋቋመበት ጊዜ ድረስ ባለው የኢትዮጵያ ታሪክ በነገዳዊ/ አካባቢያዊ ደረጃ ካልሆነ በስተቀር በሃገረ-መንግስትነት የሚታወቁ በብሄረሰብ ስማቸው የሚጠሩ የኦሮሞም ሆነ የአማራ፣ የትግራይም ሆነ የሌሎች በአሁኑ ስያሜያቸው የሚታወቁ መንግሥታት ስለመኖራቸው በታሪክ አልተዘገበም፡፡ በሁለተኛ ደረጃ "ኰንፌደሬሽን" የተሰኘው የእንግሊዘኛ ቃል ፅንሰ ሃሳብ ከአንድ በላይ የሆኑ የተለያዩ መንግሥታት የሚፈጥሩት <u>የላላ</u>

*<u>የስርዓተ መንግሥት ጥምረት</u>* እንጅ በአንድ ብሄረሰብ ስር የሚካተቱ ነገዶችን ግምባር/ጥምረት የሚያመለክት አይደለም። የጅኦግራፊ ባለሙያው ሪቻርድ ግሪንፊልድ ፅፎታል የሚል ክርክር ከተነሳም፣ እሱ ሊያመላክት የፈለገው የተለያዩ የኦሮሞ ነገዶች የማእከላዊውን የአፄያዊ መንግሥት ለመዋጋት የፈጠሩትን ነገዳዊ ጥምረት እንጅ ሃገረ-መንግሥትን የመመስረት ሂደት እንዳልነበረ እራሱም በመፅሐፉ ልዩልዩ ክፍሎች ከሠፈራቸው አባባሎች መገንዘብ ይቻላል።

በኢትዮጵያ ታሪክ ተዘግቦ የሚገኘው ኦሮሞዎች ከዛሬይቱ ኢትዮጵያ ደቡባዊ ክፍል ከገናሌ ወንዝ እና ከአባያ ሃይቅ መካከል ይገኝ እንደነበር ከተዘገበው **<u>መደወላቡ</u>** ይባል ከነበረው ቦታ ተነስተው ወደ ላይ እስከ ደጋው ድረስ እየተሰራጩ መምጣታቸውን ነው።* ዱከም ላይ የኦሮሞ ኵንፌደራሲ ቀደም ሲል መሥርተው በኋላ ወደ ባሌ መመለሳቸውን የሚገልፅ የታሪክ መረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀርብ የተስተዋለው በዶ/ር ነጋሶ ነው። የዚህም ዓላማ ግልፅ ነው። ኦሮሚያ የሚባል እራሱን የቻለ መንግሥት ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ እንደነበረ እና ይህ ሂደት በአፄ ሚኒሊክ እንደተቀለበሰ ለማስረገጥ ነው። ይህ አዲስ ታሪክ ዶ/ር ነጋሶ በአፄ ሚኒሊክ ጊዜ የተከሰተውን የኢትዮጵያ መልሶ ግንባታ **<u>"ከሰፋሪ ቅኝ አገዛዝ ስርዓት"</u>** ጋር ለማመሳሰል ሊጠቀሙበት ያሰቡ መሆኑ ግልፅ ነው። ዶ/ር ነጋሶ በ1997 ምርጫ ዋዜማ በቅንጅት ስዊዘርላንድ ፓልቶክ ፕሮግራም ቀርበው ሲወያዩ "የኦሮሞ ህዝብ የራሱን እድል በራሱ መወሰን አለበት ... ሪፈረንደም ያካሂድ፤ እኔም ከኢትዮጵያ ጋር እንዲሆን ዘመቻ አደርጋለሁ" እንዳሉ ተዘግቧል። (አውራምባ ታይምስ ቁጥር 54፣ መጋቢት 2/2001) የኦሮሞ ህዝብ ከገዛ ሀገሩ ከኢትዮጵያ ለመገንጠል እፈልጋለሁ የሚል ድምፅ ይሰጣል ብሎ ለማሰብ ያስቸግራል። ሃገርን በፕሬዚዳንትነት እንዲያገለግሉ ተመደበው ከነበሩ እና ሃላፊነት ከሚሰማቸው ምሁር ይኸ አይነት አባባል ሲሰነዘር የስጋት ምንጭ ይሆናል። ከዚህ በላይ ከቀረበው ዘገባ ለመረዳት እንደሚቻለው የታሪክ ግንዛቤ አሁን በተለያዩ የፖለቲካ ጐራዎች የተሰለፉ የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች የሚያራምዱትን የፖለቲካ አመለካከት መቀራረብ ወይም አለመቀራረብ ከሚወስኑ ጉዳዩች መካከል አይነተኛ ቦታ ይዞ ይገኛል። ለዚህም ነው የታሪክ ግንዛቤ ልዩነትን በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ዘርዘር ባለ ሁኔታ ማቅረቡ የግድ የሆነው።

-----------

* ስለ ኦሮሞዎች ሰፋ ያለ ጥናት ያካሄደው ሃበርላንድ ኦሮሞዎች ስለነገዳቸው አመጣጥ የጋራ ተረት-መሰል እምነት እንዳላቸው በመጠቆም 'ባሪጋማ' ከሚባል ቦታ መጣን ብለው እንደሚያምኑ ጽፏል። ይህም 'ከጠዋት ወጋገን ማዶ' ወይም ከባህር ማዶ ተብሎ ሊተረጉም ይችላል። በሌሎች ዘገባዎች ደገሞ ኦሮሞዎች ሓሮ ውላቦ ከሚባል ቦታ ተነሳን እንደሚሉ ተዘግቧል። በኦሮሞዋች እምነት መሠረት ሓሮ ውላቦ በተባለው አካባቢ ኵሬ መሰል ባህር እንደነበረ ይተረካል። በኦሮሚፋ 'ዑማን ውላቦ ባቲ' የተሰኘው አባባል 'ከውላቦ ውሃ ፍጥረት ወጣ' ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። በመሆኑም ሰውም ሆነ እንስሳ ከዚያ የባህር ውሃ እንዳይጠጣ የተከለከለ ነው። ለኵሬዋም ክብር ሲባል ከብትም፣ በግም ፍየልም በመስዋእትነት ይታረዳል። አንዳንድ የታሪክ ዘጋቢዎች ይህ ቦታ ከግራኝ ወረራ በፊት ባሕር ገሞ በመባል ይታወቅ የነበረ፣ በአጼ ይስሃቅ ዘመነ መንግሥት (1414-1429) ለንጉሠ ነገሥቱ ግዛት ፈረስ ይገብር የነበረ፣ በደቡብ በገላና ወንዝ እና አባያ ሐይቅ አካባቢ ይገኝ የነበረ ቦታ ነው ይላሉ።

## 4. የፖለቲካ ፓርቲዎች ውህደት፣ የግንባር እና የጥምረት ግንኙነት ከአንድነት የፖለቲካ ዓላማ አንፃር

በጽንሰሃሳብ ደረጃ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በትብብር መስራታቸው ተደጋፊነት ያለው መሆኑ በቅድሚያ ግልጽ ሊሆን ይገባል። ይሁንና የትብብራቸው ስፋት እና ጥበት እንደ አቋማቸው መቀራረብ እና መራራቅ የሚወሰን ይሆናል። ፕሮግራሞቻቸው ሙሉ በሙሉ የሚጣጣሙ ከሆነ ጎራቸውን አፍርሰው በአንድ ጎራስር በውህደት መልክ ሊጠቃለሉ ይችላሉ። ፀባይ በሆኑ የፖለቲካ ራእዩቻቸው እና ዓላማዎቻቸው እንዲሁም በኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ፖሊሲዎቻቸው ተመሳስለው በድርጅታዊ አወቃቀር እና የአሰራር መርህ ላይ መሠረታዊ ልዩነት ካላቸው የድርጅታዊ ነፃነታቸው እንደተጠበቀ ሁኖ የጋራ ግንባር በመመስረት በአንድ የምርጫ ማኒፌስቶ ዙሪያ በጋራ ለምርጫ የመቅረብ ወይም በተናጠል በምርጫ ከቀረቡም በሚያገኙት ድምፅ መሠረት የጥምር መንግሥት ሊያቋቁሙ ይችላሉ። ከዚህ ውጭ ያለው አማራጭ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሚያገናኙአቸው እና መፈጸማቸው የፓርቲዎቹ የጋራ ፍላጎት በሚሆኑባቸው እና በሚያስተባብሩ ጥያቄዎች ዙሪያ ተጣምሮ በትብብር መስራት በጣም ተቀባይነት ሊኖረው የሚገባ አካሄድ መሆኑ የሚታመንበት ነው።

በአንድነት እና በመድረክ ዙሪያ የተሰባሰቡ የፖለቲካ ድርጅቶች ግንኙነት ለጊዜው ሊመሠረት የሚገባው ከውህደት እና ከግንባር ውጭ ባለው ሶስተኛው አማራጭ ማለትም በአንድ መዋቅር ውስጥ በመታቀፍ ሳይሆን በሚያስማሙ ጉዳዩች ዙሪያ በጥምረት ወይም በትብብር በመስራት ነው። በዋና ዋና የሃገር ጉዳዩች ላይ ያሉት ልዩነቶች በውህደት እና በግንባር መልክ ሊያሥሩ የሚያስችሉ አይደሉም ማለት በምንም መልኩ ሶስተኛ በሆነው ቀመር (modality) በጥምረት መሥራትን የሚያንኳስስ አይደለም፣ ሊሆንም አይገባም። በጥምረት የመንቀሳቀሱን ወቅታዊነትም የሚያንትት መሆን አይኖርበትም። መሠረታዊ ልዩነቶች በጊዜ ሂደት ሊጣበቡ ይችሉ ይሆናል። ካልተጣበቡም የልዩነት መኖር መጠፎ አይደለም። ልዩነት በሰለጠኑት እና በዳበሩት አገሮች እና ሕዝቦች ዘንድም አለ። ልዩነት በመሠረቱ የለውጥ እና የእድገት ምንጭ ነው። ቁምነገሩ የአያያዙን ስልት ማወቅ እና ልዩነቱ ሊመራ በሚችበት አካሄድ ላይ የጋራ ስምምነት ላይ መድረሱ ነው። ፈረንጆቹ እና የሰለጠኑት ሕዝቦች የሚበልጡን በዚህ ዓብይ ጉዳይ ነው። የሰለጠኑቱ ከነፃ የፍትህ ስርዓት በመነጨ የሕግ የበላይነት ስለሚገዙ፣ አለመግባባቶችን ማንም በማይጠራጠረው እና ሁሉም ለተግባራዊነቱ በቆመለት ነፃ የፍትህ ስርዓት አማካይነት በሰላማዊ ሁኔታ ይፈቱታል። በሰለጠኑት አገሮች ይህ በየወቅቱ የሚፈፀም ተግባር ከመሆን አልፎ ባህል ሁኗል። ሃገራችንን ኢትዮጵያን ጨምሮ በብዙ የአፍሪካ አገሮች ይህ ባህል ሀ ብሎ የሚጀምርበትን ጊዜ ህዝቡ እየናፈቀ ለመሆኑ የ1997 ምርጫ ምስክር ነው። እንዳልመታደል ሁኖ ይህ ጉዳይ በሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ በአሮጌ ጨርቅ ላይ ሌላ ድሪቶ እንደመጣፈት እየሆነ አልዋናድ ብሎናል። ለሀገራችን አዲስ የሆነውን የዲሞክራሲ አሠራር ባህል አሃዱ ብሎ በመጀመር ረገድ የማይሞት ታሪክን በማስመዝገብ ረገድ ለኢህአዴግ ሁለተኛ ታሪካዊ አጋጣሚ ቀርቦለታል። ይህን ከ1997 ምርጫ ወዲህ የተደገመ የታሪክ አጋጣሚ ሊጠቀምበት ይገባል። ይህ እንዲሆን ደግሞ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ሊያስተባብራቸው በሚችለው ቀመር ላይ ተስማምተው፣ ስምምነታቸውን ባለማዛነፍ መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል።

መድረክም ሆነ አንድነት ተቀዳሚ ዓላማቸው ሊሆን የሚገባው ስለግንኙነታቸው ቅርፅ ከመወሰናቸው በፊት ሁለቱም የፖለቲካ ስብስቦች የጸና ዓላማዎቻችን ናቸው ብለው የሚያምኑባቸውን አንኳር አንኳር አመለካከቶቻቸውን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ራእዩቻቸውን እና ዓላማዎቻቸውን እንዲሁም የፓርቲ ድርጅታዊ አወቃቀር እና የአሠራር መርሆዎቻቸውን አንጥረው በማውጣት የሚመሳሰሉባቸው እና የሚለያዩባቸውን ነጥቦች ለይተው ማወቅ ነው።

በኢትዮጵያ በተለይም ከ1983 ወዲህ ያሉትን የፖለቲካ ድርጅቶች ህብረቶች ድክመት ነቅሶ በማውጣት እና የመፍትሄ ሃሳብ በማቅረብ ረገድ አቶ ስዬ አብርሃ **"የፖለቲካ ድርጅቶች የሕብረት ጥያቄ በኢትዮጵያ፤ ትናትና ዛሬ "** በሚል ርእስ ለምክክር መድረኩ ሴሚናር ያቀረቡት ፅሁፍ የተዋጣለት ነው። የእስካሁኑ ህብረቶች ያልተሳኩባቸውን ምክንያቶች ሲዘረዝሩ 1) ህብረታቸው ከአቋሞች መቀራረብ አለመጀመሩ 2) ህብረቶቹ በሁኔታዎች አስገዳጅነት (በምርጫ ዙሪያ) የሚጠነሰሱ እና በአጭር ጊዜ እይታ የተለከፉ 3) ወደፊት ያለመመልከት ችግር ያለባቸው መሆኑ 4) ለተግዳሮቶች (challanges) ያለመመጠን ችግር በሚል ከፋፍለው አቅርበዋቸዋል። (ገፅ 20-23)። በአራተኛነት የተጠቀሰውን ችግር ለማብራራት ያሰፈሩት አባባል እጅግ ወቅታዊ በመሆኑ ሊጠቀስ ይገባዋል።

> … ፓርቲ መመሥረት ትርፍ ማስገኛ ትንሽ ኩባንያ ወደ መሆን እየወረደበት (ያለ) ሁኔታም ይታያል። ፖለቲካና ፖለቲከኝነት ለሃገር ጥቅም ይበጃል የተባለውን አቋም ይዞ ችግሮችን እየተጋፈጡ ለቁምነገር ማድረስ መሆኑ ቀርቶ ተቃዋሚ ነኝ ብሎ የማሳሳቻ ሥራ ለመስራት እንደሽፋን እየሆነ ነው። … በተቃዋሚው ሠፈር ዲሞክራቲክ የሆነ የፖርቲ አሠራር ያለመገንባት ችግር አለ። ዲሞክራቲክ ስርዓት እንገነባለን እያሉ በውስጣቸው ግን ዲሞክራቲክ አሠራርን (ያላዋሃዱ) ዲሞክራቲክ ፓርቲ ለመገንባት ያልቻሉ ብዙ ናቸው። ዲሞክራሲ ደግሞ ዲሞክራቲክ ባሆኑ ፓርቲዎችና መሪዎቻቸው ሊገነባ አይችልም። ዲሞክራቲክ ያልሆነን ስርዓት ዲሞክራቲክ ባልሆነ ፓርቲ አሸንፎ ዲሞክራሲ ላይ መድረስ አይቻልም።(ስዬ አብርሃ፣ ታህሳስ 18/2001፡ ገፅ 23)

በወቅቱ የተቃውሞ ፖለቲካ ውስጥ የነበረውን እና በአዲስ እያቆጠቆጠ ያለውን ችግር በተመለከተ ከዚህ በተሻለ ሁኔታ ለመግለፅ ያዳግታል፡፡

ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ልዩነቶቻቸውን አንጥረው ሳያወጡ ከሶስቱ በአንዱ የግንኙነት ቀመር ላይ አብረው ለመስራት ቢስማሙ ግንኙነቱ ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል እንደሚባለው ይሆናል፡፡ ይህ አካሄድ የሚጠቅመው ለሁለቱ ሳይሆን ለኢህአዴግ ነው የሚል የስነ-አመክኗዊ (Logical) አስተያየት ሊቀርብ ይችላል፡፡ መቅረቡም ትክክል ነው፡፡ ይህ ሊሆን አይገባውም ከሚል መነሻ እንነሳ እና የ2002 ምርጫን በተመለከተ በቅድሚያ ሊቃኙ የሚገባቸውን ሁለት የግንኙነት መስኮች እንመርምር፡፡

የመጀመሪያው ከላይ እንደ ተጠቀሰው ውህደት ሲሆን፣ ይህ አማራጭ (modality) በተለይም መጭውን ምርጫ አስመልክቶ ሊያስከትላቸው የሚችላቸውን ሁኔታዎች እንመርምር፡፡ በዚህ ግምታዊ ትንተና (Senario) መሠረት አንድነት እና መድረክ ውህደት ቢፈጥሩ ለምርጫው በአንድ ስያሜ እና የምርጫ ምልክት መቅረብ ሊጠቅባቸው ነው፡፡ ይህ ማለት የአላማ እና የፕሮግራም ልዩነት የላቸውም፣ ለህዝቡም የሚያቀርቡት ፕሮግራማዊ አስተሳሰብ አንድውጥ ነው ማለት ነው፡፡ በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ውስጥ ለማመላከት እንደተሞከረው፣ ሁለቱም የፖለቲካ ጐራዎች የሃገራችንን ችግሮች የሚተነትኑባቸው መነሻዎች እና እንዳሉ ለሚታመንባቸው ችግሮች ከሚያቀርቧቸው መፍትሄዎች አንጻር ሁለቱ የፖለቲካ ስብስቦች (አንድነት እና መድረክ) የሚለያዩባቸው የአመላካከት አንጓዎች አሉ፡፡

ዲሞክራሲ ማለት ሕዝቡን የመብቱ እና የሃገሩ ባለቤት እንዲሆን ማብቃት ነው፡፡ የመጀመሪያው የፖለቲካ ፓርቲዎች ሚና የሃገሪቱን መጻኢ አካሄድ በተመለከተ በህዝቡ ስነ-ህሊና ውስጥ ባልተቀናጀ እና በተበታተነ ሁኔታ የሚወጡ እና የሚወርዱ አስተሳሰቦችን በዘርፍ በዘርፍ በስርዓት በመደልደል፣ ጥሬት አርጎ በመተንተን፣ አንኳር አንኳር የሆኑት አስተሳሰቦች ጎልተው እንዲወጡ እና ሕዝቡ እንዲጨብጣቸው ማድረግ ነው፡፡ ተከታዩ ተግባር ፖለቲካ ፓርቲዎቹ በምርጫ ማኒፌስቶዋቻቸው አማካይነት አጉልተው ባወጡአቸው የፖለቲካ ጭብጦች መካከል፣ በነጻ እና ፍትሃዊ ምርጫ አማካይነት ሕዝቡ ምርጫውን እንዲያሳውቅ ማድረግ ነው፡፡ ከዚያ አመለካከቱ እና ፖሊሲዎቹ የአብዛኛውን ሕዝብ ድጋፍ ያገኘው ፓርቲ ወይም ፓርቲዎች ከምርጫው በኋላ በተናጠል ወይም በጥምር መንግስትነት ስልጣን ይዘው ፖሊሲዎቻቸውን ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡

በዋና በዋና የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ አመለካከታቸው የሚለያይ ፓርቲዎች አመለካከታችን አንድ ነው ወይም ተመሳሳይ ነው ብለው ለህዝብ ምርጫ ሊቀርቡ አይገባም፡፡ ይህ ዓይነት አካሄድ ሕዝብ የሚወናበድበትን ሁኔታ ስለሚፈጥር ትክክለኛ አካሄድ አይሆንም፡፡ በዋናዋና የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ልዩነት ያላቸው የፖለቲካ ልዩነታቸውን ማጠበብ ካልቻሉ ልዩነታቸውን ይዘው ነው ለህዝብ መቅረብ የሚጠበቅባቸው፡፡ ፓርቲዎች ልዩነታቸው እንደተጠበቀ በልዩ ልዩ ስያሜ እና በልዩ ልዩ የምርጫ ምልክት ለህዝብ ምርጫ ቀረቡ እንበል፡፡ ያገኙት ድምጽ ሁለቱንም መንግስትን ለብቻ ለመያዝ የማያበቃቸው ከሆነ፣ የምርጫ ማኒፌስቶአቸውን ይበልጥ በማሻሻል በተደጋጋሚ ምርጫ መንግስትን ለብቻ ለመቆጣጠር የሚያስችል ድምጽ ለማግኘት መምከር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ተቀናቃኝ አስተሳሰብ ካለው ሌላ የፖለቲካ ፓርቲ ጋር የጥምር መንግስት ለማቋቋም መሞከር ከአጭር ጊዜ እይታ አንፃር ካልሆነ በስተቀር ለዘለቄታው የሚጠቅም አይሆንም፡፡ በአንድ መንግስት ውስጥ ሁለት ተጻራሪ ፖሊሲዎች በአንድ ጊዜ ህግ ሊወጣላቸው እና ሊተገበሩ አይችሉም፡፡ በርከት ያለ ግን ለብቻው መንግስት ለመመስረት የማያስችል ድምጽ ያገኘ ፓርቲ በአመለካከት ከሚቀራረቡ ግን አነስተኛ ድምጽ ካገኙ ፓርቲዎች ጋር በማበር በድርድር መንግስት ቢመሰርት፣ በፓርላማ ውስጥ ህግ ለማሳለፍ የሚያስችል አቅም ሊያገኝ ይችላል፡፡

በመሠረታዊ የፖለቲካ ጥያቄ ዙሪያ በተለያየ ጎራ የተሰለፉ ፓርቲዎች ውህደት ፈጥረው በአንድ የፖለቲካ ፕላትፎርም በአንድ ስያሜ እና በአንድ የምርጫ ምልክት ለመራጩ ህዝብ ሊቀርቡ አይችሉም፡፡ ፕሮግራማቸው የሚያዋህዳቸው አይሆንም፡፡ እንለያይበታለን ብለው ባስቀመጡት መሠረታዊ የፖለቲካ አመለካከት ዙሪያ መለስተኛ የጋራ ፕሮግራም ነድፈው በጋራ ፕሮግራሙ ስር የምርጫ አካባቢያቸውን ከምርጫ በፊት ተከፋፍለው ወደ ምርጫ ሊገቡ አይችሉም ወይ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ የአመለካከት ልዩነታቸው በመሠረታዊ የፖለቲካ ጥያቄ ላይ እስካተኮረ ድረስ ይህን ዓይነት ልዩነታቸውን በመርህ ደረጃ ወደ መለስተኛ ልዩነት ደረጃ ሊያወርዱት አይችሉም፡፡ ማለትም ልዩነታቸው ስትራቴጂያዊ እንጅ ታክቲካዊ አይደለም ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ተፎካካሪ እንጅ ተደጋጋፊ ሊሆኑ አይችሉም ማለት ነው፡፡

ሁለቱም ወይም ከሁለቱ አንዱ በሃገርአቀፍ ደረጃ ለመወዳደር እስከ አቀዱ ድረስ ደግሞ ከምርጫ በፊት የምርጫ አካባቢን በስምምነት ሊከፋፈሉ አይገባም፡፡ የምርጫ ክልልን ከምርጫ በፊት በስምምነት ሊከፋፈሉ የሚገባቸው በዋና ዋና የሀገር ጉዳዩች ላይ አመለካከታቸው አንድ ዓይነት ሁኖ የፓርቲ ድርጅቶቻቸው በፓርቲ አደረጃጀት መርሆ ልዩነትም ሆነ በመሪዎች ስልጣን ክፍፍል አለመግባባት ምክንያት ድርጅታዊ ውህደት ሊፈፅሙ ያልቻሉ ፓርቲዎች ናቸው፡፡ ከምርጫ በኋላም ቢሆን ያገኙትን ድምጽ በማሰባሰብ የጥምር መንግስት ሊያቋቁሙ የሚገባቸው

ተመሳሳይ አመለካከት ያላቸው ፓርቲዎች ናቸው። ለሃገሪቱ ያላቸው ራእይ በመሠረታዊ ይዘቱ የሚለያይ፣ የተለያየ ፖሊሲ የሚያራምዱ ፓርቲዎች መንግስትን በጋራ ለመምራት አይቻላቸውም። ስለሆነም ግንኙነታቸው የህብረት/ግምባር ደረጃ ሊኖረው አይገባም። በዚህም ምክንያት ከውህደት እና ከህብረት/ ግምባር ውጭ ሶስተኛው የግንኙነት ዓይነት በሆነው በጥምረት/ቅንጅት መልክ አብረው ሊሰሩ ይችላሉ፣ ይገባልም። አንድነት ሃገራዊ የሆነውን የፖለቲካ ዓላማውን በመተግበር የህዝብን አመኔታ ለማግኘት የሚችለው በምክክር መድረኩ ውስጥ አንድ አባል ድርጅት(structural relationship) በመፍጠር/በመሆን ሳይሆን፣ ከምክክር መድረኩ ጋር የጥምረት ወይም የጉንዬሽ ግንኙነት (functional relationship)በመመስረት የፖለቲካ ዓላማውን በነፃነት ለማራመድ ሲችል ነው።

ይህን ሁኔታ ወደ ወቅቱ የሃገራችን ፖለቲካ እንተርጉመው። በመድረክ ዙሪያ የተሰበሰቡት እና አንድነት መሠረታዊ አመለካከታቸው ተመሣሣይ እንዲሆን ካልተስማሙ በስተቀር ከምርጫ በፊት የምርጫ ክልል ለመከፋፈልም ከምርጫ በኂላ በስምምነት የጥምር መንግስት ሊያቋቁሙ አይችሉም ወይ የሚሉ ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። በመድረክ ድርጅቶች በኩል አንድነትን እንደ አማራ ፓርቲ እና የከተማ ነዋሪዎች ፓርቲ አድርጎ የማየት ዝንባሌ እንዳለ ይነገራል። ይህ ግምታዊ አባባል ለዚህ ጽሁፍ ሲባል እውነት እንደሆነ አድርገን እንውሰድ እንበል። የሚኖረው አካሄድ (Senario) የሚሆነው ከምርጫ በፊት በሚደረግ ድርድር ከአማራው አካባቢ እና ከከተሞች ውጭ አንድነት ለምርጫ እጩዎች ሳያቀርብ፣ መድረክ ደግሞ ለአንድነት በተለቀቁ አካባቢዎች እጩዎች ሳያቀርብ፣ ምናልባት ደቡብን አስመልክቶ ሁለቱም ሊያቀርቡ እንዲችሉ ቅድመ ስምምነት ማድረግን የሚጠይቅ ሊሆን ይችላል። ባለፈው ቅንጅት እና ህብረት የተሳተፈበት የ1977 ምርጫ ይህን ዓይነት ስምምነት ያስተናገደ አልነበረም። ይህ አካሄድ በተለይ ለአንድነት ፓርቲ ሲጠቅም አይታይም። አንድነት በ2001 እሠራለሁ ብሎ ካስቀመጣቸው አምስት ታሳቢዎች መካከል ከዚህ ጉዳይ ጋር አግባብ ያላቸው ሁለቱ እንደሚከተው ይነበባሉ።

1. እስከ 2002 የምርጫ ጊዜ ድረስ የፓርቲያችንን የአንድነትን ፖለቲካዊ ተቀባይነት አጎልብቶ በመላ ሃገሪቱ ዋንኛ የኢህአዴግ ተፎካካሪ እና ታዋቂ ሃገራዊ የፖለቲካ ፓርቲ ሁኖ እንዲገኝ ማብቃት

2. በነዚህም ላይ በመመስረት በ2002 ሃገራዊ እና ክልላዊ ምርጫ ቢቻል ለብቻው ካልተቻለም ከአጋር* የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በማበር የመንግስት ስልጣን ለመያዝ ወይም ለመጋራት የሚያበቃውን ከ327 በላይ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቀመጫዎችን እና የክልል ምክር ቤቶችን አብላጫ መቀመጫዎች መያዝ/ መቆጣጠር ናቸው ይላል።

ስለሆነም አንድነት ከምርጫ በፊት ህብረት/ወይም የጋራ ግንባር በመመስረት በአንድ የምርጫ ማኒፌስቶ አማካይነት ቢጋራ ለምርጫ ሊቀርብ የሚችለው ከምርጫ በኂላ የጥምር መንግሥት ሊያቋቁም የሚችለው ከአንድነት ፓርቲ የተለየ የፖለቲካ አመለካከት ከሚያጠነጥኑት በመድረክ ዙሪያ ከተሰባሰቡት የፖለቲካ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ጋር ሳይሆን፣ ከምርጫ በኂላ በሚያገኙት የህዝብ ድምጽ መጠን በአንድነት ሀይሎች ጉራ ስር ሊካተቱ ከሚችሉት በነፃነት ከተደራጁት እና ከሚንቀሳቀሱት ከኢህአዴግ ጋር ንክኪ ከሌላቸው አገር አቀፍ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ነው ሊሆን የሚገባው።

የሃገር አቀፍ አቋም ይዞ ጠንክሮ የቤት ስራውን ከሠራ፣ በመላ ኢትዮጵያ ተቀባይነት አለኝ በሚል እምነት የተቋቋመ እና ይህንንም በተልእኮ መልክ ቀርጾ ያስቀመጠ ፓርቲ፣ ለህዝብ ምርጫ ቀርቦ ተቀባይነት ማግኘቱን እና ማጣቱን ሳያረጋግጥ ቀደም ብሎ የምርጫ ክልልን ለመከፋፈል ቢስማማ፣ ለዚህ ድርጊት የሚሰጠው ትርጉም ሁለት አይነት ይሆናል። አንደኛው ትርጉም አንድነት በቅርጽ እንጅ አገርአቀፍ ፓርቲ ነኝ ብሎ የቀረበው፣ ከምርጫ በፊት የምርጫ ክልሎችን የመከፋፈል ስምምነት ከመድረክ ጋር ቢደርስ፣ በሌሎች አካባቢዎች የማሸነፌ እድል ጠባብ ነው ብሎ አምኗል ማለት ነው። ይህም በይዘት የአማራ እና የከተማ ነዋሪ ፓርቲነኝ ብሎ ማመኑን ያረጋግጣል። ሁለተኛ በሌሎች ክልሎች የሚኖረው ህዝብ ከኢትዮጵያ የብሄረተኝነት ስሜቱ ይልቅ የክልል በሄረተኝነት ስሜቱ ያይልበታል የሚባለውን አባባል አንድነት ተቀብሎታል ማለት ነው። ከዚህ ዓይነት ግምት መነሳት ስህተት ከመሆኑም በላይ ህዝቡን ትክክለኛ አማራጭ ማሳጣት ይሆናል።

----------------

*አጋር ፓርቲዎች የሚለው የሚያመለክተው ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ፕሮግራም ያላቸውን የፖለቲካ ፓርቲዎች ነው።

ይህን ነጥብ በተመለከተ ጉልቶ አኢሳ የተባሉ የደቡብ ኢትዮጵያ ተወላጅ **<u>በአዲስ ነገር</u>** ጋዜጣ ባወጡት ጽሁፍ ላይ የሚከተለው ሰፍሮ ይገኛል።

> በሚገርም ሁኔታ የሌ/ኮ/ል መንግስቱ ሃይለ ማሪያም ዘመን መምጣት ደቡብ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሰሜኖች ጋር ራሱን የኢትዮጵያ ታሪክ ተካፋይ እንደሆነ የቆጠረበት ጊዜ ነበር።... ይህ [የአሁኑ] መንግሥት ከአንድነት ይልቅ ልዩነቶችን በማድመቅ ላይ የተወሰነ እንደመሆኑ በአሁኑ ወቅት ለብዙ ዘመን በደቡብ ተጎራብተው የኖሩ ሕዝቦች ከመቸውም ጊዜ ይልቅ እረስበርስ ይጋጫሉ። ... ኢትዮጵያን የመቆራረጥ ስትራቴጂ ለማንም አያዋጣም፤ መክንያቱም ማንም ራሱን ሳይቆራረጥ ኢትዮጵያን መቆራረጥ የሚችል የለምና ... የሕዝቦችን የጥንት ብሶት በመቆስቆስ ላይ የተመሠረቱ ፖለቲካዊ ስትራቴጂዎች ለአገራችን የሚያበረክቱልን ብቸኛ ነገር ጥፋት ነው። ይልቁንስ የሚያስፈልገን ከባለፈው ስህተት ተመክሮ ወስደን እንዴት የነገ ችግሮቻችን እንደመንፈታ አቅጣጫ የሚያሳዩን ጠቋሚዎችን ነው።

ከዚህ አባባል ለመገንዘብ የሚቻለው ቁምነገር የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝብ የኢትዮጵያ ብሄረተኝነትን እንደ ብቸኛ አለኝታው አጥብቆ መያዙን ነው። አስተዳደራዊ ተጽእኖው አመች ባለመሆኑ ሃገራዊ ፓርቲዎች በልዩ ልዩ የሃገሪቱ አካባቢዎች ለመንቀሳቀስ የማያመቻቸው ሁኖ ነው እንጅ በሌሎችም የኢትዮጵያ አካባቢዎች ይኸው ተመሳሳይ ስሜት ለመኖሩ ጥርጥር የለውም። የ1997 ምርጫ በአጭር ባይጨናገፍ እና ውጤቱ እንደተድበሰበሰ ባይቀር ኑሮ ሊያረጋግጥ ይችል የነበረው ሃቅ ከዚህ ሊርቅ የሚችል አልነበረም።

## 5. አሁን ካለው የፖለቲካ አሰላለፍ አንፃር ለአንድነት ከውህደት፣ ከግንባር እና ከጥምረት ግንኙነት የትኛው ተመራጭ ይሆናል??

አንድነት በመደረክ ውስጥ ከተሰባሰቡት ድርጅቶች ጋር ከአጭር እና ከመካከለኛ ጊዜ አንጻር ሊዋሃድ የሚችል ያለመሆኑ፣ ህብረት ወይም ግንባር መመስረቱም አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ ቀደም ሲል በቀረበው ትንተና ለማብራራት ተሞክሯል። "ገዥውን ፓርቲ ለመጣል ሃይል ማሰባሰብ" የተሰኘው ስልትም ስትራቴጂያዊ እይታ መኖርን አያመለክትም። የአንድነት የመጨረሻ እና ብቸኛ ዓላማ ደግሞ ኢህአዴግን ከስልጣን ማውረድ ብቻ መሆን የለበትም። አንድነት ከመድረክ ጋር በጥምር መንግስት አማካይነት ኢህአዴግን አሸንፎ ስለጣን ቢይዝ በፕሮግራሙ መግቢያ አንቀጽ 2 ውስጥ እንደተጠቀሰው የመጀመሪያ ተግባሩ ሕገመንግስቱ የሚሻሻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት እና ለዚህም ቅድመ ሁኔታ የሆነውን የሕግ መንግስት ማሻሻያ ረቂቅ ህግ በፓርላማ እንዲጸድቅ ማድረግ ነው። የሚሻሻሉ አንቀጾች አንድነትን እና መድረክን ሊያግባቡ የሚችሉ አይደሉም። አንድነት ከመድረክ ጋር በጋራ አብዛኛውን መቀመጫ የሚቆጣጠርበት ሁኔታ ቢከሰት ሕገ መንግስቱን ለማሻሻል መነሻ የሚሆነውን የሕግ ረቂቅ ለፓርላማ ድምጽ እንዲሰጥበት አንድነት ቢያቀርብ፣ መድረክ ከአቋሙ በመነሳት ድጋፍ እንደሚከለክል መገመት ይቻላል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ አንድነት ስልጣን ተጋርቶም ህገ መንግስቱን ለማሻሻል (Constitutional Reform) የማይችልበት ቅርቃር ውስጥ ሊገባ ነው። በዚህ ሁኔታ ስልጣንም ተጋርቶ የመረጠውን ህዝብ ፍላጎት ለማርካት ሳይችል በመቅረቱ ህዝባዊ ተቀባይነቱን ረዘም ሳለ ጊዜ የማጣት እድሉ ከፍ ያለ ይሆናል።

ይህ እንደተጠበቀ ሁኖ በ1997 ምርጫ ዋዜማ ቅንጅት እና ህብረት አካሄዳቸውን ለማቀናጀት ጀምረውት የነበረው ጥረት በምን መልኩ ማሳረጊያ እንደተሰጠው ሁሉም የሚያውቀው ነው። ያ ክስተት የራሱን ልምድ ጥሎ አልፏል። የጣለውም ልምድ ቅሬታን ያስከተለ ስለነበር በመጭው ሂደት ላይ ስጋትን በመጫር ረገድ አስተዋጽኦ ሊኖረው እንደሚችል አስተያየቶች ሲሰነዘሩ ይደመጣል።

መድረክ እና አንድነት ከምርጫ በፊት ግንባር በመመስረት የምርጫ አካባቢዎችን ቢከፋፈሉ፣ አንድነት በ2001 አከናውናለሁ ብሎ ያቀዳቸውን ተግባሮች ለጋራ ግንባሩ የጋራ ፕሮግራማዊ እቅድ ማስገዛት ሊጠበቅበት ነው። ይህ ደግሞ እስከ ምርጫው ድረስ በራሱ ሂደት አከናውናቸዋለሁ ብሎ ካቀዳቸው ድርጊቶች መካከል ከመድረክ ጋር በጋራ ለሚነድፈው መርሃግብር መሳካት ሲባል፣ የተወሰኑትን ማጠፍ ሊገደድ ነው። በዚያው መጠን ለሃገራዊ ተቀባይነት የሚያደረገው ሁለገብ ጥረት ሊዳከም ነው። ሐምሌ 22/2000 የምክክር መድረኩ ባወጣው የውስጥ አሠራር ደንብ ላይ እንደተመለከተው የመድረኩ መዋቅር ከሀገር አቀፍ እስከ ወረዳ የሚዘረጋ እንደሚሆን ተመልክቷል። አንድነት ከመድረክ ጋር ግንባር ቢመሠረት ለጋራ ግንባሩ መርሃ ግብር መሳካት የፋይናንስ እና የሰው ሃይል አስተዋጽኦ ማድረግ ሊጠበቅበት ነው። ይህ ደግሞ የራሱን አቅም የመገንባቱን ጥረት የሚያዳክም ነው።

በመድረኩ ውስጥ ያሉት የብሄረሰብ ድርጅቶች አምስት ሲሆኑ በስብስቡ ውስጥ እያንዳንዳቸው ድርጅቶች ሊኖራቸው የሚችለው ድምፅ ተመጣጣኝ ነው። አንድነት ከመድረኩ ጋር በግንባር ደረጃ ለመስራት ቢወስን፣ የሚኖረው ድመጽ ለሌሎች አባል የፖለቲካ ድርጅቶች የሚሰጠው ድምጽ ነው ሊሆን የሚችለው። እስከምርጫው ድረስ በሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች በአንድነት እና በመድረኩ ሌሎች አባል ድርጅቶች መካከል

ልዩነት ቢከሰት፣ በመድረኩ ውስጥ የሚኖረው የድምጽ ልዩነት አንድነትን በሚደግፍ ሁኔታ መፍትሄ እንዲያገኝ ለማድረግ አያስችለውም። ይህ ደግሞ አንድነት እራሱን ለህዝብ ለማስተዋወቅ ያለውን እድል በማጥበብ መለያ ጠባዩን ሊያሳጣው ይችላል።

በሌላ በኩል ከምርጫ በፊት አንድነት እና መድረክ የጋራ ግንባር ቢፈጥሩ የጋራ ግንባሩን የውጭም ሆነ የሃገር ውስጥ ተቀባይነት ሊያጎላው ይችላል፤ ገዥውን ፓርቲ ኢህአዴግን ለመፎካከር ይበልጥ አመች ሁኔታ ያስገኛል፣ በተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል ያለውን ልዩነት ለማጥበብ አመች ሁኔታ ይፈጥራል፤ ለሰላማዊ ትግሉ መጎልበት የጋራ ግንባሩ ይበልጥ የሚያግዝ ይሆናል፤ በኢህአዴግ ላይ በተቃዋሚዎች ሊፈጠር የሚገባውን ተጽእኖ ይበልጥ ያጠናክረዋል የሚሉ ጠንከር ያሉ አስተያየቶች ሊሰነዘሩ ይችላሉ።

ለወደፊቱም አካሄዳችን መሆን ያለበት ከዳር እስከዳር ያለው የኢትዮጵያ ህዝብ ሁሉቱም የፖለቲካ አማራጮች በግልጽ ተዘርዝረው ቀርበውለት ይበጀኛል የሚለውን አማራጭ እንዲመርጥ በማስቻሉ አስፈላጊነት ላይ ነው ማተኮር ያለብን ብሎ ይህ ጽሁፍ ያምናል። ከህዝብ ጻርባ እና ከህዝብ ነጻ ምርጫ በፊት የፖለቲካ ልሂቃኑ በመሰረታዊ የህዝብ ጥያቄ ላይ ተደራዳሪ እና ወሳኝ ሊሆኑ አይገባም። ምርጫ ደግሞ ነጻ እና ፍትሃዊ ሊባል የሚችለው አፋኝ የሆነ መንግሥት በነጻ እና ፍትሃዊ ምርጫ አፈፃፀም ላይ የጣለውን አፍራሽ ማእቀብ በማንሳቱ ላይ ብቻ ሳይሆን፣ ግልጽ የሆኑ የፖለቲካ አማራጮች ለህዝብ መቅረባቸውም ሲረጋገጥ ነው።እንደሚታወቀው ማናቸውም እራሱን በፖለቲካ ፓርቲነት ያደራጀ ስብስብ ተቀዳሚ ተልእኮው በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ተቀባይነት አጎልብቶ፣ ብዙሃኑ ህዝብ እንዲመርጠው እና ለስልጣን እንዲያበቃው መስራት ነው። በህዝብ ነጻ እና ፍትሃዊ ምርጫ ለብቻው የመንግስት ስልጣንን ለመቆጣጣር የተቻለውን ያህል የፖለቲካ ስራ መስራት በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ማናቸውም በሃገር አቀፍ ደረጃ የተዋቀረ የፖለቲካ ፓርቲ ተቀዳሚ አላማ ሊሆን ይገባል።

ከምርጫ በፊት እሰራቸዋለሁ ብሎ ያቀዳቸው ተግባሮች ላይፈጸሙ ይችሉ ይሆናል የሚል ስጋት ካለው ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር የቅድመ ምርጫ ትብብር/ ግንባር ወዘተ ሊመሰርት ይችላል። ይህ አካሄድ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ተደጋፊነት ቢኖረውም፣ ተግባራዊ ክንውኑ እንደተጨባጩ ሁኔታ የሚወሰን ይሆናል። በመርህ ደረጃ በአንድ ነገር ክንውን ላይ ሁለት ድርጅቶች የጋራ ተጠቃሚ ነን ብለው ሲያምኑ፣ ለዚያ ነገር መከናወን ሃይላቸውን አቀናጅተው በጋራ ሊሰለፉ በትብብር ሊሰሩ ይችላሉ።እንዲከናወን የሚፈልጉት ነገር ያለውን መንግስታዊ ፓርቲ በምርጫ አሸንፈው ስልጣን መያዝን የሚመለከት ሲሆን፣ የሚመሰረተው የፓርቲዎች ጥምረት ስልጣን በሚይዘበት ጊዜ የሚተረጎመው ፖሊሲ **__በመሠረታዊ ይዘቱ የማይጻረር እንዲሆን ይጠበቅበታል__**። ከእስትራቴጃዊ ግብ አንጻር ተጻራሪ ፖሊሲ እያራመዱ አንድን መንግስት በአንድ ጊዜ መምራት አይቻልም። ስለሆነም ተመሳሳይ ፖለቲካዊ አቋም በማያራምዱ የፖለቲካ ድርጅቶች/ፓርቲዎች መካከል የቅድመ - ምርጫም ሆነ የድህረ - ምርጫ የፓርቲዎች ትብብር መሠረት ሊሆን የሚገባው ሊያስማሟቸው በሚችሉ የጋራ ጉዳዮች ላይ ማተኮር ነው። የእስራኤልን የሰሞኑን ምርጫ ውጤት እና የመንግሥት ስልጣን ለመያዝ ከምርጫ በኂላ የፓርቲዎችን አሰላለፍ በጥሞና መመልከቱ ጠቃሚ ልምድ ሊያስጨብጥ ይችላል።

የከዲማ ፓርቲ መሪ ዚፒ ሊቭኒ በምርጫው አሁን ስልጣን ከያዘው የቀኝ ክንፉ ሊኩድ ፓርቲ መሪ ቤንጃሚን ናተኒያሁ የአንድ ፓርላማ መቀመጫ ብልጫ ነበራቸው። ይሁንና አዲስ መንግሥት በማቋቋም ላይ የሚገኙት የምርጫ አሸናፊዋ ዚፒ ሊቭኒ ሳይሆኑ ተመሳሳይ አመለካከት ያላቸውን ሌሎች አነስተኛ ፓርቲዎች ለማስተባበር የቻለው የሊኩድ ፓርቲ መሪ ናቸው ። በአንፃሩ ዚፒ ሊቭኒ ከሳቸው ፓርቲ ፕሮግራም ጋር የሚቀራረቡ አነስተኛ ፓርቲዎች ስላላገኙ፣ በእስራኤል ፓርላማ (ክነሴት) የፓርቲያቸውን ፖሊሲ ለማስፈፀም ያብላጫ ድምጽ እንደማይኖራቸው ተገንዝበው በምርጫ ያገኙትን መንግሥት የመመስረት ኃላፊነት ለቀቁ። የሰለጠኑ ፓርቲዎች ስልጣንን እንደ ግብ ሳይሆን እንደመሣሪያ እንደሚጠቀሙት የሚያሳይ ተጨባጭ ምሳሌ ነው።

መሠረታዊ ባልሆኑ እና በሚያግባቡ ጉዳዮች ላይ የሚመሠረተው ትብብር ደግሞ በህብረት መልክ ከሚገለጽ የጋራ ግንባር ማቋቋም በመለስ በእያንዳንዱ ጉዳይ ዙሪያ የሚደረግ ትብብር ሊሆን ነው የሚገባው። በአንድ የግንባር የመግባቢያ ሰነድ ላይ መስማማትን፣ በሂደት ወደላቀ የህብረት ደረጃ ማለትም ከምርጫ በፊት የምርጫ ክልሎችን እና ወረዳዎችን ወደ መከፋፈል ማምራትን የሚጠይቅ ቢሆን፣ ይህን አካሄድ ማስተናገድ ለአንድነት ፓርቲ ስትራቴጂያዊ ዓላማ ጠቃሚ ሲሆን አይታይም።

ላለፉት ሰላሣ አመታት የኢትዮጵያን ፖለቲካ ሰንገው በያዙት የኢትዮጵያ ብሄረተኝነት (Ethiopian Nationalism) እና ክልላዊ ብሄረተኝነት (Ethnic Nationalism) መካከል ሲካሄድ የቆየው ፍልሚያ መፍትሄ ሲያገኝ የቆየው በመሳሪያ ትግል አማካይነት ነው። የመጨረሻውም የ1997 ምርጫ ውጤት አሸናፊ በውል ሳይለይ የተደመደመው በወታደራዊ ሃይል አማካይነት ነው። የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሊሂቃን የስልጣን ምንጭ ህዝብ ነው የተሰኘውን ዝነኛ አባባል እንደዳዊት ሲደግሙት የኖሩ ቢሆንም፣ ይህን አባባል ወደ ተግባር ለመተርጎም ግን በእጅጉ ሳይቻላቸው ቀርቷል። ከ1966 ህዝባዊ አብዮት ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ ብሄረተኝነት እና በክልል ብሄረተኝነት መካከል ከአርባ አመታት ላለፈ ጊዜ ሲካሄድ የቆየው ወንድማማቾችን ደም ሲያፋስስ የቆየው እና የዚችን አገር ልማት ቀፍድዶ የያዘው በሃገሪቱ የፖለቲካ

ልሂቃን መካከል ያለው የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት ጉዳዩ በቀጥታ በሚመለካተው ህዝብ ነጻ ምርጫ ቢፈታ ነው ለሃገር ጠቃሚ የሚሆነው። ይህ ጥያቄ በጦርነትም ሆነ ከህዝብ ጀርባ በሚደረግ የፖለቲካ ልሂቃን ድርድር የሚፈታ አይደለም፣ ሊሆንም አይገባም።

በመድረኩ ስብስብ የታቀፉ የፖለቲካ ድርጅቶች የካቲት 12/2001 ባወጡት የጋራ መግለጫ ሁለት ነጥቦች ግልፅ ሁነዋል።

1ኛ/ የመድረኩን ስብስብ ቀድመው በሰኔ ወር 2000 ዓ.ም የመሠረቱት ስድስት የክልል የፖለቲካ ድርጅቶች እና ሁለት ታዋቂ የፖለቲካ ሰዎች በቅርቡ እንደተቀላቀሏቸው በመግለጫው ውስጥ የተጠቆሙት ሁለት አገር አቀፍ የፖለቲካ ድርጅቶች መድረኩን የተቀላቀሉት ቀደምቶቹ ሐምሌ 22/2000 ዓ.ም ባፀደቁት ውስጠ-ደንብ መሠረት ነው። ይኸው ውስጠ ደንብ ባለበት መልኩ የተሳታፊ ፖለቲካ ድርጅቶችን አመኔታ በማግኘቱ ከመድረኩ የጋራ መርሃግብር ጋር ለምርጫ ቦርድ በሚቀርብበት ጊዜ መድረኩ ህጋዊ ይሆናል ማለት ነው።

2ኛ/ የመድረኩ አባል ድርጅቶች ለምርጫ የሚቀርቡት በጋራ ለምርጫ ለመቅረብ የሚያስችል ማኒፌስቶ በማዘጋጀት ነው። መግለጫው በገፅ 2 ላይ በግልፅ እንዳስቀመጠው "**ወደፊት መድረኩ በፓርቲዎች አዋጅ መሠረት ለሚፈጠረው የትብብር ደረጃ የሚሆን ማኒፌስቶ ያዘጋጃል**" ይላል።

የካቲት 12/2001 የመድረኩ አባል ድርጅቶች ባወጡት የጋራ መግለጫ መሠረት "መድረክ ለዲሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ/መድረክ የተባለውን ስብስብ ስድስት የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ሁለት ታዋቂ የፖለቲካ ሰዎች በሰኔ ወር 2000 ዓ.ም ላይ የጀመሩት .... መጀመሪያ በተወሰኑ መርሆዎችና ግቦች ዙሪያ ሊሰባሰብ የሚችለውን ሀይል የማሰባሰብን እና በዚህ ጥላ ስር ሁኖ ለሚቀጥለው ስራ አስፈላጊ የሆኑትን ቅድመ ዝግጅቶች እያካሄዱ የመቆየትን ስልት መርጦ በዚሁ መሠረት ሲንቀሳቀስ ቆይቶአል" በሚል የሰፈረው አባባል ወደፊት ሊለወጥ ቢችልም፣ ውስጠ ደንቡ የሚመራባቸው መርሆዎችና ግቦች መኖራቸውን ያመለክታል። ሐምሌ 22/2000 በስብስቡ አባላት የፀደቀው የመድረኩ ውስጠ ደንብ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 2.1 "የምክክር መድረኩ አባላት የተስማሙበትን መስፈርት ያሟሉ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ቡድኖች እና ታዋቂ ግለሰቦች የምክክር መድረኩ አባል መሆን ይችላሉ። የአዲስ አባላትም ቅበላ በሙሉ ስምምነት ይሆናል" ይላል።

መጋቢት 30/2001 በወጣው ሰንደቅ ጋዜጣ ላይ አቶ ገብሩ አስራት የመድረኩ ስብስብ ፓርቲዎችን በአባልነት የሚያሰባስበው ባወጣቸው በባለ 5 ነጥብ መርሆዎች አማካይነት እንደሆነ ጠቁመዋል። እነሱም 1ኛ/ ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት እና አንድነት መቆም 2ኛ/ የግለሰብ፣ የብሄር ብሔረሰቦችና የቡድን መብቶች በተንዳኝነት ማስከበር፣ 3ኛ/ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለገደብ እንዲከበሩ ማድረግ 4ኛ/ የፍትህ ስርዓት ተዘርግቶ የሕግ የበላይነት በተግባር እንዲገለፅ ማድረግ 5ኛ/ ሰብዓዊ መብት በሁለንተናዊ መልኩ መከበር የሚሉ እንደሆኑ አብራርተዋል። ከሶስት እስከ አምስት ያሉት ሁሉም የሚስማማባቸው ስለሆኑ የትብብር መሠረት ሁነው ሊያገለግሉ ይችላሉ። ቀደም ባሉ ገፆች ለማብራራት እንደተሞከረው በአንቀፅ 39 የሰፈረው "የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል" ለሚለው አስተሳሰብ ድጋፍ መስጠት እና የኢትዮጵያ መንግሥት ፌደራላዊ አወቃቀር ብቸኛ መመዘኛ ቋንቋ/ብሄረሰብ መሆኑን መቀበል፣ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት መግለጫ ብሄር ብሄረሰቦች ናቸው የሚለውን አመለካከት ማራመድ ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት እና አንድነት መቆምን ያመላክታል ለማለት አይቻልም። ይህ የልዩነት ነጥብ በመሆኑ የትብብር መሠረት ሊሆን አይችልም።

የግለሰብ፣ የብሄር ብሄረሰቦች እና የቡድን መብቶች በተንዳኝ ማስከበርንም በተመለከተ ሃገር አቀፍ ፓርቲዎች እና የክልል ፓርቲዎች የሚያራምዱአቸው አመለካከቶች ለየቅል ናቸው። ባለፉት ገፆች ለማመላከት እንደተሞከረው በአንዳንድ የምእራቡ ዓለም አገሮች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተተገበረ በመሄድ ላይ ከሚገኘው የበሃውርታዊ ፌደራሊዝም (Multi-national Federalism) የሚቀሰመው ልምድ ግልፅ ነው። ለውል ወይም የብሄር መብቶች በመደላድልነት ያገለገለው ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ ተግባራዊ ሁኖ የቆየው የግለሰብ ወይም ዜግነት መብት ነው። ግለሰብ የማህበረሰብ መነሻ መሠረት ነው። በመብትም ረገድ ቀዳሚውን ስፍራ ሊይዝ የሚገባው የግለሰብ መብት ነው። ለምሳሌ በመረጠው ቋንቋ የመጠቀም መብት በመሰረቱ የግለሰብ መብት ነው። ይሁንና የዚህ መብት ተግባራዊነት ሊገለፅ የሚችለው በወል በመሆኑ ይህን መብት ለማስከበር አብሮ መሄድ ያለበትን ለዚህ መብት ተግባራዊነት የሚመች መንግሥታዊ የአወቃቀር ዘይቤን መጠቀም ነው። የግለሰብ እና የወል መብት እንደአግባቡ መከበር ያለባቸው ቢሆንም ለወል መብት መሠረቱ የግለሰብ መብት መሆኑ ተገቢ ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባል። በአንፃሩ የክልል የፖለቲካ ድርጅቶች የግለሰብ እና የወል መብት በተንዳኝነት ሊከበሩ ይገባል ሲሉ፣ በሃገር አቀፍ ደረጃ የተቋቋሙ ፓርቲዎች የግለሰብ የዜግነት መብት ከመብቶች ሁሉ የላቀ መብት ነው ብለው ስለሚያምኑ ይህ ጥያቄ የልዩነት ነጥብ ነው። የመድረክ ስብስብ የፖለቲካ ድርጅቶች ካወጧቸው ባለ 5 ነጥብ የመሰባሰቢያ መመዘኛዎች መካከል፣ የማያከራክሩ እና የትብብር መሠረት ቢሆኑ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት የሚኖራቸው መርሆዎች 3ኛ/ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለ ገደብ እንዲከበሩ ማድረግ፣ 4ኛ/ የፍትህ ስርዓቱ የሕግ የበላይነት በተግባር ሊገለፅ የሚችልበት ሁኖ እንዲሠራ ማድረግ፣ 5ኛ/ የሰብዓዊ መብት በሁለንተናዊ መልክ እንዲከበር ማድረግ፣ የሚሉት ብቻ ናቸው።

በየካቲት 12/2001 መግለጫ ግልፅ የሆነው ሌላው ጉዳይ የመድረኩ አባላት ለምርጫ የሚቀርቡት በ1997 ምርጫ በቅንጅት ውስጥ የታቀፉት እና በኋላ ድርጅታዊ ውህደት ለመፍጠር ተስማምተው የነበሩት አራቱ ብሄር-ዘለል የፖለቲካ ድርጅቶች በጋራ ተስማምተው እንደነበረው የምርጫ ማኒፌስቶ ለማዘጋጀት መስማማታቸው ነው። በቅንጅት ውስጥ ታቅፈው የነበሩት አራቱ ድርጅቶች አንድ ወጥ የምርጫ ማኒፌስቶ አዘጋጅተው ለምርጫ ቢቀርቡ፣ ፕሮግራሞቻቸው ብቻ ሳይሆን ድርጅቶቻቸውን ለማዋሃድ ቅድሚያ ስምምነት በማድረጋቸው ነበር። ሐምሌ 22/2000 በመድረኩ ስብሰብ አባላት ስምምነት ላይ የተደረሰበት የምክክር መድረክ የውስጠ አሠራር ደንብ አንቀፅ 6 "ወደፊት ሊኖር ለሚችለው አደረጃጀትና የምርጫ ስትራቴጂና ስልት" እንደሚዘጋጅ ይደነግጋል። በዚህም መሠረት የካቲት 12/2001 የወጣው የጋራ መግለጫ "መድረኩ በፓርቲዎች አዋጅ መሠረት ለሚፈጠረው የትብብር ደረጃ የሚሆን ማኒፌስቶ ያዘጋጃል" ይላል። በጋራ የምርጫ ማኒፌስቶ ማዘጋጀት በአንድ ስያሜ እና በአንድ የምርጫ ምልክት ለመራጩ ህዝብ መቅረብን የሚጠይቅ ነው። ይህን ለማድረግ በስብሰቡ ውስጥ የታቀፉ ህብረብሄር እና የብሄር ድርጅቶች በህግ ከተደነገጉት የፖለቲካ ድርጅቶች የትብብር አይነቶች ማለትም ከውህደት ከግንባር እና ከጥምረት መካከል ቢያንስ ግንባር/ህብረትን ለመመስረት እንዲሳሰቡ የሚጠቁም ነው።

ውህደት በአንድ ስያሜ እና በአንድ የምርጫ ምልክት ለመራጩ ህዝብ ከመቅረብ በተጨማሪ፣ ድርጅታዊ ውህደትን ለመፈፀም መስማማትን ይጠይቃል። ሶስተኛው አማራጭ ጥምረት በጋራ ጉዳዩች ላይ የሚደረግ ትብብር (Functional Relationship) እንጅ መዋቅራዊ ትስስርን (Structural Relationship) አይጠይቅም። ይህ ቀመር (modality) የምርጫ ተሳትፎን የመወሰን ጉዳይን በተመለከተ ካልሆነ በስተቀር የጋራ የምርጫ ማኒፌስቶ ማዘጋጀትን አይጠይቅም። ከነዚህ ከሶስቱ መካከል በአንዱ ላይ በቅድሚያ ስምምነት ሳይደረስ፣ ስለጋራ የምርጫ ማኒፌስቶ ዝግጅት ማውሳቱ ከፈረሱ ጋሪውን ያስቀደመ ግልፅነት የጐደለው አካሄድ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ቅንጅት ይፋ ያደረገው የዲሞክራሲያዊ ተቋማት ምስረታ ጥያቄ ሳይፈታ በማናቸው መልኩ ለምርጫ ቢቀርብ ኢህአዴግን ማሸነፍ አይቻልም። በዲሞክራሲያዊ ተቋማት ምስረታ የምርጫ ቅድመ ሁኔታ በመሆኑ ላይ በመድረኩ በተሰባሰቡ ድርጅቶች መካከል የማያወላዳ ስምምነት ሳይኖር የሚደረግ የምርጫ ተሳትፎ ኢህአዴግን ከማጀብ አይዘልም። ተዓምር ተፈጥሮ ኢህአዴግ የስልጣን ቆይታዬ ይበቃኛል ብሎ የመድረኩ ስብስብ በመጭው ምርጫ ኢህአዴግን ቢያሸንፍ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ከተመዘገቡት ሁለት አስገራሚ ክንውኖች በተጨማሪ ማለትም በረዥም ርቀት ሩጫ ሁልጊዜ ማሸነፍ እና ማባሪያ በሌለው የርሃብ ቸነፈር ያለማቋረጥ መጠቃት በሶስተኛ አስገራሚ ክንውንነት ሊመዘገብ ነው። ክንውኑን አስገራሚ የሚያደርገው ምርጫውን ማሸነፉ ሳይሆን ምርጫውን ተከትሎ የሚነሱ በርከት ያሉ ጥያቄዎች የሚፈቱበት ዘዴ ነው።

አሁን የመድረኩ ስብስብ በሚከተለው የአሠራር ቀመር መሠረት መድረኩን የተቀላቀሉት በሀገር አቀፍ ደረጃ የተቋቋሙት የፖለቲካ ድርጅቶች በየቶቹ ክልሎች ነው እጩዎቻቸውን የሚያቀርቡት? ሃገር አቀፍ ፓርቲዎች በተወሰነ ክልል ወይም ምናልባት በከተሞች ብቻ ከሆነ እጩዎቻቸውን ለምርጫ ለማቅረብ የሚስማሙት "**ሃገር አቀፍነታቸው**" ምኑ ላይ ነው? ይኽ ታልፎ ምርጫውን ቢያሸንፉ እጃቸው ላይ የሚወድቀውን የመንግሥት ስልጣን በምን ቀመር አማካይነት ነው የሚከፋፈሉት?? የአሁኑ የስብስቡ ደንብ በደነገገው ለአባላቱ እኩል መብት በሚሰጠው ደንብ መሠረት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን እኩል እኩል መካፈሉ ያስማማቸው ይሆን? የጠቅላይ ሚኒስትሩን እና የፕሬዚዳንትነቱን ቦታ የትኛው የፖለቲካ ድርጅት ወይም የትኞቹ ድርጅቶች ሊደርሳቸው ነው?? ይህ አስቸጋሪ ጥያቄ መነሳቱ ስለማይቀር በዚህ ጥያቄ ዙሪያ በመድረኩ አባል የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ከፍተኛ ውዝግብ መነሳቱ አይቀሬ እንደሆነ ይገመታል። ውዝግቡን ለመፍታት ሊኖር የሚችለው ፍቱን ዘዴ የማናቸውም ፓርቲ አባል ያልሆኑትን ሁለቱን ታዋቂ ግለሰቦች ጠቅላይ ሚ/ር እና ፕሬዚዳንት ማድረግ ሊሆን ይችላል። የፓርቲ አባል ሳይኮኑ ስልጣን የሚያዙበት ቀመር ምናልባትም ኢትዮጵያ የምትታወቅበት አራተኛው ተዓምራዊ ክንውን ሊሆን ይችላል። በመጭው ምርጫ ኢህአዴግ ቢሸነፍ በሚለው ስሌት መሠረት በአሸናፊዎቹ የመድረክ አባል ድርጅቶች መካከል የሚነሳው የስልጣን ሹክቻ መፍትሄ ሳያገኝ ቢዘገይ እና በዚምባብዌ እንደተከሰተው ተሸናፊው ኢህአዴግ የሠራዊቱን የደህንነቱን እና የፖሊሱን የእዝ ሰንሰለት አመራር እንደያዝኩ እቆያለሁ ቢል፣ የመድረክ ስብስቡ ችግሩን የሚፈታበት ዘዴ ይኖራል? ዘዴው በወቅቱ ይገኛል ሊባል ይችል ይሆናል። ይኽ አይነት አካሄድ በጠባዩ ለህዝቡ ግልፅ ሊሆን ስለማይችል የመድረኩ ስብስብ በህዝቡ ላይ ሌላ ዙር አምባገነንነት ላለመጫኑ ምን ዋስትና ይኖራል?? የሁኔታው ውስብስብነት መፍትሄ የሚገኝበትን ጊዜ ቢያራዝመው፣ በምርጫ የተሸነፈው ፓርቲ (በዚህ ግምት መሠረት ኢህአዴግ) የሠራዊቱን አመራር አለቅም ቢል ዙሪያ ገባ በደህንነት ስጋት የታጠረች ኢትዮጵያን ሀገራዊ አንድነቷን፣ ሰላምና ፀጥታዋን የማስከበር ታላቅ ሃላፊነት ተሸናፊ በሆነ የፖለቲካ ድርጅት ጫንቃ ላይ ሊወድቅ ነው ማለት ነው። ይኽ ግምት እውን ቢሆን ደግሞ ይህቺ ትንግርተኛ አገር አምስተኛ ተዓምር ልታስመዘግብ ነው።

ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ ጀምሮ እስከ ዛሬይቱ ኢትዮጵያ ድረስ የሚታየው የፖለቲካ አካሄድ የፖለቲካ አላማን በህዝብ ድምጽ ማስገዛት ሳይሆን፣ አላማን በህዝብ ላይ የመጫን አካሂድ ነው የሚስተዋለው። ይኽ አካሂድ ሊያበቃ ይገባል። በህዝባችን ፊት የፖለቲካ እምነታችን እና አመለካከታችንን በሃቅና በግልጽ አቅርበን ለመፍታት ወይም ለማስታረቅ ካልቻልን፣ በሁለቱ የፖለቲካ አካሂዶች ላይ ህዝብ በነጻ ምርጫው

ለሚሰጠው ውሳኔ ተገዥ ለመሆን መስማማት ይኖርብናል። ለስልጣን ሲባል በዋና ዋና የሃገር ጉዳዬች ላይ የሚደረግ መሞዳሞድ ለሃገርም ለወገንም አይበጅም። የተጨናገፊው የ1997 የህዝብ ምርጫ ውጤት ፋይዳም የሚያስገነዝበን ይህንኑ ነው።

## 5.1 ምን ሊደረግ ይገባል?

በፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ መሠረት የፖለቲካ ፓርቲዎች በውህደት፣ ግንባር/ህብረት በመመስረት ወይም በሶስተኛ ደረጃ በጥምረት ወይም ትብብር መልክ አብረው ለመስራት እንደሚችሉ ተደንግጓል።

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ቀደምት ክፍሎች ዘርዘር ባለ ሁኔታ ለማመልከት እንደተሞረው አንድነት እና በመድረክ ውስጥ የተሰባሰቡት የክልል ድርጅቶች በየፕሮግራማቸው ላይ ባሰፈሩአቸው ዓብይ በሚሏቸው የሀገሪቱ ጉዳዬች ላይ አንድ ወጥ አመለካከት ስር ለመንቀሳቀስ ሳይስማሙ ውህደት መፈፀም የማይገባቸው መሆኑን ለማብራራት ተሞክሯል። ፓርቲዎች የሚዋሀዱት በተወሰኑ የአመራር አባላት ፍላጐት ሳይሆን ተቋማዊ በሆነ ሁኔታ ፓርቲዎቹ ደንቦቻቸው በሚያዙት መሠረት ፕሮግራሞቻቸውን አጥፈው በአንድ ወጥ ፕሮግራም ስር ሲጠቃለሉ ነው። ሁሉም ድርጅታዊ ነፃነታቸውን እንደጠበቁ የጋራ ግምባር/ህብረት መመስረት አይቻላቸውም ወይ? ለሚለው ጥያቄም የሚሰጠውን መልስ ይህ ጹሁፍ በሁለት መልኩ ተመልክቶታል። በመርህ ደረጃ አንድ ፓርቲ ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር በግንባር/ህብረት የግንኙነት ቀመር መልክ ሊሰራ የሚገባው በዋና ዋና ሃገራዊ ጉዳዬች ዙሪያ ተመሳሳይ የሆነ ርእዬተ ዓለማዊ እይታ እና ፕሮግራማዊ መቀራረብ ሲኖረው ነው። ይህ ቅድመ ሁኔታ መኖሩ በማያሻማ ሁኔታ ሳይረጋገጥ ግንባር መመስረቱ ሃገራዊ ፋይዳ የለውም። በአሁኑ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንድነትና የመድረክ ድርጅቶች በዋና ዋና ሀገራዊ ጉዳዬች ዙሪያ ተመሳሳይ የሆነ ርእዮተ ዓለማዊ እይታና ፕሮግራማዊ መቀራረብ እንደማይታይባቸው በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ቀደምት ክፍሎች ለማመላከት ተሞክሯል። በተጨማሪም ይህ የግንባር/ህብረት የግንኙነት ዓይነት የምርጫ ክልል የመከፋፈልን በቅድመ ሁኔታነት የሚጠይቅ ነው። ሃገራዊ ወይም ብሄር-ዘለል ፓርቲ ነኝ ብሎ የተቋቋመ ፓርቲ በህግ ሊወዳደርባቸው የሚገባ ክልሎችን ለብሄር/ክልል ድርጅቶች የሚለቅ ከሆነ፣ እራሱን ወደ ክልል ፓርቲነት ለመለወጥ ፈቃደኛ ሁኗል ማለት ነው። ስለዚህ ምዝገባውን ከሃገር አቀፍ ፓርቲነት ወደ ክልል ፓርቲነት ማሸጋሸግ ይጠበቅበታል።

ኢህአዴግ እንደሚያደርገው የክልላዊ ፓርቲዎችን "የመድረክ ድርጅቶች ዲሞክራሲያዊ ግንባር" በሚል ስያሜ ለኢህአዴግ እንዳአማራጭ ሁኖ ለማቅረብ ታስቦም ከሆነ፣ ዓላማው ኢህአዴግን ከስልጣን ለማፈናቀል ወይም ይህ ካልተቻለ ስልጣን ለመጋራት ከማሰብ የዘለለ ሊሆን አይችልም። ኢህአዴግን ከስልጣን ማውረድ ብቻ የትግሉ ሁሉ አልፋ እና ኦሜጋ የሚመስላቸው ሃይሎች ካሉ ይህ አካሄድ ችግር አለው። ከኢህአዴግ የጐሣ ፖለቲካ የተለዬ፣ በሃገራዊ ራዕይ ላይ የተገነባ ትክክለኛ አማራጭ ሳያቀርቡ ኢህአዴግ በተጓዘበት መንገድ ኢህአዴግን "በምርጫ ለማሸነፍ" መነሳሳት ለኢትዮጵያ ህዝብ አንድነት መጠበቅ፣ ለሃገር እድገት እና ልዕልና እንዲሁም ለዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እውን መሆን ሊደረግ የሚገባውን የላቀ ሃገራዊ ትግል ለፖለቲካ ስልጣን ሲባል በሚደረግ ጠበብ ባለ ትግል ለመተካት ከመሞከር ተለይቶ አይታይም።

ስለ ግንባር ከተነሳ አይቀር ውይይት ሊደረግበት የሚገባ ተዘማጅ ርእስ አለ። ይኸውም አንድነት ከኢህአዴግ ነፃ በሆነ ሁኔታ ከተቋቋሙና ከሚንቀሳቀሱ ብሄር - ዘለል ፖርቲዎች ጋር ሊኖረው የሚገባው ግንኙነት ሊታሰብበት የሚገባ ጥያቄ የመሆኑ ጉዳይ ነው። ተመሳሳይ ወይም በጣም ተቀራራቢ የሆነ ራዕይ፣ ተልእኮና ዓላማዎች ያሉዋቸው ሃገራዊ ወይም ክልል - ዘለል ፓርቲዎች ከኢህአዴግ ንክኪነት ነፃ በሆነ ሁኔታ የሚንቀሳቀሱ መሆናቸው ሲታመንበት፣ ፓርቲን በዲሞክራሲያዊ ሁኔታ በመገንባቱ ጥያቄ ላይ ልዩነት ቢኖር፣ ድርጅታዊ ነፃነታቸው እንደተጠበቀ ሁኖ የምርጫ ክልልን እስከመከፋፈል ድረስ ሊያመራ የሚችል የጋራ ግንባር ቢመሰርቱ፣ የገዥ ፓርቲውን ጨምሮ ሌሎች በክልል ፖለቲካ ዙሪያ ለተደራጁ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ጥምረቶች የተጠናከረ ሃገራዊ አማራጭ ሁነው ሊቀርቡ ይችላሉ። አንድነት ጥምረት በተሰኘው ሶስተኛው የፓርቲዎች ግንኙነት ቀመር መሠረት በመድረክ ውስጥ ከተሰባሰቡት የክልል የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር አብሮ መስራቱ ተገቢ እና አግባብነት ያለው አካሄድ ነው። ለአንድነትም ሰፊ እና ሃገራዊ የፖለቲካ ምህዳር መፍጠር የሚቻለው በዚህ የግንኙነት ቀመር ነው። ይሁንና ይህ ቀመር አንድነትን በመድረክ ውስጥ በአባል ድርጅትነት የሚያስገባ ሳይሆን ከመድረክ ጋር በእኩልነት ደረጃ የሚያስቀምጥ የጉንዬሽ ግንኙነትን መፍጠርን የሚጠይቅ ነው። ሃሳባቸውን በአጭሩ በመግለፅ ረገድ ልዩ ችሎታ ያካበቱት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም የካቲት 21/ 2001 በአዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ ባወጡት ፅሁፍ የአንድነት እና የመድረክ ግንኙነት በሚያስማሙ ጉዳዬች ዙሪያ የሚደረግ ተግባራዊ (Functional) ግንኙነት እንጅ መዋቅራዊ (structural) ግንኙነት ሊሆን አይገባም ሲሉ በትክክል አስቀምጠውታል። በዚህ ፀሐፊ በኩል ለማለት የሚፈለገውም ይኸንኑ ነው።

በገዥው ፓርቲ በኢህአዴግ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ እንዲታቀብ መደረጉ፣ በፕሬስ ነጻነት ላይ መንግስት አሳሪ አዋጅ ማጽደቁ፣ የሰብዓዊ እና የዲሞክራሲያዊ መብቶች መታፈናቸው፣ የህግ የበላይነት መጣሱ፣ በነጻነት ሊንቀሳቀሱ የሚገባቸው ተቋሞች በገዥው ፓርቲ ተጽእኖ ስር መውደቃቸው፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንቅስቃሴ መገደቡ፣ የሙያ እና የሲቪል ማህበረሳቡ ነጻ አደረጃጀት መሽበቡ፣ ወገናዊ ያልሆነ የምርጫ ቦርድ ጉዳይ፣ ሠራዊቱ እና ፖሊሱ እና ደህንነቱ ለህገመንግስቱ ብቻ መወገን የሚገባቸው የመሆኑ እና የመልካም አስተዳደር መስፈንን በተመለከተ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ሃይላቸውን አሰባስበው በጋራ ሊንቀሳቀሱባቸው የሚችሉባቸው የትብብር መስኮች ናቸው፡፡

ይህም ማለት በድህር ግንቦት 1997 ተጨባጭ የፖለቲካ ሁኔታ በኢትዮጵያ ለዲማክራሲያዊ ስርዓት ምስረታ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ በሆኑት ከላይ በተቀጠሱት የነፃ ተቋማት መመስረት ላይ የሚያተኩር መሆን ይኖርበታል ማለት ነው፡፡

አንድነት በጀመረው የሰላማዊ እና ህጋዊ የፖለቲካ ተቃውሞ መስመሩ በሃገራዊ ደረጃ ለኢህአዴግ እውነተኛ አማራጭ መሆኑን በተግባር ማስመስከር መቻል አለበት፡፡ የቅንጅትን ፕሮግራም የኔ ፕሮግራም ነው ብሎ መቀበሉ በቂ ሊሆን አይችልም፡፡ ከ1997 ወዲህ የህዝቡ መነሳሳት ቀዝቅዟል፡፡ ይህን የቀዘቀዘ የፖለቲካ አየር ለመግፈፍ ከሚጠይቀው በሳል የፖለቲካ ስትራቴጂ ጋር የሚመጥን፣ ያሉትን ዋና ዋና ሀቀኛ ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶችን ለማስተባበር የሚያስችል የፖለቲካ አጀንዳ መቅረፅን ይጠይቃል፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ ሁለት ዓይነት አካሄዶችን መከተሉ ትክክል ይመስላል፡፡ 1ኛ/ በክልል - ዘለል ፓርቲነት ከተቋቋሙት መሃል በኢህአዴግ የይስሙላ ተቃዋሚነት ወይም አጃቢነት ከማይጠረጠሩት፣ ይሁንና በዲሞክራሲያዊ ፓርቲ አደረጃጀትና አሰራር ዙሪያ ባለ ልዩነት ምክንያት ለጊዜው ድርጅታዊ ውህደት ለመፍጠር ከማይቻልባቸው የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ግንባር መፍጠሩ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡ 2ኛ/ የክልል ፓርቲዎችን በተመለከተ በመድረክ ውስጥ ከተሰባሰቡት የክልል የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ከምርጫ በፊት መቅደም ባለባቸው የዲሞክራሲያዊ ምርጫ ቅደመ ሁኔታዎች መሟላት ዙሪያ ተመሳሳይ አቋም የመያዝን ዓላማ መሠረት ያደረገ፣ ካለፈው የቅንጅት እና የህብረት ግንኙነት ተገቢውን ልምድ የቀሰመ፣ በአግባቢ የፖለቲካ ጉዳዬች ዙሪያ የተገነባ (Functional) ግንኙነት ሊመሠርት ይችላል፡፡ አሁን በተደረሰበት የኢትዮጵያ ፖለቲካ ተጨባጭ ሁኔታ አንድነት የቅንጅት ሃቀኛ ወራሽ መሆኑን ለህዝብ ተቀባይነት ባለው መልኩ ለማስመስከር የሚችለው ይህን በሁለት ዘርፍ ተከፍሎ የቀረበ ታሪካዊ ሃላፊነት ለመወጣት የቻለ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

# ዋቢ ሰነዶች


1. *ተቃዋሚዎች ሆይ! የመድረክ እና የጥምረት ስትራቴጂያችሁን ትታችሁ የተሻለ ሌላ አማራጭ አቅርቡ፣* ኢኮኖሚ፣ የካቲት 22 (16) 2001፣
2. አስፋው ቦጋለ፣ *የብሄሮች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ፅንሰሃሳብ እና አባሪ ችግሮች፤* መድረክ 1985 1 (1)
3. ተሰማ ወንጄ፣ *ዘመናዊ ህገ መንግሥት በኢትዮጵያ - ከየት ወዴት? አንዳንድ የትኩረት ነጥቦች፣* መድረክ 1986፡ 1 (2)
4. አንዳርጋቸው አሰግድ፣ 1992፣ *ባጭር የተቀጨ ረዥም ጉዞ፣*አዲስ አበባ፣ ሴንትራል ማተሚያ ቤት
5. ተስፋዬ መኮንን፣ 1985፣ *ይድረስ ለባለ ታሪኩ፣* አዲስ አበባ፣ ብራና ኤሌክትሮ አሳታሚ፣
6. Turton, D. 2006. *Ethnic Federalism: The Ethiopian Experience in Comparative Perspective*, Addis Ababa, Addis Ababa University Press.
7. ነጋሶ ጊዳዳ (ዶ/ር) 2001፣ *የብሄር እና የግለሰብ መብት ጥያቄ በኢትዮጵያ ትናትናና ዛሬ፣* ታህሳስ 18፣ 2001 (በምክክር መድረክ ሴሚናር ላይ የቀረበ)
8. ገብሩ አስራት፣ *በኢትዮጵያ የፌደራል መንግሥታዊ አወቃቀር ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች* (ታህሣሥ 18/2001፣ በኢምፔሪያል ሆቴል በተደረገ የምክክር መድረክ ሴሚናር ላይ የቀረበ )
9. ___________ ፣ የኢህአዴግ አብዮትየዋ ደሞክራሲና ችግሮቹ (ታህሣሥ 18/2001፣ በምክክር መድረክ ሴሚናር ላይ የቀረበ)
10. መራራ ጉዲና (ዶ/ር) 2001፣ *የኢህአዴግ "አብዮታዊ ዲሞክራሲ" እና ችግሮቹ፣* ታህሳስ 18/2001 (በምክክር መድረክ ሴሚናር ላይ የቀረበ)
11. *በአፍ መፍቻ ቋንቋ መማርና አገራዊ ቋንቋ፣* አዲስነገር፣ መስከረም 21 ( 31 ) መስከረም 17/2001
12. ቅንጅት ለአንድነት እና ለዲሞክራሲ፣ የምርጫ ማኒፌስቶ፣ 1997፣ አዲስ አበባ፣
13. አንድነት ለዲሞክራሲ እና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ፕሮግራም፣ ሰኔ 2000፣
14. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት፣ 1987 ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ ነሐሴ 15፣ አዲስ አበባ
15. የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲ ግንባር (ኢህአዴግ) ፕሮግራም፣ 1987
16. ባህሩ ዘውዴ (ዶ/ር) *የሶስት ሺህ ወይስ የመቶ አመት ታሪክ?*ውይይት፣ 3ኛ ሴሪ፣ ቅጽ 1፣ ቁጥር 1 መጋቢት 1984
17. Bonnic K, Hollcomb and Sisai Ibssa. *The Invention of Ethiopia: The Making of a Dependent Colonial State in North East Africa*, Trenton, 1990. (የሶስት ሺህ ወይስ የመቶ ዓመት ታሪክ? በተሰኘው የዶ/ር ባህሩ ዘውዴ ፅሁፍ ውስጥ የተጠቀሰ)
18. ላጲሶ ዲሌቦ፣ 1987፣ *የኢትዮጵያ ረዥም የሕዝብ እና የመንግሥት ታሪክ፣* አዲስ አበባ
19. ባዩ ይማም፣ *ስርዓተ ፅህፈት፣* ውይይት፣ 3ኛ ሴሪ፣ ቅፅ 1፣ ቁጥር 1 መጋቤት 1984
20. Bartinic A and Niecko J.M. 1979. *GESCHICHTE ÄTHIOPIENS (History of Ehtiopia)*; Akademia-Verlag, Berlin, East Germany. (Translated from German into Amharic - prepared for publication)
21. National Atlas of Ethiopia, 1988. *The Great Ethnic Migrations Ca. 1520 - 1660.* Ethiopian Mapping Authority; Berhanena Selam Printing Press, First Edition, Addis Ababa.
22. Rendel, Sidgwolk and Jacson. 1978. An Introduction to Political Thought, London.
23. ስዩ አብርሃ፣ *የፖለቲካ ድርጅቶች የሕብረት ጥያቄ በኢትዮጵያ ትናትና ዛሬ፣* ታህሣሥ 18፣ 2001 (በምክክር መድረክ ሴሚናር ላይ የቀረበ)
24. *ቅንጅት ላይ የተፈፀመው ችግር እንዳይደገም እንጥራለን፣* ሪፖርተር፣ መጋቢት 6 2001፣

25. Meles Zenawi. *African Development: Dead Ends and New Beginings*, (Unpublished Incomplete monograph) www.gsb.Columbia.edu/ipd/programmes/item.cfm?prid. Downloaded: August 2006.
26. Evans, P. 2007. *In Search of The 21st Centuary Developmental State*, University of California, Berkeley.
27. Weiss, L. 2000. *Developmental States in Transition: Adopting, Dismantling, Innovating and Normalizing*, The Pacific Review, 13 (1)
28. Mkandawire, T. 2001. *Thinking about Developmental States in Africa*, Cambridge Journal of Economics 25(3)
29. Johnson, C. 1982. *MITI and the Japanese Miracle*, CA. Stanford University Press
30. White, G. 2006. *Towords a Democratic Developmental State*. IDS Bulletin, 37(4)
31. Greenfield, R. 1965. *Ethiopia: A New Political History*, Pallmall Press, London
32. Trimingham, S. 1952. *Islam in Ethiopia*, 1st Edition, Frank Cass Co. Ltd, London.
33. *ቅንጅትን ያፈረሰው የጥቂት ሰዎች ግለኛ እና አምባገነናዊ አሠራር በሌላ መልክ በአንድነት ውስጥ ሲከሰት*፣አዲስ አድማስ፣ የካቲት 21/2001.
34. Randal, V. 2007. *Political Parties and Democratic Developmental States*, Development Policy Review 25 (5): 633-652.
35. Grabowski, R. 1994. *The Successful Developmental State: Where does It come from?* World Development. Vol. 22 (3)

# እዝል

## "ራስ ይሸብታል እንጅ ልብ አይሸብትም"

የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ በጥናታዊ ጽሁፍ አቀራረብ ባልተለመደ ሁኔታ በእዝል መልክ የተደረበ ጽሁፍ ያቀረበበት ምክንያት በየጊዜው ምርጫ በተቃረበ ቁጥር እየተነሳ ከምርጫ በኋላ የሚጣለውን የፖለቲካ ፓርቲዎች ትብብር ጥያቄ በተመለከተ <u>"በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች አሰላለፍ እና የፖለቲካ ትብብር ጥያቄ"</u> በሚል ርእስ ያዘጋጀውን ጥናታዊ ጽሁፍ ከምን እይታና ተግባራዊ የተሳትፎ ልምድ ተነስቶ ነው ለማቅረብ የፈለገው ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት አስፈላጊ መስሎ ስለታየው ነው።

በርእሱ የተጠቀሰው አባባልም የተወሰደው ተዝቆ ከማያልቀው ባህላዊ ቅርሳችን ውስጥ ነው። የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ንቁ ተሳታፊ የነበረ ነው። በ1964 የአ.አ ዩኒቨርስቲ ሁለተኛ ዓመት ተማሪ እያለ ዓ.ም ከነ ግራማቸው ለማ፣ ጌታቸው ማሩ እና አማረ ተግባሩ ጋር የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የተማሪዎች ማህበር (ኡዝዋ) የሥራ አስፈፃሚ ኰሚቴ አባል ሁኖ ሠርቷል። በዚያው ዓመት ተማሪዎችን ለረብሻ ቀስቅሳችኋል በሚል ከአዲስ አበባ ወለቂጤ መንገድ ላይ በሚገኝ ቦተር በተሰኜ ቦታ ከሌሎች የኡዝዋ መሪዎች ጋር ለሰባት ወር ታስሯል። ከእስር በኋላ ከሌሎች የማህበሩ የአመራር አባላት ጋር ከዩኒቨርስቲ ለአንድ ዓመት እንደሚታገድ ስለተገለፀለት፣ ትምህርቱን ለመቀጠል በ1965 መስከረም መጀመሪያ ላይ ወደ አሜሪካ ሄደ። በ1967 በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር (ESUNA) ሊቀመንበር ሁኖ አገልግሏል። የየካቲት 1967 ስር ነቀል የመሬት አዋጅ በደርግ በታወጀበት ጊዜ አዋጁን በመደገፍ አለመደገፍ ጥያቄ ላይ በማህበሩ አመራር ውስጥ ውዝግብ ይነሳል። በዚያን ወቅት ማህበሩን ኢህአፓ ጠቅሎ ሊይዘው ተቃርቦ ስለነበር፣ አብዛኞቹ የማህበሩ አመራር አባላት አዋጁ ሊደገፍ አይገባም ሲሉ፣ ይህ ፀሐፊ እና ሌሎች ሁለት የአመራር አባላት ሊደገፍ ይገባል የሚል አቋም ያዙ። የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ በሊቀመንበርነቱ የማህበሩ ማህተም በእጁ ነበር። የ1967ቱ የመሬት አዋጅ የሃገሪቱን መሬት የሕዝብ ሃብት እንዲሆን ያደረገ ነው። የተማሪው እንቅስቃሴ ሲታገልለት ከቆየው የመሬት ላራሹ ጥያቄ ጋር ልዩነት ቢኖረውም፣ የጉልታዊ/ባላባታዊ ስርዓቱን በማስወገድ ረገድ ይህ ቀረሽ የማይባል ነበር። የፊውዳሉን የመሬት ስሪት መሻር በኢትዮጵያ ለብሄረሰቦች እኩልነት መረጋገጥ ወሳኝ ኢኮኖሚያዊ መሠረት ነበር። በመሆኑም በወቅቱ ሊደገፍ የሚገባው አዋጅ ነበር ከሚል ጠንካራ እምነቱ በመነሳት፣ ከደንባዊ እና ዲሞክራሲያዊ አሰራር ውጪ የማህበሩን አርማ በመጠቀም በማህበሩ ስም የ67ቱ የመሬት አዋጅ ሊደገፍ እንደሚገባ ጽፎ እና አትሞ የኢዙናን (ESUNA) አቋም ሲጠባበቅ ለነበረው የአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር (ESUE) ይልካል። ኢህአፓ አዋጁ እንደወጣ ደግፎ ከሳምንታት በኋላ አቋሙን መቀየሩ ይታወቃል። ደግበወቅቱ በአማረ ተግባሩ ይመራ የነበረው በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ደብዳቤው የማህበሩን (የኢዙናን) ደንብ የተከተለ መሆኑን ሳያጣራ አዋጁን ደግፎ መግለጫ ያወጣል። በዚህ የማህበሩን ደንብ በጣሰ ድርጊቱ በ1967 መጨረሻ ላይ በኢህአፓ አቀነባባሪነት የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ በኢዙና 19ኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ተወግዞ ከማህበሩ ተባሯል። ቆየት ብሎም በ1969 በአሜሪካ ምድር በኢህአፓ ቡድን ክፉኛ ሊደበደብ በቅቷል። በ1969 መጨረሻ ላይ የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ ከአሜሪካ ወደ ሃገሩ ይመለሳል።

በ1970 ዓ.ም የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ በአዲስ አበባ የአፍሪካ ኢኰኖሚክ ኰሚሽን ሲሰራ ይቆያል። በ1971 መጀመሪያ ላይ ወዝ ሊግ አመራር ውስጥ በነበሩ የበፊት የዊንጌት በኋላም የአ.አ ዩኒቨርስቲ የክፍል ጓደኞቹ አቅራቢነት በደርጉ ዋና ፀሐፊ በሻምበል ፍቅረሥላሴ ወግደረስ ትእዛዝ በየካቲት 66 ፖለቲካ ት/ቤት አስተማሪ ሁኖ ይመደባል። ከዚያም በኢሠፓአኰ ዘመን "መስከረም" ይሰኝ ለነበረው የፓርቲው የርእዩተዓለም መፅሄት ዋና አዘጋጅ፣ በኋላም ኢሠፓ ሲመሠረት የፓርቲው ማእከላዊ ኰሚቴ የኢኰኖሚ እና ማህበራዊ ጉዳይ መምሪያ ምክትል ሃላፊ ሁኖ ሠርቷል።

በ1980 ላይ የሃገሪቱ የእዝ ኢኮኖሚ ያጋጠሙትን ችግሮች በመገምገም የማሻሻያ ሃሳቦች እንዲያቀርብ የተቋቋመውን ብሄራዊ የኤክስፐርቶች ቡድን አመት ያህል የፊጀ ሥራ ከመምሪያ ሃላፊው ጋር በመሆን መርቷል፣ አስተባብሯል። በ1981 መስከረም ወር መጀመሪያ ላይ የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ የእዝ ኢኰኖሚው ወደ ቅይጥ ኢኰኖሚ (Mixed Economy) እንዲሸጋገር በቀረበው ሃሳብ ላይ ከኢሠፓ ሊቀመንበር መንግሥቱ ሃይለማርይም ጋር አራት ሰዓት ተኩል የፈጀ የግንባር ለግንባር ክርክር እና አለመግባባት በኋላ በሊቀመንበሩ ትእዛዝ አንድ ዓመት ያህል ለቆዬ እስር ይዳረጋል። ከእስር እንደተፈታም ከኢሠፓ እንዲባረር እና ወደ ስራ እንዳይመለስ ይደረጋል። ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ የመፅሄት፣ የትርጉም እና የአማካሪነት ሥራ በመስራት ላይ ይገኛል። መድረክ በተሰኜ በ1985 ተጀምሮ በነበረ መፅሄት አማካይነት ጥናታዊ ፅሁፎችን በብዕር ስም አውጥቷል። ሰኔ ወር 2000 ዓ.ም ላይ የአንድነት ለፍትህ እና ለዲሞክራሲ ፓርቲ የሥራ አስፈፃሚ ኰሚቴ አባል ሁኖ በመመረጥ የፓርቲው የጥናት እና ምርምር ቋሚ ኰሚቴ ሰብሳቢ ሁኖ ይመደባል። በዚህም ከ19 ዓመት በኋላ እንደገና ወደ ፖለቲካው አለም ይመለሳል። ዓመት ሳይሞላው የፖለቲካ አቋሙን በጋዜጣ ላይ በመግለፁ እና የፓርቲውን የተወሰኑ የአመራር አባላት የፓርቲውን በሄራዊ ምክር ቤት ሉዓላዊነት ተጋፍታችኋል ጥሳችኋል በማለታቸው ከአንድነት ሥራ አስፈፃሚ ኰሚቴ አባልነቱ ለአንድ ወር ታግዷል። "በፊት የወጣን ጆሮ በኋላ የወጣ ቀንድ በለጠው" ሆኖ ነው እንጂ ነገሩ የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ወደ አርባ ዓመት ለተጠጋ ጊዜ በመጀመሪያ ላይ በንቁ ተሳታፊነት በኋላም በታዛቢነት የኢትዮጵያን ፖለቲካ በጥሞና ተከታትሏል። ንቁ ተሳታፊ በነበረበት ጊዜ እንደሌሎቹ የግራ ርእዩተዓለም አቀንቃኝ ዘመንተኛ ጓደኞቹ ሁሉ፣ ሲያነበንብ የነበረውን ይሁንና በቅጡ ያላስተዋለውን የግራ ርእዩተዓለም የህዝቡን ፍላጐት ባላገናዘበ መልኩ በሃገሪቱ ላይ እንዲጫን በማድረግ ሂደት ተሳትፏል። ይህ አካሄድ በሃገር ላይ ላደረሰው ጥፋት የድርሻውን የታሪክ ተጠያቂነት በፀጋ ይቀበላል።

የፖለቲካ ንስሃ መግባት  ካስፈለገም የሚከተለውን ማለት ይቻላል። የቀድሞው ትውልድ የፖለቲካ ብስለት ምንጩ የሀገርን ታሪክና ባህል መረዳት፣ ሕዝቡ ለመደጋገፍ ያለውን ብርቱ ስሜት በማክበርና ይህንንም ስሜት በተገቢው መልክ በመቀስቀስ ላይ የተመሠረተ ነበር። በመሆኑም ነው ከዘመናዊነት ጋር ሳትተዋወቅ የኖረችው ሀገራችን የሕዝቦቿን አንድነት፣ ሀገራዊ ነፃነቷንና ሉዐላዊነቷን አስከብራ የኖረችው። ከአዲሱ ትውልድ መሀል የተማረው ክፍል ይህን የአባቶቹን የፖለቲካ ቅርስ በሚገባ ለማገናዘብ ባለመፈለጉ ብቻ ሳይሆን በዚያ ከዘመናት ልምድ ነጥሮ በወጣ ክቡር ቅርስ ላይ ንቀት በማሳየቱ፣ ለሀገሩ ዘመናዊነት ከዓመታት በፊት የጀመረው ትግል ከሥር አንስቶ ውሉን የሳተ፣ በስሜታዊነት የሚመራና የሚካሄድ ነበር። ቀለም ቀመስ የሆነው አዲሱ ትውልድ ለዘመናዊነት የተጋለጠ እንደመሆኑ ትግሉን በተሟላ የሀገርና የዓለም አቀፍ እውቀት ማስደገፍ ሲጠበቅበት፣ የገዛ ሀገሩን ከባዕዳን ኃይሎች በተሟላ መልካቸው እንኳን ሳይሆን በቁንፅል የታቀዱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሞዴሎች መፈተሻ ጣቢያ በማድረግ በሀገሩ ላይ ታሪክ የማይረሳው በደል ፈፅሟል፤ በመፈፀምም ላይ ይገኛል። ይህ ትውልድ ለሀገር እድገትና ልዕልና በሚደረግ የጋራ ትግልና ለፖለቲካ ስልጣን ሲባል በሚደረግ ወገናዊ ትግል መካከል ያለውን ከፍተኛ ልዩነት ባለመገንዘብ የከፈለው መስዋእትነት ከባድ ነው። በሂደትም በውስጡ በተከሰተው መከፋፈል ሳቢያ እርስ በርስ በመጠፋፋቱና በሌላ በታጠቀ ኃይል ለዓመታት ተመቻችቶ በመገኘቱ፣ እጅግ ከጋለ ሀገራዊ ስሜቱ አንፃር የሀገር ገንቢ ሊሆን ይችል የነበረ እልፍ አእላፍ የወጣት ኃይል ለአሳዛኝ እልፈት ተዳርጓል። አሁንም የዚሁ ትውልድ የተወሰነ ክፍል እርምጃውን ከሀገሩ ታሪካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ማገናዘብ የሚያስፈልገው መሆኑን የተቀበለ አይመስልም። ሲመራበት የነበረው የግራ ርዕዮተ ባላሰበው ፍጥነት ስለተንኮታኮተበት በምትኩ የወየበ ለዘብተኛነትና የክልል ፅንፋዊ ብሔረተኛነት ቦታውን እንዲሞላ እያደረገ ነው። በዚህ ሁኔታ፣ በአዲስ መልክ ከምዕራቡ ዓለም የወሰደውን (ወይም የተሰጠውን) የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሞዴል ከቀድሞው የግራ የፖለቲካ ቅሪቶች ጋር አቀናጅቶ በተቻኮለ ሁኔታ ተግባራዊ በማድረግ ለዳግም ጥፋት ሁኔታዎችን በማመቻቸት ላይ የሚገኝ ይመስላል። በኢትዮጵያ የተማረው ክፍል መድረሻውን በውል ለይቶ ባያውቀውም በአጠቃላይ መልኩ የሶሺያሊስት ርዕዮተ ዓለምን ከመቀበል አንፃር የጎላ ልዩነት ያልነበረውን ያህል፥ በብሔር ጥያቄና ለዚህ ጥያቄ እንደመፍትሄ በቀረበው የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ላይ ግን ከመጀመሪያው አንስቶ የተከሰተው ልዩነት አሁንም እንደቀጠለ ነው። አሁን በሚሰራበት ህገ-መንግሥት ውስጥ የተደነገገው የብሔሮች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትም የነበረውን ልዩነት እያሰፋው እንጅ እያጠበበው አልመጣም። አሁንም ቢሆን ልክ እንደ በፊቱ መድረሻው በውል የማይታወቅ በጭፍን የተጀመረ ጉዞ ነው። ልክ እንደ በፊቱ አሁንም የሙከራ ጣቢያ የሆነችው የሁላችንም ሀገር ኢትዮጵያ ናት።

ይህ ጽሁፍ ይህን ያለፈውን የሃገሪቱን ታሪክም ሆነ የሀገራችን ተራማጅ የህብረተሰብ ክፍል ያለፈበትን የትግል ታሪክ መለስ ብሎ ማየትን መነሻ አድርጐ የተዘጋጀ ነው። እንደመሆኑም ወደፊት በይበልጥ እየተተነተኑ በጥናታዊ ጽሁፍ መልክ ሊዘጋጁ የሚችሉ አራት ያህል ርእሶችን በማካተት እጭቅ ያሉ ሃሳቦችን ይዞ የቀረበ ነው። አንዳንድ አንባቢያን ይህ ዓይነት አቀራረብ ላይጥማቸው ይችላል። ፀሀፊው የበኩሉን ከሰነዘረ ማረም፣ ማስተካከል፣ ይበልጥ ማዳበር የሁሉም ድርሻ ሊሆን ይገባል። የግል ጋዜጦች አዘጋጆች እራሳቸውም ሆኑ ሌሎች ምሁራንን እየጋበዙ በጽሁፉ ላይ የሚኖሩአቸውን ትችቶች ቢያስተናግዱ ጉዳዩን ለማብላላት ይረዳል። የሚያስተናግዱአቸው ትችቶች በግለሰብ ላይ ሳይሆን በሃሳብ እና አመለካከት ላይ ቢሆኑ ይበልጥ ትምህርታዊ ይሆናል። አስተያየትና ትችት ለመላክ ለምትፈልጉ ፀሐፊውን በ amha.dagnew@gmail.com ልታገኙት ትችላላችሁ።